# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ዛሬም እንደ ጠፍ ከብት . . . ?

ዛሬ ዛሬ በአዲስ አበባ የሚገኙ አንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንደሚያካሒዱት ጠንካራ የአገልግሎት መርሐ ግብር በአንዳንድ የገጠር ከተሞች የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶችም እየታየ ነው:: በዚህም በሃይማኖታቸው የጸኑ ለቤተክርስቲያናቸው የሚያስቡ፣ በመልካም ሥነ ምግባር የታነጹ ወጣቶችን እያፈሩ ነው:: በተጓዳኙም የበግ ለምድ ለብሶ የመጣውን ተኩላ፤ የእውነት በግ ነው በማለት ተከትለው ከእውነተኛው መንገድ እየወጡ ያሉ የዋህ አርቶዶክሳውያን ወገኖቻችን ቁጥር ጥቂት አይደለም:: ይህ ሁኔታ በተለይ እኔ ባለሁበት አርባ ምንጭ ከተማ በስፋት እየተስተዋለ ነው::

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች፣ ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ:: ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ::» እንዳለ /ማቴ.፯÷፲፮/ ጎምዛዛ ፍሬ ከሚያፈሩ ተኩላዎች መጠንቀቅ ስላልቻልን እንደ ጠፍ ከብት እየተነዳን ከእውነት እየራቅን የምንገኝ ጥቂቶች አይደለንም:: ይህ ሁሉ የሆነው፤ አሁንም እየሆነ ያለው በቂ የሃይማኖት ትምህርት ባለመማራችን የተነሣ በመንገድ፣ በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታም ቢሆን የሚያጋጥመንን ፈተና ባለመቋቋማችን ነው:: እነዚህ ከሀድያን የተሰወረ እኩይ ዓላማ በውስጣቸው ሰንቀው የእውነት ሐዋርያ በመምሰል ከምእመናኑ ጋር ሊመሳሰሉ ቢሞክሩም ለሁሉም ጊዜ አለውና ተሰውሮ የነበረው ዓላማቸው አሁን አሁን ግን ይፋ እየሆነ መጥቷል:: ስለዚህ እንዳንፀፀት ከእነዚህ መሰሪዎች አካሔድ ልንርቅ ራሳችንንና ቤተሰቦቻችንን ልንጠብቅ ይገባል::✤

*ገበየሁ ገተሎ*
*አርባ ምንጭ*

## አስመሳዮችን መስለው እንጂ ሆነው አናገኛቸውም

በአምባሰል ወረዳ መምህር ለመሆን ሥራ በማግኘቴ ልቤ ሐሴት አድርጋለች:: ምክንያቱም የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀሉ ያረፈባት ዳግማዊቷ ኢየሩሳሌም ግሸን ደብረ ከርቤ በዚያ በመገኘቷ ነው:: በየዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን የሚከበረውን ታላቅ በዓል በሰከነ መንፈስ በቦታው ተገኝቼ እንዳከብር ያለውንም ሁኔታ እንድከታተል ሁኔታዎቹ ተመቻችተውልኛል:: በዚሁ አካባቢ አንዳንድ የተመለከትኳቸው ነገሮች ብዕሬን ከወረቀት እንዳገናኝ አደረገኝ:: ከበጎች መካከል ፍየሎች ተቀላቅለው መገኘታቸው የትንቢቱን ፍጻሜ የሚያሳይ በመሆኑ፤ ዛሬም ፀጉራቸውን ጎንጉነው ለምድ /ቆዳ/ ለብሰው ባንዲራ ይዘው፣ መስቀል ከመቁጠሪያ ጋር አንግተው፣ ሰንሰለትና ካቴና ይዘው ያገኙትን የየዋሕ አድማጭ ጆሮ በድንጋጤና በስጋት የሚሞሉ «ባሕታዊ ነን» ባዮች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: «ባሕታዊ ነን»ባዮች ቤተክርስቲያኗን ከነሥርዓቷ፣ አገልጋዮቿንና ምእመናኑን ጨምሮ ይዘልፋሉ፣ ይተቻሉ ይሰድቡማል::

ባለራዕይና ባለትንቢት ነን ባዮቹ «ባሕታውያን» ራእይ አየን እያሉ ሕዝበ ክርስቲያኑን እያታለሉ ነው:: አንዳንድ ምእመናንም እውነት እየመሰላቸው የነዚህኑ አሳሳቾች ትምህርት እየሰሙ ተከታዮች ሆነው ሲመላለሱ ለችግር የተጋለጡትን ቤት ይቁጠራቸው:: ይህ ሁኔታ በተለይ በንግሥ በዓላት ላይ ጎልቶ ይታያል:: «የበግ ለምድ ለብሰው ይመጣሉ» ነውና የተባልነው እናት ቤተክርስቲያንን እየተቹ ወንጌልን ሳይሆን ወንጀልን እየሰበኩ ካሉት እንራቅ፤ ራሳችንን እንጠብቅ፤ አስመሳዮችን ሁሌም መስለው እንጂ ሆነው አናገኛቸውምና::✤

*መምህር እንዳለ አበበ*
*አምባሰል*

## እንደ ክርስቲያንነትህ ምን አደረግክ?

ይህችን ደብዳቤ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ሐመር መጽሔት በ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ግንቦት/ሰኔ ፳፻ ዓ.ም ከአንባብያን ለአንባብያን ዓምድ ላይ ላወጣችው «ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ማን ያስከብር» ለሚለው ጽሑፍ እውነታውን ለማስቀመጥ ስለፈለግሁ ነው::

የካቲት ፳፰ ቀን ፳፻ ዓ.ም ወርሃዊ መርሐ ግብር በማካሔድ ላይ እያለን ከቀኑ 12:00 ሰዓት አካባቢ አንዲት ከቤተክርስቲያን የማትጠፋ የአካባቢው ወጣት፤ ሁለት ሕፃናት ልጆቿን ይዛ ወደ ዐውደ ምሕረቱ መጣች:: የዛሬ ዓመት ሆስፒታል ውስጥ በምጥ ተይዤ በአደገኛ ሁኔታ እያለሁ በሕይወት እንድተርፍና በሰላም እንድገላገል ወደ አምላኬ ወደ አማኑኤል ልመናዬን አቀረብኩ፤ ስእለትም ተሳልኩ:: ስእለቱም «በሰላም ተገላግዬ በሕይወት ከተረፍኩ የልጆቼን ልደታቸውን በደጅህ አከብራለሁ የሚል ነበር::» በማለት ወደ እኛ መጥታ አስረዳችንና ጥያቄ አቀረበች:: በወቅቱ ልደት በቤተክርስቲያን ማክበር እንደማይቻል ነገር ግን በወንዶች መግቢያ በር በኩል ለማስታወሻ ፎቶ እንድታነሣቸውና የያዘችውን ዳቦ በመጠለያ ውስጥ ቆራርሳ እንድታከፋፍል ነገርናት:: እሷም ይህንኑ አደረገች:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ጸሐፊው ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ባናውቅም ትክክል ያልሆነ መርጃ ሰጥቷል::

፩ኛ. ቤተ መቅደስ ውስጥ ይህ ተደረገ ሲል ቤተመቅደስ ብሎ በግልጽ ያስቀመጠው ቦታውን ለይቶ ነው:: ይህንንም ሲያስረዳ «ሥጋውና ደሙ በሚሰጥበት» በማለት የገለጸው አገላለጽ ሥጋውና ደሙ የት ቦታ ለምእመናን እንደሚቀርብ ይታወቃል:: በዚህ ቦታም ምግብ እንደማይበላ ለማንም ግልጽ ነው:: በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ለማለት ፈልጌ ነው ካለ ደግሞ ሰንበቴ ቤት፣ ጽዋ ማኅበራት፣ የነዳያን ምገባ ወዘተ የማይለያት ቤተክስቲያን በቅጽሯ ውስጥ የፈቀደቻቸው እነዚህ ከሥጋ ምግቦች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማኅበራት ስሕተት ናቸውን? እንደ ጸሐፊው አባባል ልደት መከበሩ የማይደንቀው ከሆነ፤ ምግበ ሥጋ በቅጽረ ቤተክርስቲያን የሚበላ ከሆነና ቪዲዮ ለሠርግ፣ ለዓመታዊ ክብረ በዓል ወዘተ የሚቀረጽና የሚነሣ ከሆነ ምንድን ነው የገረመው?

፪ኛ. አንድ ባለ ሀብት ብሎ መሰለኝ የጻፈው፤ ሐሳቡ ተአማኒነት እንዲኖረው ነው? ወይስ ለምን ዓላማ? በሌሎች ላይ ከመፍረድስ አስቀድሞ ቢቻል የድርሻን መወጣት ካልተቻለ ደግሞ ነገሩን በትክክል መረዳት አይቀድምምን? «የፈቀደው ማነው?» በማለት የሚጠይቀው እውነተኛና ለቤተክርስቲያን የሚቀረቆር፣ ከሆነ እንደ ክርስቲያንነቱ ምን አደረገ? በወቅቱም ሥነ ሥርዓት ለሚያስከብሩት አስተናባሪዎች ወይም ወደ መድረኩ ወረቀት ጽፎ በመላክ ነገሮችን ለማስቆም ለምን ጥረት አላደረገም? ለመጻፍ ከሚቸኩልስ ይህንን ጉዳይ ለሚመለከተው ለቤተክርስቲያኑ አስተዳደር ማሳወቁ አይቀለውም ነበር? ተቆርቋሪ ለመምሰልና ራሱን ነፃ ለማድረግ ከሚጥር እንደ ሃይማኖተኛ ሰው ቢያስብ የሚጠቅመው ይመስለኛል:: አዘጋጆቹም እንደነዚህ ዓይነት ጽሑፎች ሲመጡ ጽሑፉን ከማውጣታችሁ በፊት የሚመለከተውን ክፍል ብታነጋግሩ መልካም ነው:: የሚወጡትም ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ብቻ የሚያነቧቸው ስላልሆኑ በተቻለ መጠን ጸሐፊዎችም ሆንን አሳታሚዎች እንደ ሃይማኖት ሰው ልንጽፍና ልናወጣ ይገባናል እላለሁ::✤

*ስሜነህ ይፍሩ*
*የደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተክርስቲያን*
*የስብከተ ወንጌል ሓላፊ*



www.eotcmk.org

እነዚህ ርኩሰቶች ከጥንት ጀምሮ የሚፈጸሙ ሲሆኑ ከእግዚአብሔር የታዘዙ የተለያዩ የጅምላና የተናጠል ቅስፈቶች እንዳስከተሉ ቅዱስ መጽሐፍ ይገልጻል። ዛሬም እነዚህ ርኩሰቶች አልቆሙም። አዲሱ ትውልድ መልካቸውን በማቀያየር እየፈጸማቸው ይገኛልና።

በረከተ ወንጌል

አንድ ፕሮፌሰር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እኒህ ሁሉ ሥራ የሚያስፈቱ በዓላት ያሏት ቁጥር ስለማታውቅ ነው፣ በግእዝም ቁጥር ስለሌለ ነው ሲሉ ሰምቼ ቁጥር መኖሩንና የሒሳብ ትምህርትም መኖሩን፣ የበዓላቱም ብዛት እሳቸው እንደ ገመቱት ሳይሆን በጣም በጣት የሚቆጠሩ መሆናቸውን ነግሬያቸው ነበር። የሚስያስደንቀው ነገር እኚህ ፕሮፌሰር በኢትዮጵያ ውስጥ የዩኒቨርሲቲ መምህር መሆናቸው ነው። ነገር ግን ከእንዲህ ያለ ሰው የሚቀርብ ነቀፌታ በሀገር እድገት ላይ ጭምር ከፍ ያለ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ለመግለጽ ነው።

ዕሥራ ምእት

ከዚያ አንጻር ደግሞ ቅድስት ቤተክርስቲያን ዜማው ለሥርዓተ ቤተክርስቲያንና ለምእመናን ሥነ ምግባር ካለው ጥቅም አንጻር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለዝማሬ ይህን እንድንጠቀም አድርጋለች። ይህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ነው። ቤተክርስቲያን ደግሞ የሚመሯት አባቶቻችን ናቸው፤ ካሳመፅን በስተቀር።

ስምምነቱ በ፲፱፻፵፩ እና በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በተፈረሙ ስምምነቶች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከነበረው የግብጾች ሙሉ ወይም ከፊል የበላይነትና ቁጥጥር በእጅጉ ተለይቶ ለቤተክርስቲያኒቱ ነጻነት ፍጹም ዕውቅና የሚሰጥ ነው። ነጻነቷም ቤተክርስቲያኒቷ በሁሉም ደረጃ ያሉ የራሷን ኤጲስ ቆጶሳት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሾም በመቻሏ ይገለጻል።

ወቅታዊ ጉዳዮች

የእኛ ካህናት ግን ሥልጣን የተቀበሉት በሰውነት ለምጽ ላይ ሳይሆን በመንፈሳዊ ለምጽ ላይ ነው። ከተመለከቱ በኋላ ነጽቷል ለማለት ሳይሆን በእርግጥና በፍጹም ለማንጻት ነው። ስለሆነም ካህናትን የሚነቅፉ ከዳታንና ከማኅበሩ የበለጠ እጅግ የተረገሙ ናቸው፤ ከእነርሱ የባሰ ቅጣትም የሚገባቸው ናቸው። እነዚያ ምንም እንኳ ያልተሰጣቸውን ክህነትን ይገባናል ብለው ቢነሡም ቅሉ ክህነትን በተመለከተ ከፍ ያለና የተከበረ አመለካከት ነበራቸው።

ትምህርተ ሃይማኖት


ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ
ም/ ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አዘጋጅ - ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን
ሪፖርተሮች - ጌታቸው በቀለ
- ዲ/ን ምትኩ አበራ
ኮምፒዩተር ዲዛይነር - ርብቃ ኃይለማርያም
የኮምፒዩተር ጸሐፊዎች - ጸዳሉ ሁንዴሳ
- ልደት አስፋው
- ደብረወርቅ ተክለጽዮን

የዝግጅት ክፍሉ፡
Email:- hamermk08@gmail.com

የማኅበሩ ጽ/ቤት
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org

በማኅበረ ቅዱሳን የሰሜን አሜሪካ መካነ ድር
www.mahiberekidusan.org
ስልክ 011-1-245135
መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ


## «ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፬
ሐምሌ/ነሐሴ ፳፻፰ ዓ.ም.


# ይዘት


**መልእክተ ዘማኅበረ ቅዱሳን**
* ለአፍሪካ ሚሌኒየም የዕውቀት መገኛ የሆኑትን የአብነት ት/ቤቶች እንጠብቃቸው ........ ፬

**ደብዳቤዎች** ........ ፭

**በረከተ ወንጌል**
* ከድፍረት ኃጢአት ጠብቀኝ ........ ፮

**የኢትዮጵያ ስምዓት /ዕሥራ ምእት/**
* አብነቱ ያለ አብነት እንዳይቀር ........ ፰

**ወቅታዊ ጉዳዮች**
* መዝሙራችን ወዴት እያመራ ነው? ........ ፲፬
* ኢትዮጵያ ትሴብሕ ወትዜምር ግብጽ ........ ፲፱

**ትምህርተ ሃይማኖት**
* ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት ........ ፳፫

**ምዕራፍ** ........ ፳፱

**እናስተዋውቃችሁ**
* በጆሮአችን የሰማነውን በዐይናችን አየነው ........ ፴፯

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
* እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ ........ ፵፩

**ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**
* በግእዝ እንነጋገር ........ ፵፱


*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።*

www.eotcmk.org

**ሥሉስ ቅዱስ ዘማኅበረ ቅዱሳን**

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።*

# ለአፍሪካ ሚሌኒየም የዕውቀት መገኛ የሆኑትን የአብነት ት/ቤቶች እንጠብቃቸው።

በዕሥራ ምእት ዓመተ ምሕረት እያከበርነው ያለው ኢትዮጵያ ሚሌኒየም የአፍሪካ ሚሌኒየም ሆኖ ተከብሯል። ኢትዮጵያ ሀገራችን ዕሥራ ምእቱን /የሚሌኒየም/ በዓል በማክበር አፍሪካን የራሱ ፍልስፍና እና የዘመን አቆጣጠር ባለቤት መሆኑን ያሳየችው ከአብነት ት/ቤቶች በተገኘው ዕውቀት ነው። ስለዚህ ሚሌኒየሙ «ለራሱ መገኘት» ወይም «በዓል ሆኖ ለመከበር» ምክንያት የሆኑትን የአብነት ት/ቤቶች ትቶ ሊከበር የሚገባው አልነበረም። ይህ የሚሆነው ሚሌኒየሙ «የእፉኝት ልጅ» ከሆነ ብቻ ነው። የእፉኝት ልጆች ወደዚህ ዓለም የሚመጡት እናታቸውንና አባታቸውን ገድለው /መገኛቸውን አጥፍተው/ ነውና። ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል ግን የቀመሩ መገኛዎች የሆኑትን የአብነት ት/ቤቶች አላጠፋም። ይሁን እንጂ /በቂ/ መታሰቢያ አላደረገላቸውም።

የአብነት ት/ቤቶች የሚባሉት ባለፉት ሁለት ሺሕ ዓመታትና ከዚያም በላይ በኢትዮጵያችን የነበሩት ት/ቤቶች ናቸው። ከፊደል ቆጠራ የሚያስጀምረው ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ አቋቋም ቤት፣ ቅዳሴ ቤት፣ እና ትርጓሜ መጻሕፍት ቤት ተብለው በጥቅሉ የሚጠሩት መካናተ ጉባኤያት /የትምህርት ቦታዎች/ ሁሉ የአብነት ት/ቤቶች ይባላሉ። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በየራሳቸው ብዙ ክፍልና ማኅደር ያላቸው ታላላቅ ተቋማት ቢሆኑም ከትምህርት ይዘታቸው በቀር በትምህርት አሰጣጣቸውና በአጠቃላይ አካሔዳቸው ይመሳሰላሉ።

የአብነት ት/ቤቶች ዘመናዊው ትምህርት ወደ ሀገራችን ከገባበት ከሃያኛው ክፍለ ዘመን በፊት የተማረ የሰው ኃይል ብቸኛ መገኛዎች በመሆን ሀገሪቱንም፣ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከዚህም የተነሣ የኢትዮጵያውያን የአእምሮ ውጤቶች የሚባሉት ሁሉ መገኛቸው በእነዚህ ት/ቤቶች ተምረው የሚወጡ ምሁራን መሆናቸው ለሁሉም የታወቀና የተረዳ ነገር ነው። ፊደሉ፣ ሥነ ጽሑፉ፣ ጥንታዊ ሥልጣኔው፣ አብያተ መንግሥታቱ፣ ገዳማትና አድባራቱ፣ ዜማው፣ የአስተዳደር ሕጉ፣ መጻሕፍቱ፣ ... ሁሉ የእነዚህ ት/ቤቶች ውጤቶች ናቸው። በዚህም ለሀገራችን ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሌላውም ዓለም ዕውቀትን በማካፈል ከፍተኛ ድርሻ መወጣታቸውን መረዳት ይቻላል።

ሀገራችን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ጥቁሩን የሰው ልጅ በአዳማዊ ሰብእና ለማይቀበሉት ነጮች መላው የጥቁር ሕዝብ የሥልጣኔ አሻራ ሆነው የታሪክ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የፊደል፣ የቁጥርና የዘመን አቆጣጠርን የመሰሉ የረቂቅ ሀብት ባለቤቶች ያደረጉት እነዚሁ ትምህርት ቤቶች መሆናቸው እሙን ነው። የአብነት ት/ቤቶቹ ቀዳሚ ዓላማ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያበረክቱ ሊቃውንትን ማፍራት ቢሆንም ጠለ ረድኤታቸው እንደ አርሞንኤም ጠል /ከተራራው እየወረደ ለአካባቢው ሜዳ እንደሚደርሰው/ መሪዎችን፣ ጸሐፍትን፣ ጀግኖችን፣ ... ቅርሳ ቅርስና ማንነትን፣ ታሪክንና ድንበርን፣ ... አስገኝቷል። ሌላውም ሁሉም በእነዚህ ት/ቤቶች መምህራን ጽሑፎች ወይም ከእነርሱ በወጡ ዜጐች የተሠራ ነው። ስለዚህ የጥቁሩ የሰው ዘር መመኪያ፣ የአፍሪካ ኩራት፣ የኢትዮጵያ ጸጋ ምንጮች የአብነት ት/ቤቶች ናቸው።

እንደ እውነቱ ከሆነ የአብነት ት/ቤቶች ባይኖሩ፣ ይኼ ሁሉ ዕውቀት አይኖርም ነበር። ስለዚህም አሁን ያለው ታሪኩም፣ ጽሑፉም፣ ማንነቱም፣ ... መገኘቱ አጠራጣሪ ነበር። ይሁን እንጂ ከእነርሱ የወጡ ሊቃውንት የጻፏቸውን መጻሕፍት ያህል፣ የገነቧቸውን ሕንፃዎችና የሠሯቸውን ታሪኮች ያህል ምንጮቹ ት/ቤቶቻችን የሚታወሱ አልሆኑም። የብራና ጽሑፉን እንጐኸለታለን፤ ስለ ጻፉት መምህራን ግን ማንም ምንም ሲል አይሰማም። ስለገዳማት አድባራቱና ስለታሪካዊነታቸው ይወሳል፤ የጠበቋቸውና እየጠበቋቸው ያሉት ት/ቤቶች ግን ተዘንግተዋል። ሚሌኒየሙ በአፍሪካ ይከበራል፤ የአፍሪካ ጥንታዊ ት/ቤቶች፣ ሕያው የፍልስፍና ምስክሮቹ የነበሩት ኢትዮጵያውኑ የአብነት ት/ቤቶች ግን አስታዋሽ አላገኙም።

ይሁን እንጂ ምሁራኑ በጥናታቸው መንግሥታት በፖሊሲዎቻቸው ባያካትቷቸውም የተገዙለት መለኮታዊ ኃይል ጠብቋቸው እስካሁን አል ጠፉም። በዚህ ሒደት ከቀጠሉ ግን የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው። እግዚአብሔርም የሚጠብቀውና የሚንከባከበው ተጠባቂው የአምላክን ጥበቃ በመሻቱ ብቻ ሳይሆን ከረቂቁም ከግዙፉም ይጠብቀው ዘንድ ግለሰቡ ራሱን የሚጠብቅም ሲሆን ነው። ስለዚህ የአብነት ት/ቤቶችን እግዚአብሔር ሲጠብቃቸው የኖረው፣ እየጠበቃቸውም ያለው መምህራኑ ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተው እነርሱን በመጠበቅ፤ ሕዝቡም ድርሻውን እየተወጣ ስለተንከባከባቸው ነበር። በዚሁ መሠረት አሁንም የቀጣዩን ትውልድ እገዛ ይጠይቃሉ።

የእኛ ዘመን ትውልድም ሓላፊነቱን ተወጥቶ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ይገባዋል። የትምህርት ባለሙያዎች የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ብቻ ሳይሆን የማኅበራዊ ሳይንስና የተፈጥሮ ሳይንስ ባለሙያዎችም በጥናቶቻቸው ወደ እነዚህ ት/ቤቶች እየዘለቁ ሀገር በቀሉን ዕውቀትና ፍልስፍና ማካተት ከዘመናዊው እሳቤም ጋር በአግባቡ ማዋሐድ ይጠበቅባቸዋል። መንግሥት ከፖሊሲው ጀምሮ በተለይ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ያሉ ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎች ሁሉ ከእነዚህ ት/ቤቶች የሚገባቸውን ዕውቀት ያገኙ ዘንድ ሊጠብቋቸው ያስፈልጋቸዋል። ፖሊሲ አውጭዎችም ሀገሪቱን የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ ዜጐቿንም ለማነጽ እንደ ምሁር ከሀገር በቀል ዕውቀትና ፍልፍስፍና መነሣት ይጠበቅባቸዋል።

ዘመናዊው ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ጥንታዊው ትምህርት ላይ ጥናት ተካሒዶና ጉድለቱ ታውቆ ያንን ለመሙላት አይደለም። በዚህም ምክንያት ከአውሮፓ ዘልሎ የገባው ዘመናዊ ትምህርት ከእነዚህ ት/ቤቶች ዕውቀት ጋር በአግባቡ ባለመዋሐዱ ዘመናዊውን ምሁራን ጐድቷቸዋል ማለት ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ ዕውቀት፣ ፍልስፍና እና የሰላ አስተሳሰብ ከነእነዚህ ት/ቤቶች የማይገኝባቸው፣ በሥርዓተ ትምህርትና በምክንያታዊ ቅደም ተከተል ሳይሆን በዘፈቀደ የሚመሩ የሚመስሏቸው አሁንም ብዙዎች ናቸውና። ይህ ደግሞ እውነተኛ ጉዳት ነው። እንደተጐዳ የማያውቅ የተማረ ሰው ደግሞ በዚያው ባለማወቁ መጠን ጉዳት ማድረሱ አይቀሬ ነው።

ስለዚህ እነዚህን ት/ቤቶች ከመንቀፍና ከመናቅ በፊት ቀረብ ብሎ መመርመር ማወቅ፣ መረዳትና ይዘታቸውንም መለየት ከምሁራኑ ይጠበቅባቸዋል። አንድ ጠንካራ ጥናት እንኳ ሳናካሒድ፣ ምንነታቸውንም በውል ሳናውቅ መናቅና መንቀፍ ግን ት/ቤቶቹን ከሚጐዳው በላይ ሀገሪቱንና ዜጎቿን፤ እየቆየ ሲሔድ ደግሞ በእነዚህ ት/ቤቶች ላይ የተመሠረተውን የጥቁር ሕዝብ ታሪክ፣ ማንነትና ቅርስ የሚያጠፋ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም።

የት/ቤቶቹን የትምህርት ይዘት በውል ካለመረዳትና ታሪካቸውንም ካለማወቅ የተነሣ አንዳንድ ሰዎች ጉዳያቸውን አሳንሰው ይመለከታሉ። ለአንዳንዶቹ ሃይማኖታዊ ከሆነው አገልግሎት ሰጪ ባለፈ ሌላ ሰው ቀርጸው ያበረከቱም አይመስላቸውም። ለአንዳንዶቹ ደግሞ የኋላቀርነትም ምክንያቶች ይመስሏቸዋል። ለሌሎችም ደግሞ እንዲሁ ሌላ ነገር የያዙ ይመስሏቸዋል። ከዚህ የተነሣ ጠቀሜታቸውን የሚያሳንሱት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

እጅግ የሚያሳዝነው ግን እነዚሁኑ ምሁራን ስለ ሌሎች ሀገሮች ዕድገት ተርኩልን ስንላቸው ሀገሮቹ ከራሳቸው ሀገር በቀል ዕውቀት መነሣታቸውንና ያንኑም በማዘመን ወይም ከሌላው ከወሰዱት ጋር በማዋሐድ ለዚህ እንደበቁ ለመናገር የማይቸገሩ መሆናቸው ነው። በተለይ በቅርቡ ፈጣን ዕድገት ያመጡት የእስያ ሀገሮች ምዕራባዊውን ሥልጣኔ ከራሳቸው ሀገር በቀል ዕውቀትና ትምህርት ጋር በማዋሐዳቸው እንደሆነ ብዙ ጊዜ ይነግሩናል። የራሳቸውን ግን ዘወር ብለው ሊያዩት እንኳን ይከብዳቸዋል። ስለዚህም የምንሰብከውን፤ የየሙያችንን ንድፈሐሳብ /ቲዮሪ/፣ የምንደሰኩርለትንም የሌሎች ሀገሮች ልምድ በተግባር ለማሳየት የራሳችንን ት/ቤቶች እንመልከታቸው፤ እናጠናቸውና እንጠቀምባቸውም ዘንድ መጀመሪያ እንጠብቃቸው። እንደ ኦክስፎርድ መሰል ዓለም አቀፍ ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች መነሻቸው የሀገራቸው የሃይማኖት ት/ቤቶች መሆናቸውን እየተረክን የእኛዎቹን ብንተዋቸው እንደ እፉኝት ልጆች በጽንስ አባታችንን /ማንነታችንና ታሪካችንን/ ገድለን ቆይተን፤ በልደት ደግሞ እናታችን /ት/ቤቶቹን/ የምንገድል እንዳንሆን ያሰጋል።

ስለዚህም ቤተ ክህነቱ፣ ሰንበት ት/ቤቶች፣ የምእመናን ማኅበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ የጥናትና ምርምር ተቋማት፣ የውይይት ክበቦች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ልማት ተኰር ተቋማት፣ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ ... ኢትዮጵያውያንና ከእነዚህ ት/ቤቶች ላለው ዕውቀት የምንጨነቅ ሁሉ. ሕልውና ይቀድማልና የታሪካችን ባለውለታዎች የሆኑትን የአብነት ት/ቤቶቻችንን እንጠብቃቸው፤ ከዚያም እናጥናቸው፤ እንጠቀምባቸው። አልምተናቸው እንልማ፤ አሳድገናቸውም እንደግ። ♦

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

## ንቁ

የመስቀል አደባባዩ ዐውደ ትእይንት ለምን እንደታገደና ማን እንዳገደው በውል ተለይቶ ባልታወቀበት፣ የጊዜና የገንዘብ ብክነት አላግባብ መክና የቀረበት ሁኔታ ሁሉንም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይን እጅግ ያሳዘነ ነበር:: ሁኔታው ግን ማኅበረ ቅዱሳንን ለበለጠ ሥራ እንዲነሣሣ አደረገው እንጂ፣ አንገቱን አስደፍቶ፣ ከንፈሩን አስመጥጦ በቊጭት ቆሞ እንዲቀር አላደረገውም:: ይልቁንም «መጪው ዘመን እንዳይቀድመን እንነሣ» የሚል ዐውደ ርእይ እንዲያዘጋጅ አደረገው:: «ዝክረ - ዘመንም» በደውሏ ታጅባ ንቁ፣ እያለች በርካታ ስንቅ መግባናለች:: ዐውድ ርእዩን በአካል ተገኝተው በማየት ከተጠቀሙት ምእመናን ባላነሰ በሀገር ውስጥ ርቀን ያለንና በውጭ ሀገር ያሉ አማንያን በዝክረ- ዘመን መጽሔት ብዙውን ዐቢይ ጉዳይ ተረድተን ተጠቅመንበታል::✦

*ጸጋዬ ዘውዴ*
*ወልዲያ*

## አንድነታችንን እናጠንክር

ሐመርና ስምዐ ጽድቅን እየተከታተልኩ ማንበብ ከጀመርኩ አንድ ዓመት አስቆጥሬአለሁ:: በዚህም ብዙ መንፈሳዊ ዕውቀት ገብይቻለሁ:: ዛሬ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ነገር የቤተ ክርስቲያን ጠላት የሆኑ አስመሳዮች የሚያሴሩት ተንኮል ነው:: በአሁኑ ወቅት በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍልም እየተሠማሩ ይገኛሉ:: በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ፣ በየሰንበት ት/ቤቱ አገልጋዮችን ከአገልግሎታቸው ለማደናቀፍ በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ ነው:: ስለ ማኅበረ ቅዱሳንም መጥፎ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ ናቸው:: ስለዚህ የእነዚህን አስመሳዮች ወጥመድ ለመበጣጠስ ቤተ ክርስቲያን የምናገለግል ሁላችንም አሁን አንድነታችንን ማጠንከር እንዳለብን ለማሳሰብ ነው::✦

*ዮሐንስ ብርሃኑ*
*ባሕር ዳር*

## ዛሬ ምን ተገኘ?

በምኖርበት በአሜሪካን ሀገር በሥራ ገበታዬ ላይ እያለሁ አንድ መጽሔት አግኝቼ ሳነበው «በምስጢረ ሥላሴ አስተምህሮ የሚያምኑ ሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት ተባብረን አንዳችን የሌላችንን ምእመን ከመማረክና ከማስኰብለል ይልቅ ክርስቲያን ያልሆኑትን በወንጌል ማዳረስ ግባችን መሆን ይኖርበታል» ይላል:: ማን ከማን ነው የሚተባበረው? ማን ነበር እስከ ዛሬ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት ተከታይ እያስኰበለለ፣ በጥቅማ ጥቅሞች እየደለለ ሲሰብክ የኖረ? ዛሬ ምን አዲስ ነገር ተገኘ? እስከ ዛሬስ ክርስቲያን ላልሆነው ወንጌል መስበክ እንደነበረበት አያውቁም ነበርን?✦

*ቤተልሔም መታፈሪያ*
*ከደብረ ሰላም መድኄዓለም ሰንበት ትምህርት ቤት*
*ሂውስተን ቴክሳስ አሜሪካ*

## በጸሎት እናግዛቸው

በሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ እና ፮ ተከታታይ እትሞች ያቀረባችሁት «የወደቁትን አንሡ፣ የሞቱትን ቅበሩ የቆሙትን አስተምሩ» የነዳያን መርጃ ማኅበር እያደረገ ያለው አገልግሎት ለሁላችንም አርአያ የሚሆን ነው:: በሐመር ላይ ተዘግቦ ምእመናን የማኅበሩን እንቅስቃሴ እንዲያውቁት መደረጉ የሚያስደስት ከመሆኑም በላይ፣ ማኅበሩን የማያውቁ እንዲያውቁት፣ እየረዱ ያሉትም ርዳታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያደርግ ዘገባ ነው:: ምንም የሌለንም ሰዎች ማኅበሩን በጸሎት ማሰብ ይጠበቅብናል:: በማኅበሩ ውስጥ የሚያገለግሉት ወጣቶችም ሳይሰለቹ ራሳቸውን ከውዳሴ ከንቱ ጠብቀው አገልግሎታቸውን ይበልጥ ማጠናከር አለባቸው::✦

*ንጉሤ መብራቱ*
*ዱብቲ /አፋር/*

## መምህራችን ናት

ሐመር ለምእመናን ሕይወት ልምላሜ እየሰጠችና ፍሬ እያፈራች ትገኛለች:: የእግዚአብሔር ቃል ምንጊዜም አይጠገብም:: እኔ ያለሁበት ወረዳ ግን በርሐማ ከመሆኑም በላይ ከከተማም የሚርቅ ነው:: በዚህ ቦታ መምህራንም አናገኝም:: አሁን አሁን ግን አንዳንድ መምህራን እየመጡ ቢያስተምሩንም ያምበቂ አይደለም:: ስለዚህ የዘወትር መምህራችን ሐመር ናት:: በእኛ አካባቢ የሥርጭቱ ሁኔታ አጥጋቢ ባለመሆኑ በችግር ላይ እንገኛለን:: መጥቶ የሚያስተምረን ብናጣ እንኳን ሐመርን እንዴት እንጣት? ስለዚህ የሚመለከተው ክፍል ወቅቷን ጠብቃ እንድትመጣ ቢያደርግልን ደስታችን ወደር የለውም::✦

*ሽመልስ ጌታቸው*
*በረኸት ወረዳ*

## እንረባረብ

ሐመርን ማንበብ የጀመርኩት በቅርብ ጊዜ ቢሆንም፣ ለተሳትፎዬ የመጀመሪያ የሆነችው ደብዳቤዬን ስጽፍላችሁ ታላቅ ደስታ እየተሰማኝ ነው:: በመጽሔቷ የምታስነብቡን ነገር ጥሩ ነው:: በዚሁ ቀጥሉበት:: ባለፉት ሦስት ተከታታይ እትሞች መዝሙርን በተመለከተ የቀረበው ጽሑፍ ወቅታዊ የሆነ አስተማሪ ነው:: በአሁኑ ወቅት የመዝሙራቱ ጉዳይ ወጣቶቹን እያነጋገረ በተለያየ ሐሳብ እንዲሄዱ እያደረገ ስለሆነ ቶሎ መፍትሔ ቢሰጥበት መልካም ነው:: እርስ በርሳችን ስለ መዝሙር እየተወቃቀስን ለዲያብሎስ በር ከምንከፍት ተረባርበን ችግሩን ብንፈታ መልካም ነው:: እኛም በጸሎታችን እንረዳችኋለን ትጉ::✦

*ወልደ ተክለሃይማኖት*
*መቀሌ ዩኒቨርሲቲ*

## ተምረንበታል

ብርዕ ከወረቀት እንዳገናኝ ያደረገኝ የዐውደ ርእዩን ጠቅላላ ይዘት ስለያዘችው «ዝክረ-ዘመን» መጽሔት ነው:: መጽሔቷ በርካታ ትምህርቶችን አካታ ይዛለች:: ምእመናን የሀገራቸውንና የቤተ ክርስቲያናቸውን ጣዕም ለማወቅ በሃይማኖታቸው ጸንተው ለመኖር ዝክረ-ዘመን ከፍተኛ እገዛ ታደርጋለች:: መጽሔቷ ትምህርት የምናገኝባት ብቻ ሳትሆን ቅርስም ጭምር ስለሆነች የማኅበረ ቅዱሳን ሱቅ በሌለበት አካባቢ ያሉ ክርስቲያኖች ለማግኘት እንዲችሉ ወረዳ ማዕከላት መንገዱን ሊያመቻቹ ይገባል::✦

*ዲ/ን ተመስገን ዘገየ*
*ፎገራ ወረዳ /ወረታ/*



www.eotcmk.org

## ሕገ ወጥ ተሳታፊዎች

ዛሬ ብዕሬን እንዳነሣ ያደረገኝ የኮፒ ራይት ጉዳይ ነው:: ማኅበረ ቅዱሳን ከሚሰጣቸው ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች አንዱ ስብከቶችን፣ መዝሙሮችን፣ ዶክመንተሪ ፊልሞችን በቪሲዲ ለምእመናን ማዳረስ ነው:: ታዲያ አንድ ያሳሰበኝ ነገር አንዳንዶች የማኅበሩን ቪሲዲዎች በኮምፒውተር እያባዙ መቸብቸብ ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: «መጪው ዘመን እንዳይቀድመን እንነሣ» በሚል የተዘጋጀውን ኤግዚቢሽን በአካል ተገኝተን መመልከት ባንችልም ምስሉን ለማየት ከማዕከል የኤግዚብሺኑ ካሴት አልመጣም ወይ? እያለን ስንጠይቅ ለካስ በጉን ስድስት ብር መቸብቸብ ተጀምሮ ኖሯል:: ይሄ ወንጀል ነው:: አንዳንዶችም የዚህ ሕገ ወጥ ሥራ ተሳታፊ መሆናቸው ገርሞኛል፣ አናዶኛል:: የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ደግሞ ሕግ አስከባሪ እንጂ ሕግ ጣሽ ልንሆን አይገባም:: ማኅበሩ በሚያወጣቸው የአእምሮ ንብረቶች ሙሉ መብት እስካለው ድረስ መብቱን ለማስከበር ወደ ኋላ እንደማይል ሕገ ወጦች ሊረዱት ይገባል::✦

*ዲ/ን ሰሎሞን ጌታቸው*
*ምሥራቅ ጐጃም*

## አስተካክለን ማየት ብንችልስ?

በሐመር መጽሔት ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፫ «ስለ መዝሙሮቻችን እንወያይ» በሚለው ዓምድ ሥር የአንድ አስተያየት ሰጪ ያሉት ውስጤን እጅግ በጣም ስላቆሰለኝ ነው አስተያየት ለመጻፍ የተነሣሁት:: ይህ የአርሴ ነኝ፣ የማንቼ ነኝ እየተባባሉ የመከፋፈልን ዓይነት አካሔድ ከቤታችን ብናወጣው ምን አለ? በርግጥ በዚህ ዘመን ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው የመዘመር ጸጋ እግዚአብሔርን እያገለገሉ ባሉ ዘማርያን በጣም ደስተኛ ነኝ:: ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እንደምንመለከተው ከዕውቀት ማነስ፣ ለገንዘብ ካላቸው ከመጠን ያለፈ ፍላጎት ወይም ከሌላ ምክንያት የተነሣ እያወጧቸው ያሉ መዝሙሮች ያሬዳዊ አይደሉም:: ምናልባትም ይህ የሆነው ትውልዱ ደስታን ብቻ ፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ይመስለኛል:: አሁን እኮ ጥያቄአችን በመዝሙር እንድናመሰግነውና እንድንለምነው ለፈቀደልን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መዝሙር ምን ዓይነት ነው? የሚል ብቻ ነው:: ታዲያ መከፋፈላችንን ትተን ያሬዳዊ መዝሙሮቻችን እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ ብንወያይ አይሻልም? ኧረ እባካችሁ በመንፈሳዊ ዓይን አስተካክለን ማየት እንቻል::✦

*ዲ/ን አራጋው ደምሴ*
*ጅማ*

## ደንበኛ ሆኛለሁ

የሐመር መጽሔትን በተከታታይ ባይሆንም አልፎ አልፎ አነባለሁ:: ከመጽሔቱ ብዙ ቁም ነገሮችን አግኝቻለሁ፤ በዚህም የተነሣ የዘወትር ደንበኛ ሆኛለሁ:: እኔም ከአንባቢነት ወደ ተሳታፊነት የምታሸጋግረኝን ይህችን ደብዳቤ ልኬላችኋለሁ:: ወደፊትም ለመጽሔቷ የሚሆኑ ያስተምራሉ የምላቸውን ቁም ነገሮች እልካለሁ::✦

*መ/ርት ፍጹም በቀለ*
*አቡነ ጎርጎርዮስ ት/ቤት*
*ደብረ ብርሃን*

## ከስሕተታችን እንታረም

ሐመር «ስለ መዝሙሮቻችን እንወያይ» የሚል ዓምድ ከበርካታ ምእመናን የተለያዩ አስተያየቶችን ስታስነብበን ቆይታለች:: መዝሙር የግለሰብ፣ የማኅበር.. ጉዳይ ብቻ አይለም:: የዚህች ቤተ ክርስቲያን ልጆችን በሙሉ ይመለከታል:: የባሰ አያምጣ ነው እንጂ አሁን አሁንማ የቤተ ክርስቲያናችን መዝሙሮች የማይመስሉ መስማት ጀምረናል:: ያሬዳዊ መዝሙራችን ከሌላው የሚለየን መሆኑ ተዘንግቶ ነው ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውጭ የሆኑ መዝሙራት የሚዘመሩት? የሆነ ሆኖ ያለፈ አልፏል፤ የተሳሳትንም ፈጥነን ስሕተታችንን ለማረም እንጣር እንጂ ምክንያቶችን ባንደረድር ጥሩ ነው:: አባቶቻችን ያሬዳዊውን ዜማ ጠብቀው እኛ ላለንበት ጊዜ አድረሰውናል፤ እኛ ደግሞ በሚገባ ተጠቅመን ለቀጣዩ ማስተላለፍ ይጠበቅብናል::✦

*ፍቅርተ ሚካኤል*
*ከአቡዳቢ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም*
*ቤተ ክርሰቲያን ተስፋ ስዱዳን*
*ሰንበት ት/ቤት*

## የባለቤትነት መብት በሬዲዮ አይሠራም?

ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ ያነሳሳኝ የመናፍቃን ሬዲዮ ጣቢያ ሁኔታ ነው:: ማታ ማታ ሬዲዮ ስትከፍቱ እንደ እርጐ ዝንብ ሳትፈልጉት የሚገኝ የመናፍቃን ሬዲዮ ጣቢያ ዓይነትና ብዛት በጣም አስገርሞኛል:: ደግሞም እንደታላቅ ቁም ነገር የሚተላለፍበት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መብዛቱ የሚገርም ነው፤ ይባስ ብሎ የቤተ ክርስቲያናችንን ያሬዳዊ ዜማና የተቆነጸጸሉ መዝሙሮች እየዘመሩ እኛን ሳይሆኑ እኛን ለመምሰል እየሞከሩ ያሉትን የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች የዋሁ ምእመን ይቅርና የተማረውም የእኛ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ትኩረት ሰጥቶ እስከማድመጥ የሚያደርሰው ይመስለኛል:: እኔ የምለው የኪነ ጥበብ ሥራ የባለቤትነት መብት /Copy right/ በሬዲዮ አይሠራም ወይ? ያሬዳዊ ዜማችንን ብቻ አይደለም እየሠረቁን ያሉት፤ ሙሉ የመዝሙሩን ግጥም እስከዜማው እንጂ:: ታዲያ ቤተ ክርስቲያናችን ለምን እነዚህ በአማርኛ፣ በትግሪኛ ... የሚተላለፉ ጣቢያዎች ላይ የሚቀርቡ ያሬዳዊ ዜማዎቿ ሲወሰዱ ለምን ዝም ትላለች? የዚህ ተጽዕኖ ደግሞ በስፋት የሚታየው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በሚገኙ ምእመናን ላይ ነው:: ስብከተ ወንጌል እንደከተማ ባልተስፋፋበት ገጠር ላይ የሚኖሩ ምእመናን ሬዲዮ ሲከፍቱ መናፍቃኑ በያሬዳዊ ዜማ ሲዘምሩ ሲሰሙ፤ መናፍቃን ናቸው ብለው እንዴት ሊጠረጥሩ ይችላሉ? ስለዚህ እነዚህ ለመንጋው የማይራሩ ተኩላዎች ብዙዎችን ወግተው ከመጣላቸው በፊት ቤተ ክርስቲያናችን በገጠርም፣ በከተማም በጽሑፍም በቃልም በማስተማር ልጆቿን ማንቃት አለባት::✦

*ገ/ማርያም ደሳለኝ*
*ደሴ*

*ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል:: እናመሰግናለን:: መልእክቶቻችሁንና የጥቆማ ሐሳቦቻችሁን ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን:: በተሳትፎአችሁ ቀጥሉበት::*

*መ/ር ቸርነት ጉንዱሬ- ጋሞጐፋ ዞን፣ መ/ር ብርሃኑ ድጋፌ - ምዕራብ አርሲ ዞን፤ ታደሰ ጌታቸው - ጋሞ ጐፋ፤ ታምራት ሀብታሙ - ሻሸመኔ፤ ኃ/ገብርኤል - አዲስ አበባ፤ መስፍን ሽፈራው - ሰሜን ወሎ፤ አብዩ ዓለሙ - ጅማ::*



www.eotcmk.org

# ከድፍረት ኃጢአት ጠብቀኝ

## /መዝ. ፲፰፥፲፫/

አባ ዘሚካኤል ደሬሳ

በርእሱ የተጠቀሰውን ኃይለ ቃል የተናገረው ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ነው:: ዳዊት ማለት ምርጥ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ለንግሥና ለነቢይነት ወዘተ የመረጠው በመሆኑ ምርጥ ይባላልና:: በመዝሙር መጽሐፍ «ወአልዓልኩ ኅሩይየ እም ሕዝብየ፣ ወረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ፣ ወቀባዕክዎ ቅብዐ ቅዱስ፤ ከሕዝቤ የመረጥኩትን ከፍ ከፍ አድርጌዋለሁ፣ ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት ቅዱስ ቅባትም ቀባሁት» /መዝ.፹፰፥፲፱/ ተብሎ እንደተነገረ::

ቅዱስ ዳዊት ነቢይ እንደ መሆኑ መጠን በእርሱም ዘመን የተደረገውን፣ ከዚያም በፊት የነበሩትንና በኋላም የሚመጣውን ትውልድ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ «የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ» ብሎ ለሁሉም የሚጠቅምና ተገቢ መንፈሳዊ መልእክት የያዘ ትምህርት አስተላልፏል::

ነቢዩ «የድፍረት ኃጢአት» ወይም «ልዩ ኃጢአት» ያለውን በሁለት መንገድ እንመልከተው:: አንደኛው ሐሳብ በቅዱስ ዳዊት ላይ ሰዎች በድፍረትና በግፍ በደል እንዳይፈጽሙበት ያቀረበው ተማጽኖ ሲሆን ሁለተኛው እርሱ /ቅዱስ ዳዊት/ በሕሊና ድካም የተነሣ በአካሔዱ ከእግዚአብሔር ርቆ ፀያፍ ኃጢአት በመፈጸም ከአምላኩ እንዳይጣላ «የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ» በማለት ጸሎት ማቅረቡን ያመለክታል::

የድፍረት ኃጢአት የተባሉት ጣዖት አምልኮ፣ ክህደት፣ የግፍ አገዳደል፣ ዝሙት፣ ግብረ ሰዶም እና ዛሬም በዓለም ውስጥ ሰው በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸመውን ታላቅ ዐመፅ ሁሉ ያጠቃልላል:: እነዚህ ርኩሰቶች ከጥንት ጀምሮ የሚፈጸሙ ሲሆኑ ከእግዚአብሔር የታዘዙ የተለያዩ የጅምላና የተናጠል ቅስፈቶች እንዳስከተሉ ቅዱስ መጽሐፍ ይገልጻል:: ዛሬም እነዚህ ርኩሰቶች አልቆሙም:: አዲሱ ትውልድ መልካቸውን በማቀያየር እየፈጸማቸው ይገኛልና:: በመሆኑም በርእሱ የተጠቀሰውን ኃይለ ቃል ለትውልዱ ተንትኖ መጠቆም አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም በትህምርቱ ከርኩሰት ይጠበቅበታል፤ የቀደምት ሰዎችን የተሳሳተ መንገድና እግዚአብሔርም ይመለሱ ዘንድ ያደረገውን ትድግና መሠረት በማድረግ የዘመኑን ትውልድ ሕይወት በማነጻጸር እንደሚከተለው እንመልከት::

ሀ. ከንባቡ እንዳየነው ቅዱስ ዳዊት «ከልዩ ኃጢአት አድነኝ» በማለት ተማጽኖ አቅርቧል:: ተማጽኖቱ ዐውቆም ሆነ ሳያውቅ፣ አስቦም ሆነ ሳያስብ፣ በስውርም ሆነ በግልጽ፣ በሥጋም በነፍስም አስጨናቂ በደል ከሚያደርሱብኝ ጠላቶቼ ከጥንት ጠላቴ ሰይጣንና በክፋት ከሚሸምቁብኝ ክፉ ሰው አድነኝ በማለት የእግዚአብሔርን ጥበቃ ለምኗል:: የልመናውን ትንታኔ እንመልከት::

ከሰይጣን አድነኝ ማለቱ አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን ያህል ሰይጣን የሰው ልጆችን ከጥንት ጀምሮ በፅንስ ተፀናውቶ፣ በልደት ተቆራኝቶ፣ ኃጢአት ሲያሠራ አሳድጎ፤ በሞቱ ጊዜ ሥጋቸውን በመቃብር ነፍሳቸውን በሲዖል በግዞት ያኖር ነበርና ከሥጋ መከራ ከነፍስ ግዞት አድነኝ በማለት ተናግሮታል:: በሕይወተ ሥጋ በደዌ ተመስሎ ሰውነቴን በሕማም አመንምኖ አእምሮን በማሳጣት ከመልካም ሥራ ለይቶ እንዳያኖረኝ ከልዩ ኃጢአት አድነኝ አለ::

አንድም ልዩ የውርደት ኃጢአት ከሚፈጽምብኝ ክፉ ሰው እጅ አድነኝ ማለቱ ነው:: ከአረማዊ ማለትም እግዚአብሔርን አምላክ ብሎ ከማያምንና እግዚአብሔርን አምኖ በኋላ ከካደ ሰው እጅ አድነኝ ማለት ነው:: እግዚአብሔር የሌለው ሰው ፍቅር፣ ሰላም፣ ርህራሄ የለውም፤ ሕግ የለውምና:: ስለዚህ ነቢዩ በክፉ ሰው እጅ አትጣለኝ ልዩ የድፍረት ኃጢአት ይፈጽምብኝም ዘንድ አትፍቀድለት በማለት ተማጽኗል:: በመሆኑም ቅዱስ ዳዊት በዘመኑ በአረማውያን መሸነፍና ሞት አላገኘውም:: የተለመደ የተፈጥሮ ሞትን እግዚአብሔር በፈለገው ቀን ፈጽሞለታል:: በዚህ ጸሎቱ ከዳነባቸው መካከል ሁለቱን ለምሳሌ ያህል እንመልከት::

፩. ከንጉሥ ሳዖል ደባ፡- ሳዖል በመጀመሪያ እግዚአብሔርን አምኖ፣ እግዚአብሔርም በከፍተኛ ሹመት አስቀምጦት ነበር:: በኋላ ግን ሹመት ሲመቸው፣ ኑሮ ሲደላው ሁሉን ገዛሁ፣ ሁሉን ጨበጥኩ ሲል የሾመውን እግዚአብሔርን አልታዘዝ በማለት ክዶታል:: ቅዱስ ዳዊትንም በቅናት ምክንያት ሊገድለው ፈልጓል:: ሳዖል ብዙ ጊዜ ቅዱስ ዳዊትን እንደማይገድለው ቃል ገብቶ በኋላም ቃሉን እያጠፈ በሽንገላ ሊገድለው ሞክሯል:: ስለዚህ ክፉ ሰው ከሚፈጽምብኝ ልዩ ኃጢአት አድነኝ ማለቱ ጠቅሞታል:: እግዚአብሔር ጊዜው ሳይደርስ እንዳይሞት በጥበቡ ጠብቆታል፤ ሳዖልም ምላሹን አግኝቶ በነቢዩ ሳሙኤል አማካኝነት «እግዚአብሔር ናቀህ» በመባሉ መንግሥቱም አልጸናም እርሱም በጠላቶቹ እጅ ወድቋል:: /፩ሳሙ.፲፫፥፲፰፥፮-፳/

፪. ከአረማዊው ነፍሰ ገዳይ ጎልያድ፡- ቅዱስ ዳዊት ከሕፃንነቱና ከእረኝነቱ ጀምሮ ኃያል እንዲሆን እግዚአብሔር አሠልጥኖት ነበር:: ገና ብላቴና ሳለ ለወንድሞቹ ስንቅ ለማቀበል በሄደበት ጊዜ ጎልያድ እግዚአብሔርን ሲገዳደር፣ እስራኤልን ሲንቅ በማየቱ፤ ለእግዚአብሔር ቀንቶ ምንም እንኳ ገና ብላቴና ቢሆንም በጦር ስልት ከሠለጠኑት፣ በጉልበት ከበረቱት፣ በአእምሮ ከበሰሉት ይልቅ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ስም ገጥሞ አሸንፎ ጥሎታል:: በጊዜውም ራሱንና ወገኑን ከዚህ ነፍሰ ገዳይና ከፍልስጥኤማውያን አድኗል:: እርሱ ያሸነፈው በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በራሱ ኃይል አይደለምና የድፍረት ኃጢአት ከሚፈጽሙብኝ ክፉ ሰዎች አድነኝ ማለቱ በብርቱ ጠቅሞታል::

ዛሬም ያለነው ከቅዱስ ዳዊት መልካም ተሞክሮ በመውሰድ እርሱ ከክፉ ሰዎች እንደዳነ ሁሉ አስቀድመን ሊደርስብን የሚችለውን ክፉና ጸያፉ የድፍረት ኃጢአት በማሰብ አንተ ከምታውቀው እኛ ከማናውቀው ከርኩሰት ኃጢአት ጠብቀን ማለት ተገቢ ነው:: በአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት «ከክፉ አድነን እንጂ» የሚለውን በአእምሮአችን አፅንዖት በመስጠት መማጸን አርቆ አሳቢነትን ያሳያል::

**የድፍረት ኃጢአት በእግዚአብሔር መናቅን ከዚያም ጋር የተናጠልና ጅምላ ጥፋትን ያስከትላል::**

ለ. አንድም ከልዩ ኃጢአት አድነኝ ማለቱ በዚህች ዓለም ላይ የሚከናወኑትን የድፍረት ኃጢአት ከመፈጸም አድነኝ ለማለት ፈልጎ ነው:: ይህም ሲባል ሰው በድንገት በገጠመው ሁኔታ በስሜት ተነሣሥቶ በአጋጣሚ ኃጢአት ሊፈጽም ይችላል:: ይህን ኃጢአት የፈጸመው ሰው መሳሳቱ ሲገባው ወዲያው ለምን ፈጸምኩ ብሎ ተጸጽቶ ንስሐ በመግባት ሥርየት ያገኛል:: ቅዱስ ዳዊት ልዩ ኃጢአት ያለው የዚህ ዓይነቱን ሳይሆን፣ ማፈር፣ መጸጸት ቀርቶ፣ ነውሩ እንደ ጽድቅ ተቆጥሮ፣ በተናጠልም ሆነ በቡድን ወይም በሀገር ደረጃ ኑሮአችን ነውና ሕጋዊ ይሁንልን እስከማለት ተደርሶ ከሚፈጽሙት የድፍረት ኃጢአት አድነኝ ማለቱ ነው::

አንድም እኔንም በድፍረት ኃጢአት ምክንያት ነውረኛ፣ አስጸያፊ፣ ርኩስ፣ ስሕተተኛ፣ ክፉ፣ ከሀዲ፣ ሕግን ተላላፊ በመፀኛ አታድርገኝ፡፡ ቤተሰቤም እንዲህ ያለ ርኩሰት ሲፈጽም ከማየት ሰውረኝ ማለቱ ነው፡፡

በተጨማሪም ቅዱስ ዳዊት ንጉሥ ነውና ሕዝቤንም ልዩ ከሆነ የድፍረት ኃጢአት ግዞት አድነው ሲል ተማጽኗል፡፡ ምክንያቱም የንጉሥ ዳዊት ኃጢአት የርሱ፣ የርሱ ኃጢአት የሕዝቡ ኃጢአት በመሆኑ ተጠያቂ ነውና ይህን ተናገረ፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ዳዊት ሕዝቡን ባስቆጠረ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሊቀጣው ፈለገ፡፡ ሦስት የቅጣት አማራጭ ቀረበለት፡፡ አንደኛው የሦስት ዓመት ረሀብ፣ ሁለተኛው የሦስት ወር የጠላቶቹ ሰይፍና ሦስተኛው ለሦስት ቀን የእግዚአብሔር ሰይፍ ቸነፈር ነበር፡፡ የርሱ ምርጫ ግን በሰው እጅ ከምወድቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻለኛል በማለት እርሱ እግዚአብሔር ይቅጣኝ ብሎ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ቸነፈርን ሰድዶ በአንድ ጊዜ ከእስራኤል ሰባ ሺሕ ሰዎች ወደቁ፡፡ ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤል ራራላቸው፡፡ ኢየሩሳሌምን ጨርሶ ለማጥፋት የተዘጋጀውንም መልአክ «በቃህ አሁን እጅህን መልስ» አለው፡፡ በወቅቱም ቅዱስ ዳዊትና አብረውት ያሉት ሽማግሌዎች ማቅ ለብሰው በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠገብ ቆመው ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ በሰማይና በምድር መካከል የተመዘዘ ሰይፍ ይዞ አየ፡፡ እርሱና ሽማግሌዎቹ በግንባራቸው ተደፉ፡፡ ቅዱስ ዳዊትም ለእግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲቆጠር ያዘዝሁና የበደልሁ እኔ ነኝ፤ ሕዝቤ ምን አድርጓል? አምላክ ሆይ እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ይሁን፤ ሕዝቡን አትቅሰፍብኝ፤ በማለት ጸለየ /፩ዜና ፳፩ ፥ ፩-፲፯/፡፡

> *የሰው ልጅ በድፍረት ኃጢአት አእምሮው ሲዝል ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር ያለው ግንኙነቱ ይቋረጣል፡፡ ሕይወቱም በሥጋም በነፍስም በእግዚአብሔር የተናቀ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ከናቀው ደግሞ በቅዱሳኑም ሁሉ የተናቀ ይሆናል፡፡*

ከዚህ የምንረዳው አንደኛው ነገር ቅዱስ ዳዊት በሠራው ኃጢአት /ሕዝቡን በማስቆጠሩ/ ሕዝቡ መቀጣቱንና ሕዝቡም ተጐጂ መሆኑን ሁለተኛው ነገር ደግሞ በሕዝቡ ቅስፈት ቅዱስ ዳዊት ጥፋቱ የኔ ነው፤ እኔንና ቤተሰቤን ቅጣን በማለቱና ይቅርታ በመጠየቁ ለሕዝቡ መቀሰፍ ቅዱስ ዳዊት ተጠያቂ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ታሪክ በርኩሰት ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ሲቆጣ እኔ አያገባኝም ብሎ ባለቤትነትን ለሌላ ሰጥቶ ጥግ መያዝ ተገቢ ያልሆነና ቅጣት የሚያመጣ መሆኑን ያመለክተናል፡፡

በመሆኑም ቅዱስ ዳዊት «የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ» ሲል በዚህ ጸሎቱ እኔ በፊትህ አስጸያፊ ነገር ፈጽሜ የተጠላሁ የተናቅሁ አታድርገኝ፤ አንድም በእኔ ዙሪያ ያሉትም አስቀይመውህ ባንተ ከመጠላት አድናቸው፤ ወገኔንና ሀገሬን ነውር፣ ርኲሰት ፈጽመው ባንተ ተንቀው ከመጥፋት /ከመቀጣት/ አድናቸው ማለቱ ነበር፡፡

የሰው ልጅ በድፍረት ኃጢአት አእምሮው ሲዝል ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር ያለው ግንኙነቱ ይቋረጣል፡፡ ሕይወቱም በሥጋም በነፍስም በእግዚአብሔር የተናቀ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ከናቀው ደግሞ በቅዱሳኑም ሁሉ የተናቀ ይሆናል፡፡ በዚህ ብቻ ሳያበቃ የሕዝብና የአሕዛብም መሣቂያና መሣለቂያ ይሆናል፡፡ ለዚህ ማስረጃ እንዲሆነን የሚከተለውን ማስገንዘቢያ እንመልከት፡፡

## በሕዝብና አሕዛብ /ኢአማንያን/ መናቅ

የድፈረት ኃጢአት መፈጸም ሕዝብ በተባሉ እንደ ሕጉ በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ ያስንቃል፡፡ ለምን ቢሉ በኃጢአቱ ምክንያት እግዚአብሔር ይለየዋል፡፡ እግዚአብሔር ከተለየው ገበናው ይወጣል /ይጋለጣል/፤ በዚህም መዘባበቻ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በእስራኤል ዘንድ እግዚአብሔር እርም ያለውን የወሰደ /የሰረቀ/ አካንን ስናይ ምንም እንኳ ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ሳያየው ቢሆንም በእግዚአብሔር ኃይል በመጋለጡ እስራኤል ተፀይፈውት ከነቤተሰቡ በአደባባይ በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት አድርገውታል፡፡ ዛሬ እንዲህ ዓይነቱ የድንጋይ ወገራ ባይኖርም መልካም ከሆኑት የእግዚአብሔር ሕጎች ተለይቶ በጸያፍ የተገኘና የድፍረት ኃጢአቱም አደባባይ የወጣበት ሰው የሕዝቡ ዓይን የድንጋይ ወገራ እንደሚሆንበት አያጠራጥርም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው በኅብረተሰቡ ዘንድ ለሓላፊነት የማይበቃና የማይታመን ባለፈና ባገደመ ቁጥር በጥርጣሬና በንቀት ዓይን የሚታይ ይሆናል፡፡

በአሕዛብም ዘንድ ደግሞ እንደ ሶምሶን የተናቀ ያደርገዋል፡፡ ሶምሶን በእግዚአብሔር መልአክ ብሥራት የተወለደና የእግዚአብሔር ኃይል እያደረበት አንበሳን በእጁ የገነጣጠለ፣ ሦስት መቶ ቀበሮ ይዞ የጠላቶቹን ማሳ ያቃጠለ፣ በአህያ መንጋጋ አንድ ሺሕ ሰው የገደለና ክዐለት ላይ ውኃ የፈለቀለት ሆኖ ሳለ በጋዛና በሶሬት ሸለቆ ካገኛቸው ጋለሞታ ሴቶች ጋር በመርከሱ፤ በተለይም በደሊላ ሴሰኝነት ፍትወት ውስጥ ሳለ ከእርሱ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚለይበትን ምስጢር በደሊላ ጭቅጨቃ በመግለጡና በአሕዛብ ሴት /ደሊላ/ በእጇ በመላጨቱ ከእግዚአብሔር የሚሰጠው የጸጋ ኃይል ተለየው፤ እንደጥንቱም ጠላቱን ማሸነፍ ተሳነው፡፡ ባዋረዳቸው አሕዛብ ፊት ተዋረደ፡፡ አስረው ጎተቱት፤ ዓይኑን አውጥተውም መጫወቻ አደረጉት፤ ሣቁበት ተሣለቁበት፡፡ በዚህም ለአሕዛብ ሁሉ ፀያፍ ሆነ፡፡ ቅዱስ ዳዊትም ያለው በድፍረት ኃጢአት ምክንያት እንዲህ ባለ ሁኔታ እግዚአብሔርን በማያምኑ ሰዎች ፊት ከመዋረድ አድነኝ ነው፡፡ ዛሬም እያንዳንዳችን በክርስቶስ የተሰጠንን የጸጋ ልጅነት በመጣል በአሕዛብ እጅ እንዳንዋረድ ሶምሶን እንዳደረገው ከአሕዛብ ጋር ጸያፍ ኃጢአት ከመፈጸም ይጠብቀን ዘንድ እግዚአብሔርን አስቀድመን መለመን ተገቢያችን ነው፡፡

## በቅዱሳኑ ዘንድ መናቅ

ቅዱስ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በዝሙት መውደቁ ሳያንሰው ኦርዮንን በማስገደሉ በነቢዩ ጋድ ተዘልፏል፡፡ እሱ በንስሐው ከመቀሰፍ ቢድንም በኃጢአት የተፀነሰው ሕፃን ግን የቅጣቱ ሰለባ ሆኗል፡፡ በሐዋርያት ዘመንም ሀናንያና ሰጲራ ወደ ሐዋርያት ማኅበር ለመግባት ቤታቸውን ሸጠው ከገንዘቡ ግማሹን ደብቀው ሐዋርያትን ለማታለል ቢሞክሩም ለቅዱስ ጴጥሮስ ውሸታቸው ስለተገለጸለት ለድፍረታቸው በቅዱሳን ሐዋርያትና በመላው የአንድነቱ ማኅበርተኞች ፍፁም የተናቁ ሆኑ፤ የሞት ቅጣትም አግኝቷቸዋል፡፡/ሐዋ.፭ ፥ ፩/ እነዚህ በአካለ ሥጋ ሆነው ፊት ለፊት አስነዋሪ ሥራ በመሥራታቸው በቅዱሳኑ እንዲዘለፉ ተደርገዋል፡፡

ከሕይወተ ሥጋ በኋላ ላለው ደግሞ በምድር በፈጸመው አስነዋሪ ግብር የተቀጣውን ነዌን እንደ ምሳሌ ማየት ይቻላል፡፡ በዘመኑ በሥጋዊ ደስታ ተንደላቆ በድሆች ላይ ጭከና የፈጸመው ነዌ በሕማምና በታላቅ ስቃይ በደጁ ላይ የወደቀውን፣ ስለአብርሃም አምላክ እያለ የሚማጸነውን ድሀውን አልዓዛርን ተፀየፈ፡፡ ከዚህ ዓለም መለየት በኋላ ግን በምላሹ ያተረፈው በታላቁ ጻድቅ አባት በአብርሃም ፊት አለመከበርን ነበር፡፡ /ሉቃ.፲፮/ በቅዱስ መጽሐፍ እንደምናነበው በምድር የምንሠራው ኃጢአት በምድርም ሆነ በሰማይ የሚያመጣው አሉታዊ ውጤት ከላይ እንዳየነው አሳዛኝ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ታሪክ መጠቀሱ ለመማር ነውና ከድፍረት ኃጢአት በመቆጠብ በቅዱሳኑ



www.eotcmk.org

ክብርና ሞገስ እንድናገኝ ዘወትር ከድፍረት ኃጢአት ሰውረኝ ማለት ይገባል::

## በእግዚአብሔር መናቅ

ከላይ እንዳየነው ሁሉ የድፍረት ኃጢአት በእግዚአብሔር መናቅን ከዚያም ጋር የተናጠልና ጅምላ ጥፋትን ያስከትላል:: በቅዱሳት መጻሕፍት የተዘገቡትን ያለፉትን የድፍረት የኃጢአት ሥራዎች ዛሬ ከሚፈጸሙት ጋር ለማወዳደር የሚከተሉትን የርኩሰት ኃጢአት ምሳሌዎች እንመልከት::

፩. በምድር ላይ ሳንበተን ስማችንን እናስጠራ ብለው የተነሡትን የሰናዖር ሰዎች ስናይ የፈጠራቸውን እግዚአብሔርን ሳይሆን የራሳቸውን ክብር ብቻ ሊገልጽ የሚችል ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ያሉ ናቸው:: ግንቡን ለመሥራት በታላቅ ትጋት በጀመሩ ጊዜ እግዚአብሔር ክፉ ሥራቸውን አልወደደም:: «ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው» በማለት ሁሉን የፈጠረ አምላክ በዓላማ በአስተሳሰብ እንዲለያዩ በቋንቋቸውም የማይግባቡ እንዲሆኑ አደረገ:: ምክንያቱም የተፈጠሩበትን ዓላማ ስተው እግዚአብሔር በሠራው አእምሮ ሠሪው ሳይሆን ተሠሪው እንዲደነቅ፤ እንዲመሰገንና እንዲመለክ በመፈለጋቸው ነው:: /ዘፍ.፲፩፥፩-፱/ እያንዳንዱ ክርስቲያን ዘላቂ በሆነው ስሙ በዘለዓለም መዝገብ ይመዘገብ ዘንድ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሥራ ብቻ መሥራት ይገባዋል::

፪. እግዚአብሔር በመፍጠሩ «ተፀፀተበት» የተባለለትን ሕዝብ ታሪክ ስናይ በኖኅ ዘመን የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ የሴት ልጆች /የአዳም ሦስተኛ ልጅ/ ከቃየን ልጆች ተለይተው በደብር ቅዱስ ይኖሩ ነበር:: የቃየንን ልጆች አይተው የቅድስና ኑሮአቸውን ትተው ወደ ርኩሰት ወረዱ:: እነሱም ከዚህ ዓለም ሰዎች የተሰወረውን ቅጠል መበጠስ፣ ሥር መማስ፣ የሟርትንና የመተትን ሥራ ወዘተ አስተማሩ:: እነሱም የወለዷቸው ልጆች ኔፍሊም ሆኑ:: ኔፍሊምም ወላጆቻቸው ያመረቱትን ምግበ ሥጋ በልተው ጨርሰው አባት እናታቸውን እስከ መብላት ደረሱ:: በተጨማሪም ፍጡርን አመለኩ /ሄኖ.፪፥፩-፲፩/ በዚህ እግዚአብሔር ጠላቸው፤ እነርሱንም በመፍጠሩ በሰውኛ ቋንቋ «አዘነ» ተባለለት:: በውጤቱም ዓለም በመላው በንፍር ውኃ ተጥለቀለቀ:: በጻድቁ ኖኅ አማካኝነት ጥቂት ነፍሳትን ብቻ አተረፈ::

በዚሁ አንጻር ያሁኑ ዓለምን ስንመለከት ርኩሰቱ ምን ያህል ይሆን? ከደብር ቅዱስ እንደወረዱት የሴት ልጆች ከቅድስቲቷ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ተለይተው መጀመሪያ ወደ ኑፋቄ ቀጥሎ ወደ ፍፁም ዓለማዊነት የተለወጡት የዓለም ሕዝቦች ምን ያህል ናቸው? የኛ እምነት ዓይነት ባይሆኑም እንኳ የጸሎት ቤት ናቸው የሚባልላቸው ዛሬ ግን ወደ ዳንስ ቤትና ወደ ሌላ ሥጋዊ አገልግሎት የተለወጡት ምን ያህል ይሆኑ? እንደ ኔፍሊም መብላት መጠጣት የሚወዱ የሀገራቸውን ንብረት፣ የወገናቸውን ሀብት አልፎም የቤተሰባቸውን ሳይቀር ቀምተው በልተውና ጠጥተው የራሳቸውን ድሎት ብቻ የሚሹ የሕዝብን አደራ የሚበሉ በርካቶች ናቸው::

፫. በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች /ዘፍ.፲፫፥፫/ የተባሉ በዮርዳኖስ አውራጃ ዙሪያና በሳቦኤ ምድር በገሞራና በሰዶም ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ያዘወትሩት የነበረው ኃጢአት በአካባቢው የታወቀ ነበር:: /ኩፉ.፲፪፥፶፩-፶፪/:: እርሱም ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት መገናኘት ብቻ አልነበረም:: እንግዳ ሆኖ የተቀላቀለውን ሰው ሁሉ እያስቃዩ ይሴስኑበት ነበርና:: እስኪሞት ድረስ በርሱ ላይ በደል ይፈጽሙበትም ነበር:: ስለዚህም ሎጥን ጠርተው በዚህ ሌሊት ወደ ቤትህ የገቡትን ሰዎች እናውቃቸው ዘንድ አውጣልን በማለት በሩን ለመስበር ይታገሉ ነበር:: ሎጥም ግብራቸውን ያውቅ ነበርና ወንድ የማያውቁ ሴቶች ልጆቹን ሊያወጣላቸውና እንግዶቹን ግን እንዲተውለት ለምኖአቸው ነበር:: እነሱም እንቢ በማለት ክፉታቸውን ቀጠሉበት በመሆኑም እግዚአብሔር በእሳትና ዲን አቃጠላቸው /ዘፍ.፲፱፥፳-፲፩/::

ዛሬም በዓለማችን ያለው እንደ ሰዶም ያለ ክፉትና ኃጢአት ቀላል አይደለም:: ሠለጠኑ ከሚባሉት ከተሞች ጀምሮ በመላው ዓለም እየተስፋፋ የመጣውና በየአደባባዩ በመሰለፍ ይፈቀድልን የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሣው የዘመኑ ግብረ ሰዶም ሂደት በነቢዩ ኢሳይያስ «የፊታቸው እፍረት ይመሰክርባቸዋል፣ እንደ ሰዶም ኃጢአታቸውን ያወራሉ፣ አይሠውሩአትም በራሳቸው ላይ ክፉ ነገርን ሠርተዋልና ለነፍሳቸው ወዮ! የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና» በማለት የተናገረው ይፈጸም ዘንድ ነው:: /ኢሳ.፫፥፱/ በመሆኑም ከዚህ ፀያፍና የድፍረት ኃጢአት እያንዳንዱ ክርስቲያን እንዴት ራሱን ማራቅ እንዳለበት ተገቢውን ጥረት ማድረግና ሌላ ወገኑን ለመታደግ መታገል ይኖርበታል:: ከዘመናችን አንጻር የመሥዋዕትነት ያህል የሚቆጠርም ነውና::

## ሐ. ያለንበት ዘመን የድፍረት ኃጢአት

ዓለማችን ከላይ በዝርዝር እንዳየነጠውና ከዚያም በላይ የድፍረት ኃጢአት ሠልጥኖባት ይገኛል:: በትንቢት መጽሐፍ የተጠቀሰውና ለዘመናችን የሚስማማው ኃይለ ቃል «አምስቱ ውሾች ግን ከመንግሥተ ሰማይ አፍአ ወደ ገሃነም ይወጣሉ:: እነዚህም ሥራይን የሚያደርጉ፣ ዘማውያን፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ ጣዖትን የሚያመልኩና የሐሰትን ሥራ የሚወዱ ናቸው» በማለት የተቀመጠው ነው /ራዕ.፳፪፥፲፭/:: በአሁኑ ጊዜ እነዚህ በእግዚአብሔር የተጠሉ የድፍረት ኃጢአቶች መልካቸው ተለውጦና በሥልጣኔ ተሸፍነው እንደ ቅድስና ሲፈጸሙ ይስተዋላሉ::

ዛሬ ለገንዘብና ለጾታዊ ፍላጎት፤ እንዲሁም በቅናትና በጥላቻ ወዘተ የሰውን ልጅ በሥራይ በማሳበድ፣ በማፍዘዝና በመግደል የተጠቀሙ የሚመስላቸው ብዙ ናቸው:: ለዚህም በየጠበላቱ ያለው ሁኔታ ሲስተዋል በሥራይ ምክንያት የሚንገላቱ ታማሚና አስታማሚ ቁጥር ቀላል አይደለም:: ይህ ለምን ይሆን? የድፍረት ኃጢአት ስለተጸናወተን አይደለምን?

ከላይ ያየነው ዘማነት የድፍረት ኃጢአት መሆኑን ነው:: ዛሬ እየተለመደ የመጣው ቅዱስ ቁርባንን ተቀብሎ እስከ ጋብቻ መታገስ እያቃተ ቁርባን ማፍረስ፤ በሥርዓተ ተክሊል ቅዱስ ጋብቻን ከፈጸሙ በኋላ አልተመቸኝም፣ አልተመቸችኝም እየተባለ ለራስ ያልተገደበ ሥጋዊ ፍላጎት በማድላት በድፍረት የተክሊል ጋብቻን ማፍረስ፤ አንዳንዴም ክህነትን በድፍረት ኃጢአት ማስነወር ሳይቀር ፀያፍ ኃጢአት ሲፈጸም ይታያል:: የለየላቸውም በግልጽና በስውር ሰዶማዊነቱን እያስፋፉት በመሆኑ ምን ያህል አሳፋሪ ነገር እየተከናወነ እንዳለ መገመት ያስችለናል::

ከዚህም ሌላ እንደ ቀድሞው ጣዖት አቁሞ <አምልኩ> የሚለን ባይኖርም አንዳንድ በዓለም ታዋቂ የሆኑትን ሰዎችን ማምለክ ተጀምሯል:: ለአብነትም ለመጥቀስ ማራዶና የተባለው ኳስ ተጨዋች እንደ ቤተመቅደስ ያለ ቤት ተሠርቶለት ሐውልት ቆሞለት እናደንቅሀለን የሚሉት ሰዎች ስግደትና ጸሎት ሲያደርሱለት ታይቷል:: ታዲያ ይህ አባዜ ከጣዖት አምልኮስ አይብስምን? ይለይ ይሆንን? ሊመለክ የሚገባው የሰውን ልጅ ከነጥበቡ የፈጠረ እግዚአብሔር ሲሆን ለፈራሽ በስባሹ ያልተሰጠውን መስጠት «እግዚአብሔርን እየወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ ባላመለኩት መጠን የማያስተውለው ልባቸው ጨለመ:: ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ:: የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰው ... ለወጡ» /ሮሜ.፩፥፳፩-፳፫/ በማለት እንደተገለጸው ያለ የድፍረት ኃጢአት እየተፈጸመ እንደሚገኝ ያስተውሏል::

የሐሰት ሥራና ነፍስ መግደልም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየተደረገ ያለ የድፍረት ኃጢአት መሆኑ እሙን ነው:: አፈጻጸሙ የሠለጠነ በመሆኑ ቢረቅና በሰው የማያስጠይቅ ቢመስልም ከእግዚአብሔር ጥበብ የሚያመልጥ አያደርገውም:: ከሱ የሚሰወር አንዳች ነገር የለምና:: ለሚፈጽመውም በድፍረት ኃጢአቱ እየተባበሩ እኔ የለሁበትም ማለት ከርኩሰቱ አያጠራም:: ሐሰቱ ገዝፎ፣ የእውነትን ያህል

ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል



'
www.eotcmk.org



*በሲምፖዚየሙ ከተገኙ እንግዶች በከፊል /በስብሰባ ማዕከል፣ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፳፻ ዓ.ም*

# «አብነቱ ያለ አብነት እንዳይቀር»

**፳፻** ዓ.ም የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ተብሎ ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን አህጉራዊ ሆኖ ተከብሮአል። ለዚህ በዓል አከባበር የዕውቀት መገኛዎች የሆኑት የአብነት ት/ቤቶች ግን ተዘንግተው ቆይተዋል። ይህን አስመልክቶም ሐምሌ ፳፮ ቀን ፳፻ ዓ.ም አዲስ አበባ ስድስት ኪሎ አካባቢ በሚገኘው የስብሰባ ማዕከል «አብነቱ ያለ አብነት እንዳይቀር!» በሚል ርእስ አንድ ዐቢይ ሲምፓዚዬም ተካሒዶ ነበር። ዐቢዩ ጉዳይ የአብነት ት/ቤቶች በመሆናቸው በተጠቀሰው ርእስ አንድ ዘጋቢ ፊልም ተዘጋጅቶ ይፋ ከመደረጉም በላይ ለዕለቱ የተጋበዙት እንግዶች ሁሉ በዚሁ ርእስ ላይ መግለጫዎችን ሰጥተው ነበር። የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ባደረጉት ንግግር «የአብነት ት/ቤቶች ለዘመናዊ ትምህርት መሠረት እንደሆኑ ግልጽ ነው። ት/ቤቶቹ የሚሰጡት ትምህርት እንደ ሌሎቹ በቅኝ ግዛት ተይዘው እንደነበሩ ሀገሮች ከሌላ ሀገር የመጣ ሳይሆን ውልደቱ ኢትዮጵያዊ የሆነና የራሱ የሆነ አሻራ እንዳለው እያመላከቱ ያሉ ሕያው ምስክሮች ናቸው»። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ደግሞ «የአብነት ት/ቤቶች የቤተ ክርስቲያኒቱ ቁልፍ ተቋሞት ናቸው» ብለው ነበር። የኤፌዲሪ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ክቡር አምባሳደር መሐመድ ድሪርም «ኢትዮጵያ ሀገራችን በዓለም የራሳቸው ጽሑፍ ካላቸው እንደ ቻይና፣ ሕንድ፣ ኮርያ፣ ጃፓን፣ እስራኤል እና አውሮፓ እንዲሁም የስሎቫክና የዓረቡ ዓለም ሀገሮች ተርታ እንድትቆጠር ከአራት ሺሕ ዓመታት በፊት የነበረው የሳባውያን ፊደላትም ለአሁኑ ትውልድ እንዲተላለፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የማይሽረው ታላቅ አስተዋጽዖ እንዳበረከተች ታሪክ ይመሰክራል። ... በ፬ኛው ክፍለ ዘመን የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከዚሁ ጋር በተያያዘ መስፋፋቱን የታሪክ ጸሐፍት ይዘግባሉ። በዛሬው ዕለት የምናስታውሳቸው የአብነት ትምህርት ቤቶችም በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉና ለበርካታ የሀገራችን ዜጐች የትምህርትን የብርሃን ጸጋ ያጐናጸፉ ናቸው። ... ሌሎች ተዳሳሽ ቅርሶችም ለቱሪዝም ዕድገትና ለሕዝቦች ትስስር ያላቸው ፋይዳ ተዘርዝሮ የማይለቅ ነው።... ታዲያ እነዚህና ሌሎች ዕውቀቶች ሳይበረዙና ሳይጠፉ ወደኛ ሊሸጋገሩ የቻሉት ምስጋና ይድረሳቸውና በአብነት ትምህርት ቤቶች አማካይነት ነው። ...» ብለዋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር አየሌው ሲሳይ ደግሞ «ያለ እነዚህ ት/ቤቶች በተለይም ያለ ዜማው ቱሪዝማችን አይኖርም። ፈረንጆቹ ለመስቀል በአዲስ አበባ፣ ለገና በላሊበላ፣ ለጥምቀት በአዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ አክሱምና ላሊበላ የሚገኙት የአብነት ት/ቤቶች በሚያሸጋግሩት ዜማ ነው። ሌላው ቀርቶ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶችም በቁልቢ፣ በግሸን፣ በክርስቶስ ሰምራ፣ ላሊበላና አክሱም የሚገኙበት አንዱ ምስጢር ዝማሬው ነው። ስለዚህ ያለ አብነት ት/ቤቶች ቱሪዝም አይኖርም። አየር መንገዱም፣ መኪኖቻችን፣ ሆቴሎቻችን ሁሉ ከቱሪስቶች የሚጠቀሙት በእነርሱ ነው...» ብለዋል።

ከእነዚህም ሌላ እነ ብፁዕ አቡነ ገሪማ፣ እነ መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ፣ ሊቀ ጉባኤ ፈቃደ ሥላሴ እና የማኅበሩ ተወካዮች መግለጫ ሰጥተዋል፡ የርእሰ አድባራት ወገዳማት አዲስ ዓለም ማርያም ሊቃውንትም በቦታው ተገኝተው ወረብ አቅርበዋል። የሁሉንም ሙሉ ንግግሮች በዚህ ዕትም ማቅረብ ባይቻልም ለዛሬው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑትንና በግእዝና በግእዝ ጽሑፎች ላይ ጥናት በማድረግ የሚታወቁትን የአቶ ገዛኸኝ ጌታቸውን ንግግር አቅርበንላችኋል።

*መልካም ንባብ።*



www.eotcmk.org



ኅዳሪ ወማኅደር፣ ፍቅረ ጥበብ አስተጋብአሙ በዝንቱ መካነ አእምሮ

### ፩. የአብነት ትምህርት ቤቶች ምንድን ናቸው?

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ የወቅቱ ነገሥታት ከተቀበሉት ከ፬ኛው ምእተ ዓመት በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሟላ ሁሉን አቀፍ የትምህርት ሥርዓት ዘርግታ መደበኛ ትምህርት መስጠት ጀምራለች:: ይህ ከ፩ሺሕ፭፻ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ የትምህርት ሥርዓት በዓለማችን ከሚገኙት ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርቶች አንዱ ያደርገዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጎመባቸው የመጀመሪያዎቹ ስድስት ቋንቋዎች አንዱ በሆነው በግእዝ ቋንቋ ይሰጥ የነበረው ይህ ሥርዓተ ትምህርት ዋና ዓላማው ለቤተ ክርስቲያኒቷ አገልግሎት የሚሰጡ ካህናትንና ሊቃውንትን ማፍራት ነው:: ይህን ዓላማውን በነዚህ የአብነት ትምህርት ቤቶች አማካኝነት በተሳካ ሁኔታ ሲያከናውን ኖሯል፤ አሁንም እያከናወነ ይገኛል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ ውስጥ በነዚህ ትምህርት ቤቶች መደበኛ ትምህርት የምትሰጥ ብቸኛ ተቋም ሆና እስከ ፳ኛው ምእተ ዓመት ድረስ ቆይታለች:: ኢትዮጵያ በዚህ ሥርዓተ ትምህርት አማካኝነት የራሷን ፊደል፣ ሥርዓተ ጽሕፈት፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ የዘመን አቆጣጠር፣ ... ከትውልድ ትውልድ ስታስተላልፍ ኖራለች፤ አሁንም እያስተላለፈች ትገኛለች:: እርግጥ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ያህል ያልተስፋፋ ቢሆንም በጣም በተወሰነ ደረጃ በዓረብኛ ቁርዓን የማስቀራትና ሌሎች የእስልምና ሃይማኖት ትምህርቶችን የማስተማር ተግባር ከእስልምና ወደ ኢትዮጵያ መግባት ጀምሮ ይሰጣል::

የአብነት ትምህርት ቤቶች በማእከላዊ መንግሥትም ሆነ በየአካባቢው ገዢዎች የገንዘብ ድጎማም ሆነ ሌሎች ድጋፎች የማያገኙ ሲሆኑ እነዚህ አካላትም በሥርዓተ ትምህርቱ ቀረጻም ሆነ በአስተዳደራቸው ውስጥ ጣልቃ ሳይገቡባቸው ራሳቸውን በራሳቸው ሲመሩና ሲያስተዳድሩ የኖሩ ናቸው:: ሥርዓተ ትምህርቱ በአብዛኛው ተመሳሳይ ቢሆንም እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የራሱ ነጻ አስተዳደር፣ የራሱ የብቃት (የጥራት) ደረጃ ያለው በመሆኑ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት የሚለያይ ሆኖ ይኖራል::

በነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች አካባቢያቸውን ለቀው ርቀው በመሄድ የሚማሩ ናቸው:: ተማሪዎች አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሌላ አካባቢ ሄደው የሚማሩባቸው ምክንያቶችም በጣም አጥጋቢዎች ከመሆናቸው በተጨማሪም ውጤታማ የመሆናቸውም ምስጢሮች ናቸው::

ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. ሙሉ ጊዜያቸውን ሰውተው በሙሉ ልባቸው ለመማር፤ በቤተሰብ አካባቢ መሆን እንቅፋት ስለሚሆንና ቤተሰብም ልጆቹ በአካባቢው ካሉ ለሥራም ለሌላም ጉዳይ የልጆቹን ልብና ጊዜ ስለሚሻማ ነው::

ለ. ታላላቅ መምህራን በተለያዩ አካባቢዎች ስለሚገኙ ከእነርሱ ለመማር - ወደ ትምህርት ሲኮበልሉ የትኛው ሀገር ያለው መምህር በየትኛው ሙያ ስመጥር መሆኑን መርምረው ነው::

ሐ. ከድሀ ቤተሰብ የተወለዱና መማር የሚፈልጉ ተማሪዎች በተወለዱበት መንደር ለምኖ መማር ስለሚያሳፍራቸው፤

መ. በቤተሰብና በጓደኛ መሀል በምቾት ሆኖ በሙሉ ልብ ትምህርትን መከታተል ስለሚያስቸግር፤



www.eotcmk.org

ሠ. በአካባቢው የነበሩ ታላለቆቻቸው በተማሩባቸው ትምህርት ቤቶችና በአ ስተ ማሯቸው መምህራን ለመማር ባላ ቸው መንፈሳዊ ቅናት ነው፡፡

አካባቢን ጥሎ ከመሄድ ጋር ተያ ይዞ ቲማሪዎች እናትና አባታቸው ያወ ጡላቸውን ስም ትተው የመምህራቸውን ስም ይቀበላሉ፤ ከዚያም በዚያው ስም ሲጠሩ ይኖራሉ፡፡ ይህ የስም መለወጥ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ ስም እንዳወጣላ ቸው ለመምህራቸው ደቀ መዝሙር መሆናቸውን ለማስረገጥ፣ ቤተሰቦቻቸው ቢፈልጓቸው እነሱ ባወጡላቸው ስም የሚያውቃቸው ስለሌለ እንዳይገኙና በፍ ጹም ሰብእናቸውን ጭምር ለትምህርት ማስገዛታቸውን ለራሳቸው ለማረጋገጥ ጭምር የሚቀበሉት ነገር ነው፡፡

## ፪. የትምህርት አሰጣጡ



*«መልሰው ... » «የትኛውን የኔታ»...*

የትምህርት አሰጣጡ እንደ የመስኩ የሚለያይ ነው፡፡ በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ይካተታሉ ካልናቸው ውስጥ የጥቂቱን በናሙናነት እንመልከት፡፡

**፪.፩. የንባብ ቤት፡-** በዚህ ክፍል የሚገቡት ከ፭ ዓመት ጀምሮ ያሉ ሕፃናት ሲሆኑ በዚህ እድሜ የትምህርትን ጥቅም አውቀው ወደ ትምህርት ቤት ስለማይሄዱ መምህሩ የሚቀበላቸው በጥሩ ሥነ ምግባር ኮትኩቶ የማስተማር ሓላፊነትን ጭምር ይዞ ነው፡፡ ስለዚህ መምህሩ ከመቆጣት፣ ማስፈራራት ጀምሮ አስፈላጊ ሲሆን በል ምጭና በጉማሬ እስከመግረፍ የሚደርስ ቅጣት ይቀጧቸዋል፡፡ በሀገራችን እንዲሁም በሃይማኖታችን (መጻሕፍተ ሰሎሞንን ይመለከቷል) የልጅ አስተዳደግ ሥርዓት ውስጥ «ኩርኩም ከጠፋ ልጅም አይፋፋ» የሚለው አባባል ተቀባይነት ኖሮት ሲያገለግል የኖረ ነው፡፡ ሥነ ምግባር ኖሯቸው መማራቸውም በተግባር እንዲታይ ለመምህራቸውና ከፍ ላሉት ተማሪዎች አክብሮታቸውን ጉልበት በመሳም፣ በማመስገንና በመታዘዝ ያሳያሉ፡፡ የመገረፉ ጉዳይ ከዚህ የትምህርት ደረጃ የሚያልፍ አይደለም፡፡ «ለየኔታ እንዳልና ገር» የሚለው ማስፈራሪያም በየቤተሰቡ የተለመደ ነበር፡፡

በዚህ ደረጃ ሌላው የትምህርት አሰጣጥ የቃል ጥናት (ሽምደዳ) ነው፡፡ ይህም ፊደል ከመለየት ጀምሮ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል፡፡ ፊደል የማስለየት ተግ ባር ሁልጊዜ ም በየትኛውም ደረጃ የሽም ደዳው መንገድ ይለያይ እንጂ በሽምደዳ የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ በቃል ጥናት ረገድ ሳይረዱት የሚሸመድዱት መልእክተ ዮሐንስንና ዳዊትን ነው፡፡ ይህም የንባብ ደረጃዎችንና የአነባበብ ሥርዓትን ማስተማሪያው ነው፡፡ በዚህ ረገድ የቃል ትም ህርቱ አስፈላጊነት አያከራክርም፡፡ በዚህ ክፍል ውዳሴ ማርያም፣ መልክአ ማርያም፣ መልክአ ኢየሱስና ሌሎችም ጸሎቶች በቃል ይጠናሉ፤ እነዚህ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወቅትም የሚደ ገሙ ናቸው፡፡

የጽሕፈት ትምህርት አሰጣጡ ሕፃ ናቱ እያጠፉ፣ እየሰረዙና እየደለዙ እን ዲማሩ በሰሌዳ (በእንጨት ወይም በበሬ ብራኳ አጥንት) ላይ በከሰል እየጻፉ ይለ ማመዳሉ፡፡ ይህንንም መምህሩ ወይም ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የደረሰው ተማሪ ያከናውናል፤ ስሕተ ታቸውን ያርማል፡፡ ጽሕፈት ሲማሩም ተማሪዎች ብርዕ መቅረጽና ቀለም መበጥበጥ ይማራሉ፤ ይለ ማመዳሉ፡፡ በቃል እየተነገራቸው መጻፍና ከመጻሕፍትም መገልበጥ ይለማመዳሉ፡፡ በመጨረሻም በመምህራቸው ይፈተናሉ፡፡ ይህ ደረጃ በግምት ፪ ዓመታት ይፈጃል፡፡ /አለቃ እንባቆም፣ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፣ ፩/

**፪.፪. የዜማ ቤት፡-** በዚህ ክፍል ውስጥ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ወቅት የሚዜሙ ዜማዎች ትምህርት የሚሰጥ በት ነው፡፡ የትምህርት አሰጣጡም እንደ የደረጃው የሚለያይ ሲሆን ተማሪዎቹ መዝሙሮቹን በዜማ እየጮኹ ሲያዜ ሟቸው ከነሱ በላይ ያሉት ተማሪዎችና አስተማሪያቸው እያረሟቸው ይማራሉ፡፡ ከፍ ያሉት የዜማ ትምህርቶች ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕ ት፣... በሚከተለው ሁኔታ ይሰጣሉ፡፡ «ዋናው መምህር ከፍ ወዳለ ደረጃ የደ ረሱ ተማሪዎችን ብቻ ይዘው ሌሎቹ በየ ደረጃ እንዲማሩ ያደርጋሉ፡፡ አንድ መም ህር በጣም ኀበዝና ትጉህ ከሆኑ ከአም ስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ተማሪዎችን በአንድ ጊዜ እያዳምጡ ሊያስተምሩ ይች ላሉ፡፡ የዚህ ምክንያቱ በዜማ ጬኸቱ ወቅት መረባበሽ ስላለ ያንን ለመቆጣጠር ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ክፍል የሚኖሩ ተማሪዎች ብዛት የሚወሰነው በትምህ ርቱ ባሕርይ ነው ማለት ነው፡፡

በከፍተኛ ደረጃ ያሉትን የዜማ ትም ህርቶች በተለይ ድጓንና ጾመ ድጓን የመ ሳሰሉትን ለመማር (ለመከታተል) ባለ ምልክቶቹን የዜማ መጻሕፍት ይዞ መገ ኘት በጣም ያስፈልጋል፤ የመጻሕፍት አቅርቦት ባለመኖሩም የራሳቸው የሌ ላቸው የመምህሩ መጽሐፍ በየተራ እን ዲደርሳቸው ይደረጋል፤ በየሦስትና አራት ቀን ቢደርሳቸውም፡፡

በዜማ ትምህርት ወቅት ሁሉም ተማሪ የየራሱን ዜማ ስለሚጮኽ በአንዱ ጬኸት ሌላው እንዳይረበሽ በየራሳቸው ትምህ ርት ውስጥ መመሰጥ እራሳቸውንም ብቻ መስማት አለባቸው፡፡ ይህ ትምህርት አሰጣጥ በመጻሕፍት ቤት አይታይም፤ እዚያ ትምህርቱ የሚከናወነው በፍጹም ጸጥታና መደማመጥ ነውና፡፡

መሪጌታ ሐመልማል «የግዕዝ ቅኔ፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ እና የአምስቱ ጸዋ ትወ ዜማዎች የትምህርት አሰጣጥ ሥነ ዘዴ» በሚለው ጥናታቸው፡-

*የዜማ ትምህርት ሌላው ከባድ የሚያደር ገው ነገር አንድ የግእዝ ቃል እጅግ በርካታና የተለያዩ የዜማ ዐይነቶች ያሉት የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ ዜማዎቹ የሚለያዩትም በሚዜሙበት /በሚነገሩበት/ ስልት መሠረትነት ነው፡፡ ይህም ማለት ሰኞ የሚባለው ዜማ፣ ማክሰኞ የሚባለው ዜማ ወይም ረቡዕ የሚ ባለው ዜማ ሊለያይ ይችላል፡፡ ስለዚህ እጅግ በርካታ የሆኑ ቃላት ብዙ ዐይነት ዜማ ስለ ሚኖራቸው ሁኔታው ትምህርቱን ያወሳስበ ዋል፡፡ (ገጽ.፴፩1)*

ከዚህም በተጨማሪ የዜማ ምልክ ቶቹ በርካታ (ድፋት፣ ጭረት፣ ይዘት፣ ደረት፣ ዘንጥል፣ አቀማጥል፣...) መሆና ቸውና የዘር ምልክቶቹ መብዛታቸው



www.eotcmk.org

የዜማን ትምህርት የበለጠ እንደሚያወሳስበው እኒሁ አጥኚ ይገልጻሉ::

በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚደርሱ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚባሉት በዜማ በመሆኑ የዜማ ተማሪዎች የተማሩትን ለማለትና እንዳይጠፋቸው ለማድረግ በፍጹም አይቸገሩም፤ የዕለት ተዕለት ተግባራዊ ልምምድ የማድረግ ዕድል ስላላቸው:: ከዚህም ሌላ የድምጫ ዕድል ስላላቸው የመከለስ፣ ወደፊት የሚማሩትን የመስማትና የማብላላት አጋጣሚያቸው ብዙ ነው:: በአለቃ እንባቆም ግምት በጥቅል ትምህርቶቹ ፭ ዓመት ከ፮ ወራት ይፈጃል::

**፪.፫.** አቋቋም:- አቋቋም ለመማር ከዜማ መምህራቸው ተለይተው የሚሄዱት ተማሪዎች እዚህ ሲመጡ ከፍ ባለ ክብር ይቀበሏቸዋል:: የመምህርና የተማሪ ልዩነትም በእድሜ ከገፋት መምህራን በቀር አይታወቅም:: ስለዚህም ብዙም የጉልበት ሥራና ወደ ልመና አይሰማሩም:: መምህሩም ተማሪዎቹን በአንቱታ ይጠራል፤ ተማሪዎቹም መምህራቸውን በአንቱታ ይጠራሉ::

የአቋቋም ተማሪ የዕለት ጉርሱን በእጁ ሙያና በምእመናን ቤት በመሄድ ጸሎት በመድገም ያገኛል:: በጎንደር ከተማም ብዙ የአቋቋም መምህራን ስላሉ ከመምህር መምህር እየዞሩ ይማራሉ እንጂ በአንድ መምህር ሥር ታስረው አይቀመጡም:: በአብዛኛው አቋቋም ከትምህርትነቱ ይልቅ ሥልጠናነቱ ይጎላል:: ትምህርቱ ፫ ዓመት ይፈጃል::

**፪.፬.** የቅኔ ትምህርት:- የግእዝ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንደየጉባኤው ስፋት ይለያያል:: በታላላቅ ጉባኤዎች መምህሩ ሁሉንም ተማሪዎች ማስተናገድ ስለማይችሉ ከመምህሩ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የሚያደርጉት ቅኔ መዝረፍ ደረጃ ላይ የደረሱት ከፍ ያለ እርከን ላይ ያሉት ናቸው:: እነዚህ ከመምህሩ ጋር በቀጥታ በመገናኘት የሚማሩት ተማሪዎች ከነርሱ በታች ያሉትንና ገና በጀማሪነት ጉባኤውን የሚቀላቀሉትን የማስተማር ሓላፊነት ይጣልባቸዋል:: ይህም ለአስቀጻዮቹ ተማሪዎች የማስተማር ልምድ እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል::

በቅኔ ትምህርት ወቅት ግሥ በየመጨረሻ ፊደሉ ቅደም ተከተል ይገሠሣል:: ከተማሪዎቹ አንዱ ግሥ ያወርዳል፤ የግሡን እርባታ ግን እንደየግሡ ጠባይ መምህሩ ይጨርሱታል::

ቅኔ ሲነገር በነገራው ሂደት ወቅት የቅኔው ስሕተቶች ወዲያውኑ ይታረማሉ:: የትኛውም ስሕተት ሳይታረም ስለማይታለፍና ስሕተቱ በተሠራበት ቅጽበት መምህሩ አስቁመው ስለሚያስተካክሉ ከአንዱ ስሕተት ሌሎቹ ተማሪዎች ይማራሉ:: ተማሪዎቹ ብዙውን ጊዜ በጥንድም ሆነ በቡድን የማጥናት እድል አላቸው:: ተማሪው የሚቀጽለው ከፍ ያለ ደረጃ ካለው ተማሪ ከሆነና የተሰጠውን እርማት አግባብ አይደለም ብሎ የማይቀበለው ከሆነ ለመምህሩ በቀላሉ የማቅረብና ትክክለኛውን ነገር የመረዳት ዕድል አለው::

በቅኔ ዘረፋ ሂደት ዘራፊው ቅኔውን ከዘረፈ በኋላ ተቀባዩ ሙሉ ቅኔውን በቃሉ ያነባል (ይናገራል):: መምህሩም ተቀባዩ የሚያነበውን ቅኔ አንድ በአንድ እየፈቱ ለጉባኤው ያስረዳሉ:: ቅኔው ከተፈታ በኋላም አገባቡ እየተተነተነ ተማሪዎች የግእዝ ሰዋስውን ያጠናሉ:: ለቅኔ ቆጠራቸውም የየዕለቱን ታሪክ ይማራሉ:: በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍትንም ይማራሉ:: ለማመስጠሪያ እንዲሆናቸውም አካባቢያቸውን እንደምን ማስተዋል እንዳለባቸው ይነገራቸዋል::

ጀማሪ ተማሪ በትምህርት ከሚበልጠው ተማሪ ሥር ሆኖ እንዲቀጽል በመምህሩ ከተመደበ በእሽታ ተቀብሎ ከእርሱ ጋር ያጠናል፤ በየሰፈሩ ዞሮ ለምኖ ያመጣውንም ቁራሽ ያካፍለዋል:: በግዕዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ውስጥ መከባበርና መደጋገፍ የተማሪዎቹ መገለጫ ባሕርይ ነው:: ተማሪ የመምህሩን እግር ያጥባል፤ ተንበርክኮ እግር ይስማል፤ ባልንጀሮቹን እንኳን ሳይቀር በትሕትና እጅ ይነሣል::

የቅኔ ተማሪ ተምሮ ሲያጠናቅቅ ለማስመረቅ ምስክርነት ወደሚሰጥባቸው ታላላቅ አብያተ ጉባኤያት ይሔዳል:: ከዚህ በተጨማሪም አስፋፍቶ ቅኔን ለማወቅና ስመጥር መምህር ለመሆን ጎጃም ዋሸራና ጎንጅ፣ ወሎ ደግሞ የዋድላን ቤት የተራቀቀ ቅኔ ለማጥናት ወደ ዋድላ ሄዶ እውቀቱን ያስፋፋል:: በአሁኑ ጊዜ ደግሞ እነ ጨጐዴ ሃና (አዴት) እና ዛራ ሚካኤል (ሐሙሲት) ታዋቂ መካነ ጉባኤያት ናቸው:: ትምህርቱ በጥቅል ፭ ዓመት ይፈጃል::

**፪.፭. የመጻሕፍት ቤት:-** በዚህ ክፍል የሚሰጡት ትምህርቶች ሀ.የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ለ. የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ ሐ.የሊቃውንት ትርጓሜ መ. የመጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ እና ሠ. መርሐ ዕውር የተባሉት ናቸው::

በመማሪያ አዳራሹ ውስጥ ተማሪዎቹ በፍጹም ሥርዓትና ተመስጦ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ መምህሩ ቦታቸውን ይዘው ትምህርቱን በጸሎት ይጀምራሉ:: ከተማሪዎቹ መካከል አንዱ ጥሬውን ግእዝ ያነባል:: የሚነበበውን ጥሬ ግእዝ መምህሩ እያመሰጠሩ ይተነትናሉ:: ተማሪዎቹ ያልገባቸው ነጥብ ካለ አንድ ምዕራፍ ሲያልቅ መጠየቅ እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል እንጂ በትምህርቱ መካከል አቋርጠው መጠየቅ አይችሉም:: ጥሬውን ግእዝ የሚያነበው ተማሪ ንባቡን የሚጀምረውና የሚያቆመው እንደፈለገው ሳይሆን በመጽሐፉ ውስጥ ምልክት ምልክት ተደርጎበት የሚታይ ምዕራፍ ምዕራፍ አለው:: አንባቢው ተማሪ ሲያነብ ቃል አጠራር ቢሳሳት፣ መቆም በማይገባው ቦታ ቢቆም የመምህሩ ቁጣና ተግሣጽ ይጠብቀዋል:: ይህም ንባብና ቅኔ (ሰዋስው) ለይቶ ስለሚመጣና ተራ ስሕተት መፈጸም የማይጠበቅበት ስለሆነ ነው::

ለትርጓሜ መጻሕፍት የሚመጣ ተማሪ ቀደም ብሎ የሌሎች ሙያዎች ባለቤት በመሆኑ በነዚያ ሙያዎች ስለሚተዳደርና የተማሪዎቹ ቁጥር ጥቂት በመሆኑም ጭምር የምግብ ችግር ብዙም አይገጥመውም::

የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ የላይ ቤትና የታች ቤት ተብሎ ይከፈላል:: ተማሪውም የመረጠው የትርጓሜ መንገድ ያለበትን ትምህርት ቤት ፈልጎ ይማራል:: በትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት በመምህሩና በተማሪው መካከል ያለው ግንኙነት የቤተሰብ ያህል ሆኖ በትምህርትም የቀለም አባትና ልጅ ተባብለው የሚኖሩበት ነው:: የአንዱ ደስታ የሌላው ደስታ የአንዱ ሐዘንም የሌላው ሐዘን ነው::

ሊቃውንት የሚባለው ክፍል ሃይማኖተ አብውን፣ ፍትሐ ነገሥትን፣ ዮሐንስ አፈወርቅን፣ ቁርሎስን፣ መጻሕፍተ መነኮሳትን፣ ፲፬ ቅዳሴያትን፣ ውዳሴ ማርያምንና ሌሎቹን የሚማሩበት ክፍል ነው::

መርሐ ዕውር ደግሞ የዘመን አቆጣጠርን፣ የበዓላትንና የአጽዋማትን አወጣጥ የሚማሩበት የሒሳብ (የቁጥር) ትምህርት የሚሰጥበት ነው:: ይህ አቆጣጠር የፀሐይን፣ የጨረቃንና የከዋክብትን እንቅስቃሴ በመከተል የሚመረመር ነው:: ትምህርቱ በጥቅል ፯ ዓመት ከ፮ ወራት ይፈጃል::

**፪.፮.** የታሪክ ትምህርት:- የታሪክ ትምህርት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በትምህርት መስክነት አይሰጥም:: አለቃ እንባቆም እንደሚሉት ታሪክ የሚያጠና ተማሪ ታላላቅ መምህራን ጋር በመወያየት፣ መጻሕፍትን በመመርመር፣ ታሪካዊ ቦታዎችን በመጎብኘት (በመሳለም) እና የታሪክ መጻሕፍትን በማንበብ የሚያገኘው ነው:: በአጠቃላይ ከአባቶች በቃል፣ ከመጻሕፍት በማንበብ ይማራል:: ይህ ትምህርት አለቃ እንባቆም እንደሚሉት አንድ ዓመት ሊፈጅ ይችላል::

**፪.፯.** የቁም ጽሕፈት፣ የብራና መጻሕፍት ዝግጅትና ሥዕል:- በዚህ ክፍል ተማሪው የቁም ጽሕፈት፣ የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀት ይማራል:: እነዚህን በሚማርበት ወቅትም የቀለም አበጣበጥ፣





'
www.eotcmk.org

የብርዕ አቀራረጽ፣ የመጻሕፍት አጠራረዝና አደጓጎስን ይማራል:: አለቃ እንባቆም እንዲህ ያለ ትምህርት የሚሰጥበት የታ ወቀው ቦታ አንዳ ቤት (በጌምድር ውስጥ የሚገኝ) ነው ይላሉ:: ይሄ አንድ ዓመት ይፈጃል በማለት ይገልጻሉ::

ከዚህ በተጨማሪም ተማሪው የመስ ቀልና የጽላት አቀራረጽንም ይማራል::

ሥዕሎችን በእንጨትና በጨርቅ ላይ እንዲሁም በብራና መጻሕፍት ላይ የመሳል ጥበብን ለመማርም ሦስት ዓመት የሚፈጅ ሲሆን በአጠቃላይ የእጅ ሙያዎቹን ለመማር አራት ዓመታት ይፈጃል ይላሉ:: በዚህ ዓመት ለማስተ ርስ ድግሪ ማሟያው ጥናት ያካሄደው ታምራት ኃይሉ የብራና መጻሕፍት ዝግጅትን፣ ጥረዛንና ድጎሳን ጨምሮ የሥዕል ጥበብ ትምህርት እንዴት እንደሚገኙ ሲገልጽ እንደሚከተለው ነው::

> የብራና መጻሕፍት ሙያ የሚለመደው በሁለት መንገድ ነው:: የመጀመሪያው ከቤተሰብ ሲወርድ ሲዋረድ [ሲወራረድ] የመጣ ሙያ ከሆነ ልጆች ይህንኑ ሙያ ከወላጆቻቸው ሲለምዱ ሌላው መልመጃ መንገድ በግል ቤአካባቢው በዚህ ሙያ ከታወቀ ሰው ዘንድ ሄዶ በመማር ነው:: (ገጽ. ፳፰)

ጥናቱ ይህንን ትምህርት ቤት ገብቶ ስለመማር ቃለ መጠይቅ ያደረገላቸው ሰዎች መናገራቸውን ይጠቅሳል እንጂ ይህን ሙያ የሚማሩበት መደበኛ የአብነት ትምህርት ቤት መኖሩን ግን አይጠቅ ስም::

## ፫. ለዘመናዊ ትምህርት እድገትና ለሀገሪቱ አስተዳደርስ ምን አስተዋጽኦ አድርገዋል?

የረጅም ዘመን የታሪክ ባለቤት ናት የምንላት ሀገራችን ታሪኳና ቅርሷ ተ ጠ ብቆና ተመዝግቦ የምናገኘው ከነዚህ የአ ብነት ትምህርት ቤቶች በተማሩ ሰዎች ነው:: ኢትዮጵያ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ውስጥ የራሷ ፊደልና አኀዝ ባለ ቤት፣ ከሺሕ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ የራሷ የመደበኛ ትምህርት ሥርዓትና ዕውቀት ኖሯት እስካሁን ድረስ ላለነው ትውልዶች ስታስተላልፍን የኖረችው የኢ ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን በነዚህ የአብነት ትምህርት ቤቶ ችና በሊቃውንቶቿ አማካኝነት ነው::

ከጥንት ጀምሮ የመንግሥት ጸሐፌ ትእዛዛትና የገድላትና የዜና መዋዕ ላት ጸሐፊዎች ከነዚሁ የአብነት ትምህርት ቤቶች የፈለቁ ናቸው:: ዘመናዊ የመንግ ሥት አስተዳደር ወደ ሀገሪቱ በገባ ጊዜም ዘመናዊውን ቢሮክራሲ የሸፈኑትና የዘመኑ ሕግ አውጪዎች፣ አስፈጻሚዎችና ተር ጓሚዎች ይህንኑ ትምህርት በአብነት ትምህርት ቤቶች የተከታተሉ ነበሩ::

በአጠቃላይ ለብዙ ዘመናት የኢትዮ ጵያ የሰው ኃይል ምንጭ የነበሩት እነ ዚሁ የአብነት ትምህርት ቤቶች ነበሩ:: እነዚህ የሠለጠኑ የሰው ኃይሎች ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ባይገኙ ኖሮ የኢትዮ ጵያ ዘመናዊ የፖለቲካና የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት ጨርሶ አይታሰብም ነበር::

የዘመናዊ ትምህርት በተጀመረበት ወቅት ምንም እንኳን በቀጥታ ከውጪ በመጡ ሰዎች ቢጀመርም በአንደኛ ደረጃ መምህርነትና ለዘመናዊው ትምህርት የተዘጋጁ ተማሪዎችን በማፍራት ረገድ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ከዚህ ውጪ ግን በመን ግሥታቱ የፖሊሲና የአመራር ምርጫ ምክንያት በጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርትና በዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርት መካከል የሚታይ ጠንካራ ዝምድና የለም:: በሀገራችንም ዘመናዊ ትምህርት ባለፈባቸው መቶ ዓመታት ውስጥ ማስገኘት ያለበትን ጥቅም ለሀገሪቱ አላስገኘም::

## ፬. ለዘመናዊ ትምህርት ምን የሚበጅ አስተ ዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ?

በሀገራችን በ፳ኛው ምእተ ዓመት መጀምሪያ ላይ ዘመናዊ የፖለቲካ አስተዳደርና ዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ሲገባ የተደረገው ነገር ጥቂት ኢትዮጵያውያን ወደ ውጪ የአውሮፓ ሀገራት ሄደው እንዲማሩ ማድረግ፣ የውጪ ሀገር መምህራንን (መጀመሪያ የግብጽ በኋላ የእንግሊዝና የሌሎች ምዕራባውያን ሀገራትን) በማስመጣት ጨርሶ ከሀገራችንና ከባህላችን ጋር የማይተዋወቀውን ምዕራባዊ ዘመናዊ ትምህርት ማስጀምር ነበር:: ይህ ሥርዓተ ትምህርት በአውሮፓውያን ባህልና ሥርዓት የታነፀ እንጂ ለኢትዮጵያውያን ፍጹም ባዕድ ነበረ:: ይህን ባዕድ ሥርዓተ ትምህርት ከባህሉና ከጥንታዊው የትም ህርት ሥርዓት ጋር ለማዋሐድ ምንም ሙከራ ሳይደረግ እንዳለ በተግባር መዋል ጀመረ::

አንዳንድ የሀገራችን ምሁራን (አሁንም በሕይ ወት ያሉ ጭምር) የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥርዓተ ትምህርት በመኮነን፣ መመስገን ሲገባት በምትኩ ለኢትዮጵያ ኋላ ቀርነት ተጠያቂ በማድረግ ጥቅም አልባ ሲያደርጉት ይስተዋላል:: አንዳንዶቹ ጨርሶ የዚሁን ጥንታዊ ትምህርት መኖር፣ ምን ምን ይዘቶች እንዳሏቸው እንኳን ሳያውቁ የሚነቅፉ ናቸው:: አንድ ፕሮፌሰር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን እኒህ ሁሉ ሥራ የሚያስፈቱ በዓላት ያሏት ቁጥር ስለማታውቅ ነው፣ በግእዝም ቁጥር ስለ ሌለ ነው ሲሉ ሰምቼ ቁጥር መኖሩንና የሒሳብ ትምህርትም መኖሩን፣ የበዓላቱም ብዛት እሳ ቸው እንደገመቱት ሳይሆን በጣም በጣት የሚቆጠሩ መሆናቸውን ነግሬያቸው ነበር:: የሚሰያስደንቀው ነገር እኚህ ፕሮፌሰር በኢትዮጵያ ውስጥ የዩኒቨር ሲቲ መምህር መሆናቸው ነው:: ነገር ግን ከእ ንዲህ ያለ ሰው የሚቀርብ ነቀፌታ በሀገር እድገት ላይ ጭምር ከፍ ያለ አሉታዊ ተጽእና እንደሚኖ ረው ለመግለጽ ነው::

አንዳንድ የቤተክርስቲያን እርምጃዎችንም ከወ ቅቱ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር ሳያ ስተያዩ እንቅፋት እንደነበረች ይቆጥራሉ:: ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን በሚሲዮናውያን ሲጀመር የታሰበ ውን የዘመናዊ ትምህርት ቤት መከፈት በመቃ ወም በ፲፯ኛው ምእተ ዓመት አካባቢ መጀመር የሚችለው ዘመናዊ ትምህርት እንዳይጀመር እን ፋት ሆናለች ይላሉ:: ይህ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ከምታከናውነው ተግባር፣ ከዓ ላማዋና ከነበራት ቀደም ያለ ልምድ በመነሣት ይህ እርምጃ ፍጹም ትክክለኛ መሆኑን እንረዳለን::

ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያን ወደ ሥልጣኔ በመ ምራት በተለይ ትምህርትን በማ ስፋፋት መስክ ያደረገችው አስተዋጽኦ እጅግ የተወሰነ ነው በማለት ይተቻሉ:: (ኢያሌው ሺበሺ፣ ፲፱፻፹፱፣ ፴፩) ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ በነዚህ ትምህርት ቤቶች አማካኝነት ለአገልግሎት የሚያስፈልጓትን ሊቃውንት በበቂ ሁኔታ የምታስገኝ ሲሆን በተ ጨማሪም ለመንግሥት የተማረ የሰው ኃይል ስታቀርብ ኖራለች::

ሌሎች ሰዎች ደግሞ በደካማ ሥርዓተ ትም ህርቷ አማካኝነት በአጭር ጊዜ የሚ ጠናቀቀውን ትምህርት ረጅም ጊዜ እንዲፈጅ አድርጋለች የሚል ትችት ይሰነዝራሉ (ግርማ አማረ፣ ፲፱፻፷፯፣ ፫):: ይህ ግን ፍጹም ስሕተት ነው:: እነዚህን ልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች ከእጅ ሙያው ጭምር ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ዘመናዊ ትም ህርት በምንማርበት ወቅት ከሚፈጀው ጊዜ ጋር ሲነ ፃፀር በጣም ያነሰ ነው እንጂ የሚ በዛ አይደለም:: ከአሁኑ ሙያ አንጻር እንኳን ብናያቸው የዜማ ትምህርት (በሙዚቃ መመረቅ ማለት ነው)፣ በቅ ኔና በመጻሕፍት ትርጓሜ (በሥነ ጽሑፍ ሁለተኛ ድግሪና ከዚያ በላይ ከመያዝ ጋር የሚወዳደር ነው)፣ በሒሳብና በታሪክ ትምህርት እንዲሁም በሥዕልና በቅርጻ ቅርጽ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቋል ማለት ነው:: ታዲያ እነዚህን ሁሉ



www.eotcmk.org

ሙያዎች በዘመናዊ ትምህርት ከ፴ ዓመት ባነሰ ማጠናቀቅ እንችላለን? አይቻልም::

ሌላው መሠረት የሌለው ትችት በአብነት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶች የማይለወጡ፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዳሉ የሚቆዩ፣ ተማሪውም እነሱኑ አምኖ መቀበል እንጂ መመርመር፣ መተቸትና ማሻሻል የማይችል ነው ሲሉ ይተቻሉ:: ይሄ ስሕተት መሆኑን ለመረዳት የተለያዩ የቅኔ መንገዶች፣ የተለያዩ የትርጓሜ መንገዶች፣ የተለያዩ የዜማና የአቋቋም ቤቶች መኖራቸውን ማወቅ ይበቃል:: በቅኔ ቤት መም ህሮቻቸውን የሚፈትኑ ስሕተቶቻቸውን የሚያርሙ ብዙ ተማሪዎች መኖራቸውን የሚያውቅ ያውቀዋል:: የቤተ ክርስቲያንን ትምህርቶች የሚያውቅ ሰው ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ሊያቀርብ ይችላል:: በሃይማኖታዊ ትምህርት ደግሞ ከዚህ ያለፈ የዕውቀት ዳይናሚዝም አስፈላጊ አይደለም:: የቤተክርስቲያንም ሆነ የሥርዓተ ትምህርቷም ዓላማ ዕውቀትን ጠብቆ ሃይማኖትን ማስፋፋት ነው፤ ነገረ ሃይማኖት /መለኮት/ እየተስፋፋ፣ እየታደሰ የሚሄድ ነገር አይደለምና::

እነዚህን ነቀፌታዎችና ሚዛናዊ ያልሆኑ አስተያየቶች ትተን እስኪ ጥንታዊው የቤተክርስቲያን ትምህርት ለዘመናዊው ትምህርት ምን ይጠቅማል የሚለውን እናንሣ::

ዴቪድ ብሪጅስና ባርባራ ሪደሌ የሚባሉ የትምህርት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ላይ በሠሩት ጥናት ላይ እንዲህ ይላሉ:-

«ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ትምህርት ካላወቅኸው ዘመናዊውን ትምህርት ልትረዳው አትችልም» (ገጽ፣ ፪) Tradition and Modernity Educational Development & Teachers training in Ethiopia (Cambridge Education Consultants) Bridges David & Ridley Barbara.

የዓለማችንን የልማት አኪያሄድ በመመርመር ዘመናዊውን የምዕራባውያን ሥልጣኔ (በምዕራባውያን ባህል ላይ የተመሠረተና ከዚያ ባህል የመነጨውን) ምንም ወደማይተዋወቀው ሀገርና ሕዝብ ላይ በመጫን የኢኮኖሚ እድገት አያስገኝምም ይላሉ:: ከእስያ ሀገራት ውስጥ ያደጉ የሚባሉት እነ ጃፓን፣ ኮሪያና ቻይና እዚህ ደረጃ የደረሱት የምዕራባውያንን ዘመናዊ ሥልጣኔ ከባህላቸውና ከጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርታቸው ጋር በማዋሐድ ነው:: ለብዙ ዓመታት በጦርነት፣ ከሩብ ምእተ ዓመት በላይ በምዕራባውያን ማዕቀብ ሥር ስትማቅቅ የኖረችው ቬትናም በአጭር ጊዜ ወደፊት መገስገስ የጀመረችው በዚሁ መንገድ በመጓዝ ነው:: በአጠቃላይ ሀገር በቀል ዕውቀትንና ጥንታዊ የትምህርት ሥርዓትን ትቶ ዘመናዊ ትምህርትን በማስገባት ከሥልጣኔ ደረጃ እደርሳለሁ ማለት የማይታሰብ ነው:: ይህን ያደረጉ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ሀገራት አሁንም በችግር ማጥ ውስጥ ናቸው:: ሥልጣኔው ግንጥል ጌጥ፣ ባዳ ሆኖ የታሰበውን ነገር ሊያስገኝ አልቻለም:: ለዚያች ሀገር የሚስማማውን ነገር ከምዕራባውያኑ ዘመናዊ ጥበብ ውስጥ መርጦ ለማስገባት ጥንታዊው ትምህርትና ሀገር በቀሉ ዕውቀት ወሳኝ ናቸው::

ሀገር በቀል ዕውቀትንና ጥንታዊ ትምህርትን በማያከብር ዘመናዊ ሥልጣኔ ውስጥ የመጣ ጥበብ የታቀደለትን ግብ ሊያስገኝ ቀርቶ ያልታሰበ ኪሳራ ውስጥ፣ ማንነት የማጥፋት ተግባር ውስጥ ይከታል::

የተለያዩ አጥኚዎች ዛሬ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ትልቅ ድክመት አድርገው የሚያዩት ይህንኑ እንግዳ የሆነ ጋብቻ ነው::

Efforts at modernization were necessarily doomed to failure because the approach was to discard but not to fertilize domestic cultures. Development is ...possible only by developing (enriching) one's own culture and not by replacing it by alien cultures as advocated by the followers of modernization theory. (Amare Asgedome, 1989, Culture and Development, Slambau, V.5, No.1,2)

*«ሥርዓተ ትምህርቱን ዘመናዊ የማድረግ ጥረቶቹ የተሳኩ አልነበሩም፤ ምክንያቱም ጥቅም ላይ የዋለው መንገድ ሀገር በቀል ባህሉን በማዳበር ሳይሆን ዋጋውን በማሳነስ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነበር:: ስለዚህ የዘመናዊነት ንድፈ ሐሳብ ተከታዮች እንደሚሉት ዕድገት የተሳካ የሚሆነው የአንድን ወገን የራሱን ባህል በሌላ ባዕድ ባህል በመተካት ሳይሆን ያንኑ በማዳበር ነው»*

ሌላው ተመራማሪ ዶ/ር ተከስተ ነጋሽ ደግሞ የሀገር በቀልና የጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለኢትዮጵያ የወደፊት ልማት አስፈላጊ መሆኑን እንደሚከተለው ገልጾታል::

The greatest short comings of the education system in Africa and in Ethiopia in particular is that it is poorly related to and interlinked with the traditions of education which predate the coming of the modern school. The few studies available on peasant attitudes to the modern school appear to lend support to the view that and education system that fails to respect the culture of its beneficiaries will gain little respect.

At some stage Ethiopia will have to develop an education system which is closely linked with its indigenous knowledge system which have been the mainstay for the survival of its cultures and societies. (Tekeste Negash, 1996, Rethinking Education in Ethiopia, Uppsala, Nordiska Africa institute, University of Uppsala.31)

*«በአፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያ ያለው የትምህርት ሥርዓት ያሉበት ውስንነቶች የመጡት ከዘመናዊው ትምህርት መምጣት በፊት ከነበረው የቆየ የትምህርት ሥርዓት ጋር በበቂ ሁኔታ ባለመዋሐዱ ነው::*

*አንዳንድ በገጠሩ አካባቢ ያሉ ሰዎች ለዘመናዊው ትምህርት ባላቸው አመለካከት ላይ የተደረጉ ጥናቶች የተጠቃሚዎቹን ባህል የማያከብር የትምህርት ሥርዓት ለራሱ የሚያገኘው ክብር አናሳ ነው የሚለውን ይህንኑ ሐሳብ ይደግፋሉ::*

*ኢትዮጵያ ለባህሏና ለሕዝቧ ማንነት መሠረት ከሆነው ሀገር በቀል ትምህርት ጋር የተዛመደ ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓት ማበልጸግ /መቅረጽ/ አለባት::»*

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ አጋር ብቻ ሳትሆን የግድ የምታስፈልግ መሆኗንም እንደሚከተለው ያስረዳል::

A national strategy which fails to take into account the Ethiopian Church as an important partner in development will make very little headway. *(p. 37)*

*የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ዋነኛ አጋር ከግምት ያላስገባ /ታሳቢ ያላደረገ/ ሀገራዊ የልማት ስትራቴጂ አይሳካም::*

## ፰. ምን ይደረግ?

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት መከራከሪያ ነጥቦች ላይ በመነሣት የሚከተሉትን ነጥቦች መጥቀስ ይቻላል:: ከዚህ በላይ ባነሣናቸው የአብነት ትምህርት ቤቶች የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ ያሉ የሚከተሉት ነጥቦች በዘመናዊው የትምህርት ባህል ውስጥ ቢካተቱ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይሰጣሉ::

፩. በክፍል ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው ተማሪዎች ቁጥር በትምህርቱ ባህርይ እንዲወሰን ማድረግና በትምህርትና በተግባር መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ

፪. ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉትን እንዲያስተምሩ በከፍተኛ ደረጃ መጠቀም (ይህ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ተማሪዎች ቁጥር ለመቀነስ፣ አስተማሪው ተማሪም የማስተማር ልምድ እንዲኖረው ለማድረግ ይረዳል)

፫. በመምህራንና በትምህርቱ መካከል በጣም የዳበረ ትስስር እንዲኖር ማድረግ (ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን የሚመርጡት በመምህሩ ሊቅነት (አዋቂነት) ነው) የማይረባ መምህርም ተማሪ አያገኝም::

፬. አንድ ተማሪ በአደባባይ ሐሳቡን እንዲገልጽ፣ እንዲከራከርና በቀላሉ ሐሳብ

ወደ ፴፯ ገጽ ዞሯል



www.eotcmk.org

# መዝሙራችን ወዴት

ዲ/ን ማለደ ዋስይሁንና ጌታቸው በቀለ

መዝሙር እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣የሚቀደስበት፣ የሚለመንበት ዐቢይ የጸሎት ክፍል የሆነ ጣዕመ ዜማ ነው፡፡ «ለአንተ የምሥጋ መሥዋዕትን እሠዋለሁ» እንዲል /መዝ.፻፲፭፥፲፯/፡፡ ቤተክርስቲያን ስትጠቀም የኖረችው እግዚአብሔር በሰጣት ያሬዳዊ ዜማ ስለሆነ ልጆቿም ይ ንኑ ዜማ እንዲጠቀሙበት ታስተምራለች፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መዝሙሮች የምእመናን መወያየ ርእስ ጉዳይ ሆነዋል፡፡ ምእመናን ለዝግጅ ክፍላችን ስልክ በመደወል፣ ፖስታ በመላክ፣ በአካልም በመምጣት መዝሙሮቻችን ከሥርዓት ውጭ ሆነዋል፣ ሃይ ባይ ጠፍቷል የሚ ወቀሳዎችን በተደጋጋሚ ሲያደርሱን ቆይተዋል፡፡ ስለዚህ የችግሮቹን ምንጭና ዓይነት ለማሳየትና የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማመላከት እንዲረ «ስለ መዝሙር እንወያይ» የሚል መድረክ ከፈትን፡፡

## «የተጮኸ ሁሉ የያሬድ ዜማ አይደለም»



መምህር ሐዲስ ትኩነህ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የዜማና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መምህር

*ሐመር፡- ራስዎን ቢያስተዋውቁን?*

መ/ር ሐዲስ፡- መምህር ሐዲስ ትኩነህ እባላለሁ፡፡ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሥርዓተ ቤተክርስቲያንና የዜማ መምህር ነኝ፡፡

*ሐመር፡- ዜማ ምንድን ነው?*

መ/ር ሐዲስ፡- ዜማ ስልት ያለው የተቀነባበረ ድምፅ፣ ጩኸት ነው፡፡ መንፈሳዊ ዜማ ቤተክርስቲያን የምትገለገልበት፣ ካህናቱ የሚያዜሙት የሚማሩት በአብነት ትምህርት ቤት የሚሰጥ መጽሐፍም ያለው ነው፡፡ የዜማም ዓይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ ጩኸት በተባለው ዓይነት ስናየው የቅዱስ ያሬድን ዜማ ጥሬ ዜማ ወይም የድጓ /ጾመድጓ/ ዜማ አለ፡፡ አጫብር፣ ቆሜ ተብለው የሚጠሩ ትምህርት ቤት ማድረሻዎች ያሏቸው ዜማዎች አሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ዝማሬ መዋስዕት አለ፡፡ የቅዳሴ ዜማ፣ የአቋቋም ዜማም አለ፡፡ በእነዚህና በሌሎቹ የዜማ መጻሕፍት ተመሥርቶ ስፋ ብሎ በመሣሪያ የሚገለገል ዜማ አለ፡፡ እንግዲህ ከአገልግሎቱም ከስሙም ከድምፅ አወጣጡ ተነሥተን ስናያቸው ጥሬ ዜማ፣ የቁም ዜማ ወዘተ እያልን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው በሦስት ክፍል የተከፈለ በውስጡ ብዙ ክፍሎች ኖረው ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ ዜማ ተብሎ ይመደባል፡፡ ይሄ እንግዲህ በመጻሕፍት ተጽፎ፣ መምህር እያስተማረው፣ ተማሪ የሚማረው ቤተክርስቲያን እየተገለገለችበት ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዜማ ነው፡፡

*ሐመር፡- በቤተክርስቲያናችን አንድ ዜማ ያሬዳዊ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ያሬዳዊነቱንስ እንዴት ነው የምንገልጸው?*

መ/ር ሐዲስ፡- ያሬዳዊ ዜማ ማለት ቅጽሉ እንደሚያመለክተው ያሬዳዊ ሲባል ወገናዊነትን የሚያሳይ ነው፤ የያሬድ የሆነ ማለት ነው፡፡ ሃያ ሁለቱን የድጓ አርእስቶች የያዘ፣ ምልክቶች ያለበት ቅዱስ ያሬድ የደረሰው ዜማ ነው፡፡ አንድ ሰው ከመጽሐፍ ወስዶ ለአገልግሎት ካዋለው ያሬዳዊ ዜማ ይባላል፡፡ዝም ብሎ ደግሞ እሱን የሚመስል መሪ ቃል ያለው ዘሩ ሌላ የሆነም አለ፡፡ ስለዚህ ያሬዳዊ ዜማ ስንል ድምፁን ብቻ ሳይሆን መልእክትም ሊኖረው ይገባል፡፡ ዘሩ /ንባቡ/ ከሃይማኖት መጻሕፍት ከድርሳናት ተወስዶ፣ በዚያ ላይ ዜማ ተደርሶለት፣

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል

## «ማንኛውም ዜማ



ዲ/ን አሸናፊ

*ሐመር፡- በቅድሚያ ራስዎን በአጭሩ ቢያስተዋውቁን?*

ዲ/ን አሸናፊ፡- ዲ/ን አሸናፊ ገብረ ማርያም እባላለሁ፡፡ ሥራዬ ስብከት፣ ዝማሬና የመዝሙር ግጥምና ዜማዎችን መድ ረስ ነው፡፡ እስከ አሁን ፩፻፹ የሚሆኑ ግጥምና ዜማዎችን ደርሻለሁ፡፡

*ሐመር፡- ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዝማሬ የምትጠቀምበት ያሬ ዳዊ የዜማ ስልት መሆኑ ይታወቃል፡፡ አንተም ለዘማርያኑ ያሬዳዊ ዜማ እንደ ምትሠራላቸው ገልጸህልናል፡፡ ለመሆኑ ያሬዳዊ ዜማ ማለት ምን ማለት ነው?*

ዲ/ን አሸናፊ፡- ያሬዳዊ ዜማ በእኛ ቤተክርስቲያን በፎርሙላ /በቀመር/ የሚ ቀመጥ አይደለም፡፡ በሥነ መለኮት ትም ህርት ቤት ስለ ዜማ ስንማር ያሬድ የዜማ አባት ነው ድንጋይና ድንጋይ ሲፋጭ እንኳን የሚወጣው ድምፅ ከያ ሬድ ዜማ የሚወጣ አይደለም፡፡ የሚል ትምህርት ወስደናል፡፡ ስለዚህ ያሬዳዊ ዜማ እንዲህ ዓይነት መልክ አለው ብሎ መናገር ይከብዳል፡፡ ነገር ግን የእኛ ቤተ ክርስቲያን የያሬድን ዜማ ስልት ለቅዳ ሴው፣ ለሰዓታቱ፣ ለማኅሌቱና ለውዳሴ



www.eotcmk.org

# እያመራ ነው?

ምእመናንም የመዝሙራቱን አስተዋጽዖ አስመልክቶ፣ የትኞቹ ሥርዓት ጠብቀዋል? ክፍተቶች የተፈጠሩትስ የት ነው? ወደፊት መደረግ ያለበት ምንድን ነው? በሚሉ ጥያቄዎች ላይ የተጻፉ አስተያየቶችን በተከታታይ እትም ማስተናገዳችን ይታወቃል። በዚህ ጽሑፋችንም መልካሙን ማበረታታት፣ የደከሙትን ማጠንከር፣ የጠመመውን ማቅናትና መልክ እንዲይዝ መጠቆም በቤተክርስቲያናችን የነበረና ያለ ትውፊት በመሆኑ በዚህ በኩል የሚመለከታቸውን አካላት አስተያየት ማካተት ወሳኝ ሆኖ አግኝተነዋል። በትድሚያ ግጥምና ዜማ ከሚያደርሱት መካከል ዲ/ን ቢጋሻው ደሳለኝና ዲ/ን አሸናፊ ገ/ማርያምን አስተያየት እንዲሰጡን ጠይቀን ዲ/ን ቢጋሻው ፈቃደኛ ባይሆንም ዲ/ን አሸናፊ ገ/ማርያም ለዚህ ቃለ ምልልስ ተባባሪ ሆኗል። በመሆኑም የእርሱንና የዜማ ሊቃውንቱን ቃለ ምልልስ አዘጋጅተናል። ጊዜያቸውን ሰውተው በትግሩ ዙሪያ ግልጽ አስተ

## የያሬድ ነው»



ገብረማርያም ዘማሪ

ማርያም... ዜማ በስልት እያዘጋጀች ለአገልግሎት ትጠቀምበታለች።


*ሐመር፦ አንዳንድ ዘማርያን አራቱን ቅኝቶች አምባሰል፣ ትዝታ፣ አንቺሆዬና ባቲን የያሬድ ናቸው ይላሉ። የአንተ አስተያየት ምንድን ነው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ አስቀድሞ እንዳልኩት የድንጋይና የድንጋይ ጩኸት /ድምፅ/ እንኳን የያሬድ ከሆነ እነዚህ ቅኝቶች አምባሰል፣ ትዝታ... የያሬድ አይሆኑም አይባልም። አንቺ ሆዬን ቅኝት ስመለከት በእኛ ቤተክርስቲያን ግእዝ የሚባለው የዜማ ስልት ነው። ግእዝ ዜማ ሲዜም አንቺ ሆዬና ትዝታ ቅኝቶች በውስጡ ይገኛሉ። ስለዚህ የያሬድ ዜማ እነዚህን ቅኝቶች ጠቅልሎ የያዘ ነው። ዓለም በራሱ እንዳመቸው አድርጎ ባቲ፣ ትዝታ፣ አንቺ ሆዬ ብሎ ፎርሙላ አውጥቶለት እየተጠቀመበት ይሁን እንጂ ቅዳሴያችን አራቱንም ቅኝቶች ይዞ እናገኛለን። ስለዚህ ማንኛውም ዜማ ከሰማይ በታች ያለው ሁሉ የያሬድ ነው፤ ከያሬድ ዜማ አይወጣም።

*ሐመር፦ ዜማ ስታዘጋጅ መስፈርትህ ምንድን ነው? እነዚህን መሠረት*

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል

## «ሁሉም ዜማ የያሬድ ነው ማለት አይቻልም»



መምህር በየነ ድንቁ ዜማና ግጥም ደራሲ

መምህር በየነ ድንቁ በጎንደር፣ በላስታ የዜማ፣ አቋቋም ትምህርት ተምረዋል። በላስታ ቅዱስ ላሊበላና በተለያዩ አውራጃዎች የዐሥር አብያተ ክርስቲያናት ሊቀ ዲያቆን በመሆን ፲፮ ዓመት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል። ከመንፈሳዊ ትምህርት በተጓዳኝም በአዲስ አበባ ዘመናዊ ትምህርታቸውን ተከታትለው ከእንጦጦ አጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት በአካውንቲንግ በዲፕሎማ፤ ከአድማስ ኮሌጅ በማኔጅመንት በሰርተፊኬት ተመርቀዋል። በአሁኑ ወቅትም በአልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጂ የሕግ ፫ኛ ዓመት ተማሪ ናቸው።

መ/ር በየነ በአብዛኛው በግጥምና ቅኔያት፣ መወድሶችን በማቅረብ ይታወቃሉ። በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም በተምሮ ማስተማር የሰንበት ትምህርት ቤት በ፲፱፻፸ዎቹ የነበሩ አባላትን ያሬዳዊ መዝሙር በማስጠናት፣ የኦርቶዶክሳዊ ሥነ ጽሑፍ አጻጻፍ ሥልጠናዎችን በመስጠት ለሰ/ት/ቤቱ መጠናከር ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል። የንስሐና የሰርግ መዝሙር በካሴት አዘጋጅተው ለተምሮ ማስተማር ሰንበት ት/ቤት አበርክተዋል።

ከዚያም በኋላ ሃያ ለሚሆኑ መዘምራን ዜማና ግጥም እየደረሱ ሰጥተዋል። በተለይም ለማርታ ኃ/ሥላሴ በሕዝብ ዘንድ እንድትታወቅ ያደረጋትን የመጀመሪያውን ካሴት ሠርተዋል። ለሊቀ መዘምራን ኪነ ጥበብ ወ/ቂርቆስ የስድስቱን ካሴት ሙሉ ዜማና ግጥም አዘጋጅተው ሰጥተዋል። እነዚህ ለአብነት የሚታወቁባቸው ሥራዎቻቸው ናቸው። በአሁኑ ወቅትም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የፐርሶኔል ጉዳዮች ሓላፊ ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። በሥራዎቻቸውና በአሁኑ ወቅት ያለገደብ እየወጡ ባሉት በርካታ የመዝሙር ካሴቶች ዙሪያ አነጋግረናቸዋል።

*ሐመር፦ በአሁኑ ወቅት አንዳንዶች በዓለም ላይ ያሉ ዜማዎች ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ናቸው ይላሉ። እርስዎ የያሬድን ዜማ እንዴት ይገልጹታል?*

መ/ር በየነ፦ ዜማ ሁሉ የያሬድ ነው ልንል አይገባም። ሁሉም የያሬድ ነው ማለትም አይቻልም። የያሬድ ዜማ ደግሞ ከሦስቱ /ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ/ የወጣ አይደለም። ካልሆነማ መናፍቃንስ ይዘምሩ የለም እንዴ? የምንለየው እኮ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.eotcmk.org

## «የተጮኸ ሁሉ ...»

ከገጽ ፲፬ የዞረ

መልእክት ያለው የስማዕታትን፣የነቢያትን በዓላት የምናከብርበት ዜማ ከሆነ ያሬ ዳዊ ዜማ ይባላል::

*ሐመር፦ ዛሬ ቤተክርስቲያን ለዝማሬ የያሬድን ዜማ እንደምትጠቀም ይታወቃል:: በሌላ በኩል ደግሞ የዜማ ድርሰት የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ:: ታዲያ የሰዎቹ የዜማ ድርሰት ከያሬዳዊው አንጻር እንዴት ሊታይ ይችላል?*

መ/ር ሐዲስ፦ ሌላ ሰው የደረሰው ዜማ ከሆነ መባል ያለበት የሰውየው ዜማ ነው:: ከያሬድ የተወሰደ ከሆነ የያሬድ መባል አለበት:: ነገር ግን መልእክቱም ዜማውም ሌላ ከሆነ ያሬዳዊ መባል አይችልም:: ነገር ግን አስመስሎ መድረስ ሊኖር ይችላል:: ለምሳሌ ከአቋቋሙ ወረብ የሚባል ዜማን መስሎ ንባቡ «መልክእ» ሊሆን ይችላል:: ንባቡ ሌላ ሆኖ ዜማው ግን የያሬድን መስሎ መምህራን የደረሱት አለ:: እንዲህ ያሉትን ዜማዎች አዋልድ ዜማዎች እንላቸዋለን:: ከእነዚያ የወጡ እንደማለት ነው፤ አዋልድ መጻሕፍት እንደሚባለው ማለት ነው:: ዋናው የቅዱስ ያሬድ ሆኖ እነዚያ ግን አዋልድ ድጓዎች ይባላሉ:: በንባብ ሌላ ሆነው በዜማ ከያሬድ ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው::

አሁን ለምሳሌ አርያም የሚባል አለ:: የቃል ትምህርት ድርሰቱ የሰኞ፣ የማክሰኞ... አለ፤ ብዛትም አላቸው:: ዘሩ ከሌላ መጥቶ ዜማው ግን የያሬድን ይመስላል ያሬድን የሚመስል ስለሆነ በዜማው ተመሳስሏልና አዋልድ ዜማ ነው:: ያሬዳዊ ሲባል ያሬድ የደረሰው በመጽሐፍ ካለው በቀጥታ መወሰድ አለበት:: እኔ ወረብ ብደርስ የእኔ ነው የሚባለው እንጂ የመምህር እከሌ አይባልም::

*ሐመር፦ አዋልድ ዜማዎችን በያሬድ የዜማ ምልክቶች መለካት /መሥፈር/ አይቻልም?*

መ/ር ሐዲስ፦ የያሬድ ዜማ ይመስላል ስንል የያሬድ ዜማ ልክ አለው፣ ስም አለው፣ መነሻ አለው መድረሻ አለው:: እሱን አስመስሎ ከዚያ ንባብ ልክ ምልክቶችን አስገብቶ መጠቀም የሚቻልበት ነው:: ንባቡ ድርሰቱ ምንም እንኳ የሌላ ሰው ቢሆንም፤ ዜማውን ስለሚመስል አዋልድ ዜማ ነው:: አዋልድ ድጓ እንደሚባለው ማለት ነው::

ከያሬድ በኋላ የተነሡት አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ እነ ወለተ ጴጥሮስ... እዋልድ ድጓ አላቸው:: ቅዱስ ያሬድ ስለራሱ ክብረ በዓል አልደረሰም:: ደርሶ ያለፈው ለሌሎች ነው:: ቤተክርስቲያን ቅዱስ ያሬድን የምታከብርበት፣ ወረታውን የምትመልስበት፣ የምታስብበት ለቅዱስ ያሬድ የኋላ ሰዎች የደረሱት አዋልድ ድጓ አለ:: የጎደለ ለመሙላት ንባቡን ሰዎች ይደርሳሉ፣ ዜማውን የያሬድን አስመስለው ስለደረሱት የያሬድ ባይሆንም ያሬዳዊ ማለት ይቻላል:: ደራሲው ማነው ሲባል ያ የደረሰው ሰውዬ ስም ቢጠራ ጥሩ ነው:: አሁን የሚደረሰውን የአማርኛ መዝሙር ስንመለከተው ከያሬድም፣ ከአቋቋሙም ካልሆነ የያሬድ ዜማ ሊባል አይቻልም:: ዘሩ ጎድሎ ያሬድ ሳያሟላው ቀርቶ ቢሆን ካሉት አርእስተ ድጓዎች፣ ከስያሜዎች ያን አስመስሎ ዘሩን ከዘሩ፣ ዜማውን ከዜማ አስመስሎ መድረስ ይቻላል:: ስለዚህ የያሬድ ዜማ ሊቃውንቱ የሚያውቁት ግልጽ መለኪያዎች አሉት::

*ሐመር፦ ሁሉም ዜማ የያሬድ ነው የሚሉ ሰዎች አሉ:: በዚህ ላይ የእርስዎ አቋም ምንድን ነው?*

መ/ር ሐዲስ፦ ማንኛውም ጩኸት ከቅዱስ ያሬድ አይወጣም ማለት፤ ወፍም ይጩህ አንበሳ፤ በዜማ ሲተመን ፍፁም ለሆነችው ነጠላ ድምፅ ከግእዝ፣ ከዕዝል ወይም ከአራራይ አቻ /የሚመሳሰል አና ጣለት ይሆናል ወይም አራተኛ አይኖረውም ማለት ነው:: የማንኛውንም ሰው ድምፅ ብናይ ከእነዚህ ከሦስቱ አይወጣም:: ከግእዝ፣ ከዕዝል ወይም ከአራራይ ማለት እንጂ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው ዜማ በየሰው አፍ አለ ማለት አይደለም:: ዜማ አስቀድመን እንደገለጽነው የተቀናበረ በስልት የሚወጣ እንጂ ነጠላ ድምፅ ሁሉ ዜማ ነው ብንል አያስማማም:: ፍጡር የሆነ ሁሉ የሚያሰማው ድምፅ የያሬድ ነው ማለት አይደለም:: የዓለሙ ጩኸት ዓይነቱ ሦስት ነው እንጂ አራተኛ የለውም ማለት ነው:: ሦስት ናቸው ሲባል አንዱ ብቻ በሺሕ የሚቆጠር ዓይነት አለው:: አንዱ ብዙ ነው፤ በዚህም ምክንያት ነው የሌላውን ድምፅ ሁሉ መተካት የሚችለው::

ጌታችን የፈጠረው የማንኛውም ፍጥረት ወፎች፣ ዝንጀሮዎች፣ ውሾችም... ቢሆኑ ድምፅ አላቸው:: የውሻው ድምፅ ያሬድ የሰጠው አይደለም ወይም ደግሞ ውሻው ለያሬድ አስተምሮት አይደለም:: ነገር ግን ከያሬድ መጽሐፍ ከፍለው የተቀመጡ ብዙ ግእዞች በአንድ ዜማ የሚጠሩ /አንድ የተቀናበረ የግእዝ ዜማ የሚሠሩ/፣ ብዙ አራራይዎች በአንድ አራራይ ስም የሚጠሩ /አንድ የተቀናበረ የአራራይ ዜማ የሚሠሩ/፣ ብዙ ነጠላ የዕዝል ድምፆች በአንድ ዕዝል ዜማዎች የሚጠሩ ሲሆኑ እነዚህን ሰብስበን

ወደ ፲፰ ገጽ ዞሯል

## «ማንኛውም ዜማ ...»

*አድርገህ ነው የምታዘጋጀው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ ዜማዎችን ሙዚቃዊ ይዘት እንዲኖራቸው ወደ ጭፈራ ሊያመሩ በሚችሉ መንገዶች አድርጎ መቅረጽ ይቻላል:: ከዚያ ውጭ ደግሞ በተመስጦና በንስሐ ውስጥ ሆነው ሰዎች እንዲያዜሟቸው አድርጎ መቅረጽ ይቻላል:: አሁን ብዙ ጊዜ መዝሙር ስሠራ በተመስጦና በምስጋና ሆኖ እንዲዘመር ነው:: ሰው በተረጋጋ መንገድ ወደ ልቡ እንዲገባ የሚያደርጉ የሚያሳዝኑ፣ የሚያራሩ ዜማዎችን እንጠቀማለን::

*ሐመር፦ ያሬዳዊ ዜማ የሚጠቀሱ መስፈርቶች ከሌሉት፤ ሁሉንም ዜማ ቤተክርስቲያናችን ለምን አትጠቀምበትም?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ በእርግጥ ዜማዎችን ስናዘጋጅ ወሰን፣ የራሳቸው ስልትና አቀራረጽ አላቸው:: በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ዕለት በዕለት የምንጠቀምባቸው ዜማዎች አሉ:: እንደዚሁም በመዝሙር አገልግሎት ላይ ያሉትን ስናይ የያሬድ ዜማ ቀመሩ ወይም ፎርሙላው ምን እንደሆነ እኔ አላውቀውም::

*ሐመር፦ ዜማዎች ወሰንና የሚዘጋጁበት ስልት ካላቸው፣ አንተ ደግሞ ቀመሩን አላውቀውም ካልክ በምን እየለየህ ትሠራለህ?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ በስሜቱ ታውቀዋለህ አንድ ጊዜ አንድ ወንድሜ ስለ መዝሙር ሲያወራልኝ «አንድ የሆነ ሰው ተመርቆ ፓርቲ ተዘጋጅቶ ተጠርቼ ሔድኩ፤ በጣም የሚያስጨፍር ዜማ ከፍተውልን ጨፈርን፤ ከዛ መሐል ላይ ተሳስተው ሊሆን ይችላል የይልማን መዝሙር ጨመሩት ያን ጊዜ እንዳለ አዳራሹ ጸጥ አለ:: ከዛም የመዝሙሩን ኃይል አየሁ::» ብሎ ነግሮኛል:: ይኼ ነው፤ አታውቀውም፤ ቀመሩ ምን እንደሆነ አታውቀውም:: በእርግጥ ሊቃውንቱ በበለጠ ሊያውቁት ይችላሉ::

*ሐመር፦ ታዲያ ሊቃውንቱ የሚያውቁት ቀመር ካለ አንተ ግጥምና ዜማ ስትደርስ ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን የወጡ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ የምታደርገው እንዴት ነው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ ግጥምና ዜማ ስሠራ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ለመጠበቅ ዜማውን ከአዘጋጀሁ በኋላ በቅርብ ለማገኛቸው የዜማ ሊቃውንት መሪጌቶች አሳያቸዋለሁ:: በአብዛኛው የማሳያቸው ሊቃውንት ሥራዬን ጥሩ ነው ብለው ነው የሚያሳልፉት:: በኋላ ተዘጋጅቶ ለሕዝቡ ሲቀርብ ነው የተለያዩ አስተያየቶችን የምንሰማው:: እነዚህ አስተያየት የሚሰጡ በዓለም ያሉ ሰዎች፤ የተለያዩ ዘፈኖችን ሲሰሙ የኖሩ ናቸው:: ከዚያ ጋር

# መዝሙራችን ወዴት





www.eotcmk.org

ከገጽ ፲፰ የዞረ

# «ሁሉም ዜማ...»

ከገጽ ፲፰ የዞረ


እየመዘኑት ያመሳስሉታል፤ ሌላው ይጥለዋል፤ አንዱ ያሳልፈዋል፤ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች አሉ።

*ሐመር፦ ያሬዳዊ ዜማ ወሰን ከሌለው መናፍቃን በተለያዩ ቋንቋዎች በጉራጊኛ፣ ትግርኛ... ስልት እግዚአብሔርን እየመሰገንን ነው ይላሉ። ታዲያ የእኛ መዝሙሮች ወደዚያ እየሔዱ አይመስልህም?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ የመናፍቃንና የእኛ አካሔድ የተለያየ ነው። እኛ በራሳችን ዜማ ነው የምንሠራው። አባቶች ሊቃውንቱ ዜማውን በተለያየ ቋንቋ መሥራት ካለባቸው ሊሠሩ ይችላሉ። በሐመር ቋንቋ አጥንተው ዜማ ሠርተው ሕዝቡን አስተምረው ማጥመቅ ካለባቸው ሊያደርጉት ይችላሉ። እስካ አሁን ግን አልተደረገም፡ በአንድ ወቅት የጋምቤላ ብሔረሰብ ተወላጆች ማኅበረ ቅዱሳን ሊያስተምራቸው አምጥቷቸው ነበር። በዚያን ወቅት ጴጥሮስ ወጳዉሎስ ቤተክርስቲያን ሲዘምሩ አይቻለሁ። የዘመሩት መዝሙር ያሬዳዊ ነው? የዘመሩት በራሳቸው ቋንቋ ነው፤ ትክክል ናቸው። አንድ ጊዜ ቅዱስ አባታችን ጋምቤላ ሔደው በነበረበትም ወቅት እዚያ ነበርኩ፤ የአኙዋክና የኑዌር ተወላጆች ከበዋቸው ይዘምሩላቸው ነበር። ዜማው ያሬዳዊ አይደለም፤ ነገር ግን በተሰጣቸው ስጦታ ሲያገለግሉ አይተናል።

*ሐመር፦ ሁሉም ዜማ የያሬድ ከሆነ ለምንድን ነው በእርሱ ስም የሚሰየመው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ የያሬድ ዜማ ለያሬድ የተሰጠው ቃል ኪዳን ነው። ዳዊት ልበ አምላክ መባል ተሰጥቶታል፣ ያሬድ ደግሞ የዜማ አባት ተብሏል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮችን ስናይ ማንም የዜማ አባት የተባለ የለም። የቆሬ ልጆች፣ የአሳፍ ልጆችን ዳዊት እያሰለፈ የሚያዘምራቸው ነበሩ። ነገር ግን የዜማ አባት አልተባሉም። የዜማ አባት የተባለው ያሬድ ነው። በተሰጠውም ቃል ኪዳን የትኛውም ዜማ



*የማኅበረ ሰላም የመዝሙር ልዑካን በአገልግሎት ላይ*

በያሬዳዊ ዜማ ነው። ከዚህ ውጭ ከሆነ ዘፈን ነው። ዘፈን ደግሞ የሰውን አእምሮ ዓለማዊ ወደ ሆነ ነገር የሚለውጥ ነው። ስለዚህ ዘፈንና የያሬድ ዜማ ይለያያሉ። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ምልክት አለው። ከእነዚህ የወጣ ያሬዳዊ አይደለም።

ያሬዳዊ ማለት ድጓውን፣ ጾመ ድጓውን፣ መዋስዕቱንና ምዕራፍን የሚጠቅስ ነው። የያሬድ ዜማ ባሕር ነው። እያንዳንዱ ዜማ በሰፊው አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ከዚህ የተቀዳ መሆን አለበት። ስለዚህ ዜማ ስናዘጋጅ ዘሩን ከመጽሐፍ ቅዱስ ዜማውን ከሰዓታቱ፣ ከጾመ ድጓው፣ ከመዋስዕቱ ከቅዳሴው መውሰድ እንችላለን። ስለዚህ ዜማው ወሰን አለው። ከያሬድ ውጪ መውጣት የለበትም። ወሰኑ ምንድን ነው? ያልን እንደሆን መጻሕፍቶቹ በምልክት ተቀምጠዋል። ከእሱ እየዛቅን መውሰድ እንችላለን። ቀመሩ/ፎርሙላው/ ለዚያ ዜማ የተዘጋጀ

ዜማውን ከያሬድ እንዲያወጡለት አድርጎ ቢወስድ ጥሩ ነው። ትልቁ ነገር ዜማና ግእዙን አስተባብሮ ማወቅና መልመድ ያስፈልጋል።

*ሐመር፦ አምባሰል፣ ትዝታ፣ አንቺ ሆዬ.. የሚባሉ ቅኝቶች የያሬድ ናቸው የሚሉ አሉ. . . ይህ እንዴት ነው?*

መ/ር በየነ፦ አምባሰል፣ ትዝታ፣ ... የሚሉ ቅኝቶችን ያወጡት የሙዚቃ መሣሪያ ለመጫወት የፈለጉ ናቸው። ቅኝቶቹ ለዘፈን የተያዙ ነገሮች ናቸው። የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾች ጋር አብረን ተቀምጠናል። አንድ የመዝሙር ዜማ ከተሰጣቸው በእነዚህ ቅኝት ይቃኙልሃል። አዚምልን ብለው ሲዜምላቸው ይሄ አምባሰል... ነው ይሉሃል። መዝሙሩን ለሙዚቃ መሣሪያው እንዲያመቻቸው አድርገው ይቃኙታል። የመዝሙሩን ዜማ ለመሣሪያ ጨዋታ እንዲያመቻቸው ሲያጠጋጉት ወደ እነዚያ ቅኝቶች ተገዶ ይሳባል። ረጅም ርክርክ ያለውን ግን አይከተሉህም። አሁን ቅዳሴውን ልከተል

'

www.eotcmk.org

# «የተጮኸ ሁሉ ...»

ከገጽ ፲፮ የዞረ

የማንኛውንም ጩኸት ስናወዳድረው ሦስት ብቻ ነው ማለት ነው::

*ሐመር፦ ይኸ ሁኔታ ከያሬዳዊ ዜማ ውጭ ለሆኑት ዜማዎች ያሬድን እን መስላለን ለማለት መንገድ የሚከፍት አይሆንም?*

መ/ር ሐዲስ፦ አይሆንም:: የያሬድ በመጽሐፍ ተጽፎ አለ፤ የዜማ ምልክቶች አሉት፤ መልእክቱም ሌላ ነው:: እነዚያ ምልክቶቹ ከመጽሐፍ የተጻፉትን ካልመሰለ፣ መልእክታቸው ከዚያ የተቀዳ ካልሆነ /ገጽ አለው፣ ስምም አለው/፣ ያንንም አስመስለው ካልወሰዱ ያሬዳዊ አይደለም:: አሁን የሚዘፈነው በአብዛኛው አንድ ዓይነት ነው:: ቤት የለውም ያሬድ እኮ ምልክት ብቻ ሳይሆን ወገን አለው:: ሌላ ዜማ አድርገው፣ ከደረሱ የያሬድ ነው ማለት አይቻልም:: መልእክቱንም ዜማውንም ካልያዘ የያሬድ ነው ማለት አይቻልም::

*ሐመር፦ በአሁኑ ወቅት በገበያ ላይ ስላሉት ዜማዎች ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?*

መ/ር ሐዲስ፦ የቅዱስ ያሬድ ዜማ መንፈሳዊ ዜማ ነው:: የሚዘመርበትም ጊዜ አለው:: መልእክቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተያያዘ፣ እግዚአብሔር የሚገለገልበት ዜማ ነው:: መልእክቶቹን በዶግማ፣ በታሪክና በጸሎትም ስንተምነው ትልቅ ዋጋ ያለው ነው:: እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት የቅዱስ ያሬድ ድጓ ከዓመት እስከ ዓመት የሚባልበት ወቅት አለው:: ከዚህ ውጪ ደግሞ ዘሩን ሌሎች ደርሰውት በእኛ ቤተክርስቲያን ቅዳሴያት ዓይነት ሊያዘጋጁ ይችላሉ:: ለምሳሌ የቅዳሴያት ዘሮቹን ስናይ ድርሰቱ በሌሎች ሲሆን ዜማው ግን ያሬዳዊ ነው:: ውዳሴ ማርያም ድርሰቱ የቅዱስ ኤፍሬም ሲሆን ዜማው የቅዱስ ያሬድ ነው:: እንደዚህ የመሰሉ ዘሩን ራሳቸው ደርሰው ዜማ የሚያዘጋጁ ድርሰታቸውንም በቅዱስ ያሬድ ዜማ ላይ ምልክት አበጅተው የሚያዘጋጁቸው ፳፱ የድጓ አርእስቶች አሉ:: ይህ ንባቡ የእነርሱ ሆኖ ዜማው የቅዱስ ያሬድ ሆኖ ልክ ጠብቋል እንላለን:: ነገር ግን ከሁሉም የሌለ ከሆነ ከዘፈን አይለይም::



ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ

የቅዱስ ያሬድን ዜማ ሳይማሩ ያን አስመስሎ መድረስም አይቻልም:: አሁን ያሉትን መዝሙሮች የሚዘምሩ ዘማርያንን ስናዳምጣቸው አንዳንዶቹ ድምፅም የላቸውም፤ የግድ እንጂ:: የሚወገዱ ድምፆችን እንኳ ማስወገድ አልቻሉም:: ከዘፈን ያልተለየ ሆነው የምታገኛቸው አሉ:: የቅዱስ ያሬድን አስመስለን ደረስን ብለን ስናስተያየው አንድ ካልሆነ ምኑ ነው የያሬድ የሚሆነው? የያሬድ ስንል ልኩ መጠበቅ አለበት፤ ቤት አለው፤ ምልክት አለው፤ ስያሜ አለው፤ ወገን አለው::

*ሐመር፦ በገበያ ያሉትን መዝሙራት ለመለካት ሞክረዋቸው ያውቃሉ?*

መ/ር ሐዲስ፦ እሰማዋለሁ፤ እይልን ያሉኝም አሉ:: የምለካው መልእክቱ ምንድን ነው የሚለውን ነው:: ድርሰቱ ከያሬድ ጋር ሳይተዋወቅ፣ ዜማ ሳይማር የያሬድን ደረስኩ ማለት አይቻልም:: በማያውቀው ነገር የትኛውን አልኩት ይላል:: የደረሰው ምንድን ነው? መወድስ ነው? ጾመ ድጓ ነው? ስብሐተ ነግህ ነው? ሳይማር ያን ማድረግ አይችልም:: ስለዚህ አተኩሬ የማየው መልእክቱን ዘሩን እንጂ ዜማውን አይደለም::

የቅዱስ ያሬድ ዜማ እጥር ያለ ነው:: የቅዳሴውን ዜማ ስናይ ግን ሊቃውንቱ በርክርክ አስረዝመውታል:: ምልክቶቹ ያው አንድ ናቸው:: በአንድ ምልክት ላይ አምስት ዜማ ሊኖር ይችላል:: ከዚያ ከወጣ፣ ያን ካልመሰለ፣ መልእክቱም ሌላ ከሆነ ሰውዬው ያቀነባበረው ነው የሚሆነው::

*ሐመር፦ ዘማርያኑ ግጥምና ዜማዎቻቸውን ለሊቃውንት አሳይተናል ይላሉ፤ በእርስዎ ዕይታ መዝሙራቱን ሲያደምጧቸው ሊቃውንቱ አይተዋቸዋል ማለት ይቻላል?*

መ/ር ሐዲስ፦ መጀመሪያ ለማረስ በሬ መጥመድ ማወቅ አለባቸው:: ከዚያም ከሚያርሰው ጋር አብሮ መሥራት ያስፈልጋል:: ዘማርያኑ ያን ለማስመሰል መጣር አለባቸው፤ መዝሙሮችን አሳይተናል የሚሏቸው አባቶች ማርያምን የሚያመሰግን ከሆነ ሃይማኖቱ ያልተፋለሰ መሆኑን፣ ጊዮርጊስን የሚያመሰግን ከሆነ ከገድሉ ጋር አብሮ መሔዱን ሊነግሯቸው ይችላሉ እንጂ ዜማው ከቅዱስ ያሬድ ጋር አብሮ መሔዱን ግን የሚነግራቸው መምህር ያገኙ አይመስለኝም:: ካልሆነ ግድ ምሰል ቢሉት እሺ አይልም::

*ሐመር፦ በዜማ ላይ ቤተክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት?*

መ/ር ሐዲስ፦ መፍትሔ የሚሆነው የቅዱስ ያሬድን ዜማ መጽሐፍ ማጥናት ነው:: ለምንደርሳቸው ድርሰቶች ከሌላ ከወሰድን ስሙን ያሬዳዊ ማለት የለብንም:: ቅዱስ ያሬድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አንድ የሆነ፣ ምስጋናው ለእግዚአብሔር የሆነ፤ ለበዓላቱም ለአጽዋማቱም ወቅታዊ የሆኑ ዜማዎች አሉት:: በአሁኑ ወቅት የሚዘመሩት መዝሙራት ግን ወቅትም ቀንም የላቸውም፤ እንደፈለጉ ነው የሚዘምሯቸው:: ያሬድ ግን የክረምቱን፣ የሰንበቱን፣ የመስቀልን፣ የዕርገትን፣ የጾምንም፣ የልደትንም ነክቶ ነው ድጓው የተጻፈው:: ስለዚህ ዘማርያኑ ይህን

*ወጣቶቹም የያሬድን ዜማ በትንሽ በትንሹም ቢሆን ምልክቶቹን ማጥናት አለባቸው:: የሚደርሱትን መዝሙርም የያሬድን ሳይዙ የያሬድ ነው ማለት ቢተው፤ ሌላ ከሆነ ሌላ ደራሲ አለው ቢባል ጥሩ ነው::*

ወደ ገጽ ፴፺ ዞሯል



www.eotcmk.org

# ...ኢትዮጵያ ትሴብሕ ወትዜምር ግብጽ...

## የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያናት አዲሱ የግንኙነት ዘመን

ዲ/ን ሚለደ ዋስይሁን


*ባለፈው በሐመር ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፩ እትማችን በግብጽ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል በአዎንታና በአሉታ የሚገለጹ የግንኙነታቸውን ነጸብራቆች ማቅረባችን ይታወሳል:: በዚህ እትም ደግሞ ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በአዲስ መልክ ሊገለጹ የሚችሉ ማለትም ኢትዮጵያውያን አባቶች የጵጵስና መዓርገ ክህነት ማግኘት ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ያሉትን የግንኙነቶቻቸውን መገለጫዎችና የተፈረሙ ፕሮቶኮሎችን ይተነተናሉ::*

ኢትዮጵያ ከራሷ ወገን ጳጳሳት እንዲሾሙላት ያደረገችው እልህ አስጨራሽ ትንቅንቅ መደምደሚያ ያገኘው በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ነበር:: በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ልዑል አልጋወራሽ በነበሩት ተፈሪ /በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ/ ከፍተኛ ጥረትና በግብጹ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ ፲፱ኛ አማካኝነት አዲስ የግንኙነት ዘመን ተፈጠረ፤ ይህም ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶስ የመሆን ዕድል ያገኙበት ነበር::

ከዚያም ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትና አንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ ካይሮ ላይ ተሾሙ:: በዚህ ጊዜ የተሾሙት ኢትዮጵያዊ ጳጳሳት አቡነ ጴጥሮስ/መምህር ኃይለ ሚካኤል/፣ አቡነ አብርሃም /መምህር ደስታ/፣ አቡነ ይስሐቅ/ መምህር ወ/ኪዳን/ና አቡነ ሚካኤል /መምህር ሐዲስ/ ነበሩ:: ከዚሁ ጋር ተያይዞም የግብጹ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ለጉብኝት ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅትም ለጵጵስና ተመርጠው ነገር ግን ባጋጠማቸው የጤና ችግር ወደ ካይሮ መሔድ ያልቻሉትን እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን አቡነ ሳዊሮስ ብለው አዲስ አበባ ላይ ሾሟቸው:: የግብጽ ቤተክርስቲያን ኢጲስ ቆጳሳትን ከኢትዮጵያውያን ብትሾምም የሊቀ ጵጵስና ሥልጣኑን ግን እንደያዘች ቆየች::

የኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረር ግን አንድ ታላቅ የታሪክ አጋጣሚ ፈጠረ:: ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ልጆቻቸውን በትነው ሞሶሎኒን በማነጋገር ሰበብ ሀገራቸው ገቡ:: ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ለመንጋቸው ራሳቸውን አሳልፈው ሲሰጡ /አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል/ ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ ግን ለኢትዮጵያውያን ደስ የማያሰኝ ሽሽት ውስጥ ገቡ::

በዚህ ምክንያት ከነጻነት በኋላ ቤተ መንግሥቱና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቤተክህነት ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ እንዲመጣ እንደማይፈልጉ ገለጹ:: ለዚህም መነሻው የኢትዮጵያ ገዳማት መምህራንና ሊቃውንት የየአድባራቱም አለቆች በአዲስ አበባ ጉባኤ አድርገው ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ በጦርነቱ ምክንያት ኢትዮጵያን ትተው በመሔዳቸው፣ በችግሩም ምክንያት ኢትዮጵያ ከእስክንድርያ ጋር ለመገናኘት ባለመቻሏ፣ ኢትዮጵያም ያለ ጳጳስ ቆይታ በካቶሊካውያን መዳከም ስለሌለበት፣ ከነበሩት አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሦስቱ ዐርፈው የቀሩት ሁለቱ ብቻ /አቡነ አብርሃምና አቡነ ይስሐቅ/ በመቅረታቸው፣ አቡነ ቄርሎስም ወደ ሮም ሲሔዱ አቡነ አብርሃምን ወክለው የሔዱ መሆናቸውን ከማምት በማስገባት አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ /ሜትሮፓሊታን/ እንዲሆኑ መረጧቸው::



*በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና በቤተ መንግሥቱ መልእክተኞች መካከል የተደረገ ውይይት*

አቡነ አብርሃም ከተመረጡም በኋላ አምስት ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ሾሙ:: አቡኑ ጳጳሳትን መሾማቸው በግብጽ ተሰምቶ ሲኖዶሱ ውግዘት ቢያስተላልፍም በኢትዮጵያ ሳይሰማ ቆይቶ ነበር:: በኋላም አቡነ አብርሃም በማረፋቸው አቡነ ዮሐንስ እርሳቸውን እንዲተኩ ተደረገ:: እርሳቸውም ሌሎች አራት ጳጳሳትን ሾሙ:: በዚያን ጊዜም የኢትዮጵያ ጳጳሳት ቁጥር ዐሥር ደርሶ ነበር::

ከጠላት ወረራ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከግብጻውያን ጋር ንግግር እንዲጀመር በማድረጋቸው በተደረጉ ድርድሮች ወደ ሀገራቸው ገብተው የነበሩት ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ ዳግም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ተደረገ:: ውግዘቱም በሥርዓት እንዲነሣ ተፈልጐ ስለነበር ኢትዮጵያዊው አቡነ ዮሐንስ ሥልጣናቸውን ለግብጻዊው አስረከቡ::

ይሁን እንጂ ይህንን ድርድር ጀምረው የነበሩት የግብጹ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ሰኔ ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ዓርፈው ስለነበር አቡነ ዮሳብ ተጠባባቂ ሆነው ተሾሙ:: አቡነ ዮሳብ በከፊል ግዝቱ እንዲፈታ ቢያደርጉም የኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ የሚያስደስት አልነበረም:: ከአንድ ዓመት ከሰባት ወራት በኋላ በጥር ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መቃርዮስ ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ ድርድሩ እንዲቀጥል ራሳቸው ጥያቄ አቅርበው ነበር::

የኢትዮጵያም መልስ አዎንታዊ ስለነበር ድርድሩ ከሰኔ ፱- ፳፩/፲፱፻፴፮ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ተደረገ:: ይሁን እንጂ በነሐሴ ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ደግሞ ፓትርያርክ መቃርዮስ በማረፋቸው ደግሞ እንዲዘገይ ሆነ:: ግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም አቡነ ዮሳብ ፓትርያርክ ሆነው ሲመረጡ ድርድሩ ቢቀጥልም የግብጻውያኑ ሐሳብ አሁንም ሊቀ ጳጳሳትን ግብጻውያን እያደረጉ በመላክ ላይ የሚያጠነጥን በመሆኑ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስደሳች አልነበረም:: በዚሁ ዓመት በአዲስ አበባ በቅድስት ሥላሴ ገዳም ተደርጐ የነበረው የ፷፪ ሊቃውንትና ፳፩ መምህራን መንፈሳዊ ጉባኤ በግብጾች የነበረውን የሊቀ ጵጵስና መዓርግ ጥያቄ በማለዘብ በሞከረው የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል::


በ፲፱፻፴፱ ዓ.ም ግን ሌላ አዲስ የስምምነት ሐሳብ ቀረበ:: ይኸውም ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ እስኪያርፉ ድረስ ሊቀ ጵጵስናው በግብጻውያን እጅ እንዲቆይና ከእርሳቸው ዕረፍት በኋላ ግን ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾም ተስማሙ:: በተጨማሪም ሌሎች አምስት ኢትዮጵያውያን ጵጵስና እንዲሾሙ ፓትርያርኩ ፈቀዱ::

በግንቦት ፲፱፻፵ ዓ.ም ኢትዮጵያ አምስት አባቶች ፊታውራሪ ታፈሰና ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ከሚመሩት ልዑክ ጋር አድርጋ በአቡነ



www.eotcmk.org

ዮሳብ እጅ ጳጳሳት ሆነው እንዲሾሙ ወደ ካይሮ ብትልክም በሚሾሙበት ቀን ግብጻውያኑ ያቀረቡት የውል ቃል ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሚሾመው ሊቀ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳትን እንዳይሾም የሚከለክል ነበር:: በዚህም ኢትዮጵያውያኑ ባለ መስማማታቸው ግንኙነቱ ተቋርጦ ነበር:: በሐምሌ ፲፱፻፵ ዓ.ም አቡነ ዮሳብና ሌሎችም አባቶች ሌላ የመስማሚያ ውል በማቅረብ ተፈራረሙ:: ከዚያም በግንቦት ፲፱፻፵፩ ዓ.ም ወደ ካይሮ ሔደው በቀረበው ውል ላይ ባለመስማማት የተመለሱት አምስት አባቶች ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ፤ እነሱም አቡነ ባስልዮስ፣ አቡነ ሚካኤል፣ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ አቡነ ያዕቆብ፣ እና አቡነ ጢሞቴዎስ ነበሩ::



*በ፲፱፻፵ የተሾሙት ብፁዓን ጳጳሳት*

በሐምሌ ፲፱፻፵ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ዋና ይዘትም

፩ኛ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ከኢትዮጵያውያን የሚመረጥ እንዲሆን፤ ይህ ግን የነበሩት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ካረፉ በኋላ እንደሚሆን፣

፪ኛ. የኢትዮጵያን ሊቀ ጳጳሳት ለመሾም መብቱ ያለው የቅዱስ ማርቆስ መንበር ወራሽ የሆነው ፓፓና ፓትርያርክ ብቻ እንደሆነ፣

፫ኛ. ለጵጵስና የሚታጩት ከገዳማትና አድባራት መነኮሳት ሆነው በዕውቀትና በሥነ ምግባር ከተመሰከረላቸው እንዲሆን፣

፬ኛ. ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም መብት ያለው ሊሾም ያሰባቸውን መነኮሳት ስም፣ ችሎታ እና ሕይወት ለፓፓው ሲያቀርብና እንዲሾሙ ፓትርያርካዊ ትእዛዝ ሲሰጠው እንደሆነ፣

፭ኛ. በሁለቱ ወገኖች መካከልም አንድ ካህን አገናኝ ሆኖ እንዲሾምና የሹመት ትእዛዝን ከፓፓው ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርስ፣ የተሿሚዎች ዝርዝር ሕይወትን ለፓፓው የሚያደርስ እንዲሆን፣

፮ኛ. በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ሹማምንት ሁሉ ይህን ስምምነት እንዲያከብሩ የሚያዝ ነበር:: በጥቅምት ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ሊቀ ጳጳሱ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ታመው በማረፋቸው በተገባው ስምምነት መሠረት ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም በዕለተ እሑድ የሚመተ ሊቀ



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ሊቀ ጳጳስ ሆነው ሲሾሙ*

ጵጵስናው ሥነ ሥርዓት ካይሮ ላይ በቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ተፈጸመ:: ይህ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ያስቻለ ታላቅ አጋጣሚ ነበር:: ይህንንም አጠቃላይ ሒደት በንጉሠ ነገሥቱ ተወክለው ዋና ተደራዳሪ በነበሩት በክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ከፍተኛ ጥረት የተሳካ ነበር::

ከዚህም ሥነ ሥርዓት በኋላ በ፲፱፻፵ በተገባው ስምምነት መሠረት ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነታቸውን እያስኬዱ ባለበት ሁኔታ ውስጥ የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት የሚያሻክር ሌላ ክስተት ደግሞ ተፈጠረ:: ይኸውም ኢትዮጵያዊውን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስን ሊቀ ጳጳስ አድርገው የሾሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ በሲኖዶስ ውስጥ በተፈጠረ መከፋፈል ምክንያት ከመንበረ ፕትርክናቸው ተነሡ:: ይህም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ተቀባይነት ባለማግኘቱ ግንኙነቱን የሚያሻክር ሆኖ ነበር:: ችግሩን ለመፍታት ኢትዮጵያ ልኡካን ወደ ካይሮ ብትልክም ለችግሩ በቂ መፍትሔ ሳይገኝ በእንጥልጥል እንዳለ ፓትርያርኩ ዐረፉ::

ከአቡነ ዮሳብ ዕረፍት በኋላ በእርሳቸው ላይ በተፈጸመው ጥፋትና የሚመረጠውን አዲስ ፓትርያርክ ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያውያን ሌሎች ጥያቄዎችን ማቅረብ ጀመሩ፤ እነዚህም:

፩ኛ. ኢትዮጵያ ከምእመናኗ ቁጥር ብዙ መሆን ጋር ተገናዝቦ በፓትርያርክ ምርጫው የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እንዲወሰን፤

፪ኛ. ለፓትርያርክነት እጩ ሆኖ በማቅረብ ረገድ የወገን ልዩነት /Discrimination/ እንዳይኖር፤

፫ኛ. በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በፊት የኢትዮጵያውያን የፓትርያርክ መራጮችን ቁጥር አሳንሶ የተዘጋጀው ሰነድ እንዲሻር፤

፬ኛ. ስለ ፓትርያርክ ምርጫና ስለ መንፈሳዊ ጉዳይ ባለሥልጣኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ እንዲሆን የሚሉ ነበሩ::

ግብጻውያኑ የተወሰኑት ነጥቦች ያልተዋጡላቸው ቢሆንም ከብዙ ክርክር በኋላ አዲስ መዋቅር እንዲዘጋጅ፣ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሥልጣንም ወደ ምክትል ፓትርያርክነት ደረጃ እንዲያድግ የሚሉ ሐሳቦችን አቀረቡ:: ኢትዮጵያውያኑ ግን ምክትል የሚለው መዓርግ ቀርቶ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የፓትርያርክነት መዓርግ እንዲሰጠው ይጠይቁ ነበር::

በመጨረሻም ሐምሌ ፲፱፻፶፪ ዓ.ም:

፩ኛ. በምርጫ ተሳትፎ ረገድ ሳሁኑ ኢትዮጵያ የእኩልነት መብት እንዲኖራት፤

፪ኛ. ወደፊት የምርጫው ሕግ ተለውጦ በስምምነት እንዲወሰን፤

፫ኛ ስለ ምርጫውና ስለ መንፈሳዊ ጉዳይ ባለሥልጣኑ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲሆን፤

፬ኛ. ፓትርያርኩ ለጊዜው ግብፃዊ እንዲሆን ተስማምተው አዲስ ፕሮቶኮል ተፈረመ::

ይሁን እንጂ ስምምነቱን በግብጽ መንግሥት በኩል ድጋፍ ሳያገኝ በመቆየቱ የፓትርያርክ ምርጫው እንዲዘገይ ሆነ:: በኋላም ተጠባባቂ ፓትርያርኩ በታኅሣሥ ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ የተሻሻለው የምርጫ ሕግ በሥራ ላይ ሊውል እንደማይችል ገለጹ:: ኢትዮጵያም ስምምነቱ የማይፈጸም ከሆነ የሚመረጠውን ፓትርያርክ ፓትርያርኳ አድርጋ እንደማትቀበል አስታወቀች:: በዚህም ምክንያት የግብጽ ቤተ ክርቲያን ያለ ኢትዮጵያ ተሳትፎ የፓትርያርክ ምርጫ በማድረግ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛን በግንቦት ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ሾመች::

በኋላ ግን አዲሱ ፓትርያርክ ለኢትዮጵያ ታላቅ የምሥራች ላኩ፤ የኢትዮጵያን ሊቀ ጳጳስ ወደ ፓትርያርክነት ሥልጣን ለማሳደግ:: ይህ ከመደረጉ በፊት ግን የተለያዩ ውይይቶች ተደረገው ነበር:: ከእነዚህም የሰኔ ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ስምምነት የተዘጋጀባቸው ነጥቦች መነጋገሪያ ነበሩ:: ከእነዚህም መካከል

፩ኛ. ግብጻውያን የግብጹ ፓትርያርክ የእስክንድርያ ፓፓና ፓትርያርክ ተብሎ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ አለቃ እንዲሆን ሐሳብ ቢያቀርቡም ኢትዮጵያውያን ግን «አለቃ» ሳይሆን «ከፍተኛ መንፈሳዊ አባት» ተብሎ እንዲወሰን በማሳሰባቸው ከብዙ ክርክር በኋላ ግብጾች ተቀበሉት::

፪ኛ. የማርቆስ መንበር ወራሽ የሚሆነው ፓፓና ፓትርያርክ ሁል ጊዜ ግብጻዊ እንዲሆን ግብጻውያን ያቀረቡት ሐሳብ አከራካሪ ነበር:: ግብጻውያን ሁለት መሪዎች እንዲኖራቸው አልፈለጉም ነበር:: ስለዚህም መንበሩን ከመጠበቅ አንፃር ለከፈሉት መስዋዕትነት እንደ ዋጋ እንዲታሰብላቸው ግብፃውያን ስለጠየቁ ኢትዮጵያውያንም ተስማምተዋል::

፫ኛ. በእስክንድርያው ፓፓና ፓትርያርክ ምርጫ ላይ ኢትዮጵያውያን በታዛቢነት ብቻ እንዲገኙ ግብጻውያኑ ያቀረቡት ሰነድ ውድቅ ሆኖ በወሳኝነት



www.eotcmk.org

እንድትገኝ በኢትዮጵያውያን ተደራዳሪ ዎች ጥያቄ ቀርቦ ነበር:: በኋላ ግን ከብዙ ክርክር በኋላ የተሳታፊዎቹን ቁጥር ፓፓው የሚወስን ሆኖ ወሳኝ ሆነው እንዲሳተፉ ግን ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር::

፬ኛ. ለኢትዮጵያው ፓትርያርክ «ካቶ ሊኮስ» የሚል ቅጽል ተጨምሮ በመንበረ ማርቆስ ያሉት ሁለቱ ፓትርያርኮች መለያ እንዲኖራቸው ይደረግ በማለት ግብጻውያን ሐሳብ ቢያቀርቡም ኢት ዮጵያውያን ግን «ካቶሊኮስ» የሚለውን ባለመቀበላቸው ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት» በሚል እንዲጠራ ተስማምተዋል::

ይህ ግን በእግሊዝኛና በአማርኛው ፍትሐ ነገሥት ውስጥ ቢካተትም በዐ ረብኛው ትርጉም ግን ፓትርያርክ ካቶ ሊኮስ በማለት ግብጾች አሁንም ይጠሩ ታል /ይተረጉሙታል/:: /Coptic Dictionary/:: ነገር ግን ለስምምነቱ ኦፊሲ ላዊው ቋንቋ እንግሊዝኛ እንዲሆን በመ ቆረጡ ካቶሊኮስ የሚለው ዋጋ አላገኘም::

፭ኛ. የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የሚሾ ማቸውን ጳጳሳት ዝርዝር አስቀድሞ ለፓ ፓው እንዲልክ በግብጾች በኩል ሐሳብ ቀርቦ በኢትዮጵያው ያኑም በኩል ለግንኙነቱ መጠን ከር አስተዋጽኦ ስለሚኖረው በሚል ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር::

፮ኛ. በሁለቱ ወገኖች መካ ከል ጊዜ ፈጅቶ ውይይትና ክርክር የተደረገበት ሌላው ዐቢይ ነጥብ ደግሞ ኢትዮጵያ ከግዛቷ ውጪ ኤጲስ ቆጶሳትን እንዳት ሾም የሚከለክል ረቂቅ ሐሳብ ግብፃውያኑ ማቅረባቸው ነበር:: ኢትዮጵያውያን ግን:

፩ኛ. የግብጽ ቤተ ክርስቲ ያን ካላት ጂኦግራፊያዊ ሁኔታና በዓለም ላይ ካላት ፖለቲካዊ ሁኔታ አንፃር መንበረ ማርቆስን በዓለም ለማስተዋወቅና ለማስፋ ፋት አቅም ስለሌላት ከእርሷ አንፃር ሲታይ ኢትዮጵያ መን ግሥቷ በዓለም ላይ ተደማጭነት ያለ ውና ለእነርሱም ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖ ችም የሚቆም ክርስቲያን መንግሥት በመሆኑ፤

፪ኛ. በዘርና በቀለምም ለአፍሪካውያ ንና በዓለም ጥቁሮች ዘንድ ከግብጽ ይልቅ ኢትዮጵያ ተቀባይነት በማግኘቷ፤ ለዚ ህም ወደ ደቡብ አፍሪካ ተልከው የነበ ሩትን ግብጻዊውን ጳጳስ አባ ኢዮብን የጨቋኞቻችንን የፈረንጆቹን መልክ የያዘ ነው በሚል ክርስቲያኖቹ መመለሳቸው፤

፫ኛ. ብዙ አፍሪካውያን በተለይም በዩጋንዳ፣ በኬንያ፣ በሱዳን፣ በናይጄ ሪያ፣ በጋና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋምላቸው በመጠየቃቸው፤

፬ኛ. በአሜሪካ ዌስት ኢንዲስ ሁለት መቶ ሺሕ የሚያህሉ ምእመናን የሚ ገኙበት የኢትዮጵያ ሀገረ ስብከት ተቋቁሞ ከቤተ ክርስቲያኒቱም ምእመ ናን አንዳንዶቹ በፓርላማ ተሳትፎአቸው በመንግሥት ተደማጭነት እስከ ማግኘት መድረሳቸውን በምክንያትነት ጠቅሰው ኢትዮጵያ ከግዛቷ ውጪ ሀገረ ስብ ከቶችን ማስፋፋቷ ፓፓና ፓትርያርኩን የክብሩ ተካፋይ ስለሚያደርገው ግብጻው ያን ቀድመው ሀገረ ስብከት ካቋቋሙ ባቸው አካባቢዎች ሌላ መታገድ የለ ብንም ሲሉ ተከራከሩ::

በመጨረሻም እገዳው ቀርቶ «የኢት ዮጵያ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጉዳዩን በሚያነሣበት ጊዜ አሁን ተይ ዘው ካሉት የስብከት አውራጃዎች ውጪ በቅዱስ ማርቆስ መንበር አዲስ ሀገረ ስብከቶችን ለማቋቋምና የኢትዮጵያ ፓት ርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በእነዚህ አዲስ ሀገረ ስብከቶች ላይ ሊቃነ ጳጳሳ ትንና ኤጲስ ቆጶሳትን የመቀባቱን ጉዳይ ለመጨረስ ወደፊት ቅዱስ ፓፓውና የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ይመካከሩበታል» እንዲባል ተወሰነ:: የዚህ አንድምታም ስምምነት ላይ ካልደረሱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በውጪ እንዳትስፋፋ የሚከለክላት ነገር አይኖርም ማለት ነው::

ሌላው የተነሣው ነጥብ ለፓትርያር ክነት የሚመረጠው ሰው ከቆሞስነት መዓርግ በላይ ካልሆኑት መነኮሳት መካከል እንዲሆን የሚል በስምምነቱ እንዲካተቱ ግብጾች ቢጠይቁም በዚያን ጊዜ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርቲያን ፓት ርያርክ እንዲሆኑ በቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ የታሰቡት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ስለነበሩ ከእርሳቸው በኋላ ለሚመረጠው ፓትርያርክ የሚሠራና በግ ብጽ ቤተ ክርስቲያን ላይም ተፈጻሚ የሚሆን ስለተደረገ በስምምነቱ ተካቷል::

ሌላው ደግሞ የኢትዮጵያ ፓትር ያርክ የሚሾማቸውን ሊቃነ ጳጳስትና ኤጲስ ቆጶሳት ከመሾማቸው በፊት በጽ ሑፍ በሆነ ቃለ መሐላ ላይ እንዲፈርሙና ጽሑፉ ለፓፓና ፓትር ያርኩ እንዲላክ በማለት ግብጻውያን ሐሳብ አቅርበው ነበር:: ይህም በፍትሐ ነገሥቱ በተቀመጠው መሠረት ዘጠኝ ሊቃነ ጳጳሳት ያሉት አንድ ሲኖዶስ ፓትርያርክ የመሾም መብት ስላለው ግንኙነታችን ተቋርጦ እንዳይቀር ይህንን ፓፓና ፓትርያርኩ መጠበቅ አለበት ብለዋል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በመጀመሪያ ላለመቀበል ቢወስኑም በኋላ ግን አዲስ አበባ ላይ ጉዳዩ ከተመከረበት በኋላ ለግንኙነታችን መጠንከር ተብሎ የተደረገ እንደሆነ በማጤን ስምምነት ላይ ተደርሷል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ግን የኢትዮጵ ያው ፓትርያርክ በእርሱ የሚሾሙትን የሊቃነ ጳጳስትና የኤጲስ ቆጶሳት ስም ከሕይወት ታሪካቸው ጋር ወደ ፓፓው እንዲልክ ከሚለው ቃል ጋር «ፓፓው እንዲያውቁት ለማድረግ» የሚል ቃል ተጨምሮ ስለነበር «በፓፓው ዘንድ በግልጽ እንዲመዘገብ ለማድረግ» በሚል ቃል እንዲሻሻል የኢትዮጵያ መልእክተ ኞች ጥያቄ አቅርበው በዚሁ መሠረት ስምምነት ላይ ተደርሷል::



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ

በተጨማሪም የኢትዮጵያው ፓትርያርክ ብቻ ሳይሆን ፓፓው የሚሾማቸውን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ዝርዝር ከሕይወት ታሪካ ቸው ጋር ለኢትዮጵያው ፓትርያርክ እንዲልክ በመ ስማማታቸው እኩልነትን በሚገልጽ አሠራር እንዲ ራመድ ተስማምተዋል:: ፓፓው በተለያዩ ምክንያ ቶች ቅዱስ ሲኖዶስን መሰብሰብ ባልቻለ ጊዜ የኢትዮጵያው ፓትርያርክ ተክቶ እንዲሰበስብ በኢት ዮጵያውያኑ ልኡካን የተ ጠየቀ ሲሆን ግብጻውያ ኑም ተቀብለውታል::

በዚህ ስምምነት ጊዜም በሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም የተፈ ረመው ስምምነት የተሠረዘ መሆኑ ታውቋል::

ይህ ስምምነት ደግሞ ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በግብጻውያኑና በደጅ አዝማች አሥራተ ካሣ በሚመራው የኢ ትዮጵያ ልኡክ መካከል ተፈረመ:: ከዚ ያም ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም የኢ ትዮጵያ የመጀመሪያ ፓትርያርክ የተሾ ሙበት ታላቅ ኀሠነ ሥርዓት በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ተፈጸመ::

በጊዜው በሀገሪቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተገኝተው ነበር:: ከበዓለ ሢመቱ በኋላ ፕሬዝዳንት ገማል አብደል ናሥርና ሌሎች ግብጻውያን ለንጉሠ ነገሥቱና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ታላቅ ክብር ሰጥተው ነበር:: ከዚያ በፊትና በኋላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ





www.eotcmk.org

ለግብጽ ገዳማት ሆስፒታሎች ሕፃናት ማሳደጊያዎች ብዙ ፓውንድና የእጅ መስቀሎች ሰጥተዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስም በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም አዲስ አበባ በተዘጋጀው የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስ ቲያናት ጉባኤ ለመገኘት በመጡ ጊዜ ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል::

ሁለቱ ፓትርያርኮች በተከታታይ ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላም በኢትዮጵያ ተተ ክተው በተሾሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና በግብጽ በተተኩት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መካከል ግንኙነቱ ቀጥሎ ነበር:: ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳም ከተሾሙ በኋላ ሁለት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው በመስከረም ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን ከወ ረዱ በኋላ በተፈጠረው ፓለቲካዊ አለ መረጋጋት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ የሚፈለገ ውን ያህል ተራምዳ አለመገኘቷ ከአኀት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የነበራትን ግንኙነትም ጐድቷል:: ከ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳዉሎስን ፓት ርያርክ ሆኖ መሾም ተከትሎ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት እስከ መሆን በደረሰው የኢኩሜኒዝም እንቅስ ቃሴ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋርም ላለው ግንኙነት በር ከፍቷል:: የዚያም ውጤት የእስክንድርያው ፓፓ የግብጹ ፓትርያርክ ሺኖዳ ለሁለተኛ ጊዜ ኢት ዮጵያን ለመጐብኘት በቅተዋል:: ቅዱስነ ታቸው በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ /ከዘመነ መሳፍንት በኋላ/ ኢት ዮጵያን በመጐብኘት ሦስተኛው ፓትር ያርክ ሆነዋል:: ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን መጐብኘታቸው ደግሞ ልዩ ያደርጋቸ ዋል::

ቅዱስነታቸው የሚመሩት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የአባቶች ልኡካን ቡድን በአዲስ አበባ መገኘት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን ግንኙነት በሌላ አዲስ መንገድ ማስኬድ የሚያስ ችል ስምምነት ለመፈረም አብቅቷል:: አዲሱ የስምምነት ሰነድ ዐሥራ አምስት አንቀጾችን ይዟል:: ስምምነቱ በጥቅል ሲታይ

፩ኛ. ሁለቱ አብያተክርስቲያናት የየ ራሳቸው ነጻነት ያላቸው እንደሆኑ ያስቀ ምጣል:: በአንቀጽ ፩ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ነጻነት ዕውቅና እንደምትሰጥ መቀመጡ፣ በአንቀጽ ፫ ሁለቱም ነጻ መሆናቸውን በግልጽ ማቅረቡ፣ በአንቀጽ ፯ ሁለቱም የየራሳቸውን ፓትርያርክ እንደሚመርጡ ማሥፈሩ ያንን ግንኙነታቸውን በጉልህ ያሳየናል::

፪ኛ. የኢትዮጵያ መንበረ ጵጵስናና መንበረ ፓትርያርክ ከመንበረ ማርቆስ መገኘቱን ከግምት አስገብቶ የእስክንድ ርያው ፓፓ በክብር ቀዳሚውን ሥፍራ እንዲይዝ ተደርጓል:: በአንቀጽ ፪ ይኸው ቀዳሚ ክብር ለእስክንድርያው ፓፓ እን ደሚሰጠው በማያሻማ ሁኔታ ሲገልጽ በአ ንቀጽ ፬ የሁለቱ አብያተክርስቲያናት

## የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ካላት ጂኦግራፊያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ አንጻር መንበረ ማርቆስን በዓለም ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት አቅም ስለሌላት ከእርሷ አንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ መንግሥቷ በዓለም ላይ ተደማጭነት ያለውና ለእነርሱም ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖችም የሚቆም ክርስቲያን መንግሥት በመሆኑ፤...

ፓትርያርኮች ስም እንዲጠራ በተ ስማሙባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ቀድሞ የሚጠራው የእስክንድርያው ፓፓ ስም መሆኑን ይነግረናል:: የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች ስም እንዲ ጠሩባቸው ተለይተው የተቀመጡ ሁኔታ ዎችም

ሀ. የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት አባ ቶች በሚገናኙበት፣

ለ. ከሁለቱ አብያተክርስቲያናት መሪ ዎች አንዱም ሥርዓተ ቅዳሴ ሲመራ /celebrating the liturgy /

ሐ. አንድ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ በሌላው ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ በሚሳተፉበት ጊዜ

መ. ታላላቅ በዓላት /ትንሣኤ፣ ልደት፣ ጥምቀት፣ መስቀል በሚከበሩባቸው ጊዜያት ሲሆን የእስክንድርያው ፓፓ ስም ቀድሞ የሚጠራ ይሆናል::

፫ኛ. ሌላው ጎልቶ የሚታየው ጠቃሚ የስምምነቱ ነጥብ ትብብር ነው:: በአን ቀጽ ፭ የሠፈረው የሁለቱ አብያተ ክር ስቲያናት ሲኖዶሶች የመደበኛ ጉባኤ ውሳኔ ልውውጦች፣ በአንቀጽ ፮ የቀ ረበው በየሦስት ዓመቱ እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ እንዲደረግ የተወሰነው የሁለቱ አብያተክርስቲያናት ጠቅላይ የቅ ዱስ ሲኖዶስ የጋራ ጉባኤ፣ በአንቀጽ ፯ የሠፈረው በፓትርያርክ ምርጫ አንዱ በሌላው ሲኖዶስ የሚኖረው የአምስት ልዑካን ተሳትፎ፣ እንዲሁም በአንቀጽ ፰ በፓትርያርኩ ሥርዓተ ሲመት እንዲኖር የተፈለገው በግብዣ የሚፈጸም ተሳትፎ፣ በአንቀጽ ፱ ያለው በዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ በሌላው ቤተክርስቲያን የሚኖ ረው የታዛቢነት ሚና፣ በአንቀጽ ፲ የተ ቀመጠው ሚና፣ በኢኩሜኒካል ጉባኤዎ ችና ከሌሎች እምነቶች ጋር በሚደረጉ ንግግሮች እንዲደረግ የሚፈለገው ምክ ክር፣ በአንቀጽ ፲፪ የሠፈረው በሥነ መለኮት ትምህርት፣ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ፕሮግራሞች፣ በማ ኅበራዊ አገልገሎት፣ በልማት ፕሮጀክ ቶችና በምእመናን ጥበቃና እንክበካቤ በሌሎችም መስኮች የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ በስምምነቱ ላይ ተደጋግሞ መሥፈሩ ዋናው አጀንዳ ትብብር መሆኑን ያመለክታል::

ከላይ የተጠቀሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዘው ዐሥራ አምስት አንቀጽ ያለው ስምምነት ሲጸድቅ ከዚህ በፊት የነበሩ የትኞቹንም ስምምነቶች ከተፈጻሚነት ውጪ አድርጓቸዋል:: ይህም እውን እን ዲሆን በስምምነቱ አንቀጽ ፲፫ ተቀ ምጧል:: የስምምነቱ ፲፬ኛ አንቀጽ በሁ ለቱ ሲኖዶሶች ጸድቆ ከተፈረመ ለተ ፈጻሚነቱ በሁለቱም አብያተ ክርስቲ ያናት መዋቅሮች ሁሉ እንደሚሠራጭ ይጠቅሳል::

ስምምነቱ በአማርኛ፣ በዐረብኛ በእን ግሊዝኛ ቋንቋዎች እንደሚዘጋጅ የስም ምነቱ ፲፭ኛ አንቀጽ ሲያመለክት በት ርጉም ረገድ አለመግባባቶች ቢከሰቱ የእንግሊዝኛው ቅጂ የጸና እንደሚሆን በግልጽ ተቀምጧል::

ስምምነቱ በ፲፱፻፵ እና በ፲፱፻፶ ዓ.ም በተፈረሙ ስምምነቶች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከነበረው የግብጾች ሙሉ ወይም ከፊል የበላይነትና ቁጥጥር በእ ጅጉ ተለይቶ ለቤተክርስቲያኒቱ ነጻ ነት ፍጹም ዕውቅና የሚሰጥ ነው:: ነጻነ ቷም ቤተክርስቲያኒቷ በሁሉም ደረጃ ያሉ የራሷን ኤጲስ ቆጶሳት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሾም በመቻሏ ይገለጻል::◆

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


*ምንጮች:-*

- *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ አባ ጎርጎርዮስ፣ አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም*
- *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀ መሪያው ፓትርያርክ*
- *የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና ነጻነት፣ ፲፱፻፹፯ ዓ.ም*
- *የኢትዮጵያ አጭር የሥነ ጽሑፍ ታሪክ፣ እምሳሉ አክሊሉ*
- *ሐመረ ተዋሕዶ፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም*
- *ተአምረ ማርያም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ፣ አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም*
- *ስንክሳር፣ ሚያዝያ ፲*
- *ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፣ ዲ.መርሻ አለኸኝ፣ አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም*
- *የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ፣ ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ*
- *Church & State, Taddese Tammerat, Great Britain, Oxford university, 1972*
- *A History of Modern Ethiopia, Bahru Zewde, Addis Abeba, 2002*
- *Coptic Dictionar, 1992*
- *Coptic - Ethiopian church Negotiation From 1881-1971, Eighth international conference of Ethiopian studies*
- *coptic Encyclopedia V.2 V.3*◆




www.eotcmk.org

# ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት

ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

*ባለፉት ሁለት ኅትመቶች ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለክህነትና ካህናት ካስተማረው ትምህርት በተከታታይ አቅርበን ነበር፤ ተከታዩ ትምህርት ደግሞ የሚከተለው ነው። በርግጥ በክህነት እያገለገሉና እየተገለገሉ ያሉት ሁሉ ሊያልፉት የማይገባ ትምህርት።*

፩. በመንፈሳዊ ልደት አምጠው እንዲወልዱና በጥምቀት በኩል ለሚገኘው ዳግም ልደት ሓላፊነት የተጣለባቸው እነዚህ ናቸው። በእነርሱ አማካይነት ክርስቶስን እንለብሳን፤ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር አብረን እንቀበራለን፤ ለተቀደሰው ራሳችን (ለኢየሱስ ክርስቶስ) አካላትም እንሆናለን። ስለዚህም ከነገሥታትና ከገዢዎች የበለጠ ሊፈሩ ብቻ ሳይሆን ከወላጆች የበለጠ ሊከበሩም ይገባል። እነዚህ ከደምና ከሥጋ ፈቃድ የተነሣ የሚወልዱን ሲሆን እነዚያ /ካህናት/ ግን እውነተኛ ነጻነትና ታላቅ ጸጋ ለሆነው ከእግዚአብሔር ለምናገኘው ልደት መሣሪያዎች ናቸውና።

የአይሁድ ካህናት ሰውነትን ከለምጽ የማንጻት ሀብት ነበራቸው፤ ያውም የማንጻት ሥልጣን ሳይሆን የነጹ መሆን አለመሆናቸውን መመርመርና የነጻውን ነጽቷል ብሎ ማወጅ ብቻ ነበር። /ማንጻት አይችሉም ነበርና/ እንዲህም ሆኖ ግን ካህናት ምን ያህል ይከበሩ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ይቻላል። የእኛ ካህናት ግን ሥልጣን የተቀበሉት

የእኛ ካህናት ግን ሥልጣን የተቀበሉት

በሰውነት ለምጽ ላይ ሳይሆን በመንፈሳዊ ለምጽ ላይ ነው። ከተመለከቱ በኋላ ነጽቷል ለማለት ሳይሆን በእርግጥና በፍጹም ለማንጻት ነው። ስለሆነም ካህናትን የሚነቅፉ ከዳታንና ከማኅበሩ የበለጠ እጅግ የተረገሙ ናቸው፤ ከእነርሱ የባሰ ቅጣትም የሚገባቸው ናቸው። እነዚያ ምንም እንኳ ያልተሰጣቸውን ክህነትን ይገባናል ብለው ቢነሡም ቅሉ ክህነትን በተመለከተ ከፍ ያለና የተከበረ አመለካከት ነበራቸው። በርግጥም ክህነትን የፈለጉት ለእርሱ ከነበራቸው ጉጉትና ፍላጎት የተነሣ ነበር። እነዚህ ግን ሀብተ ክህነት ዛሬ ካለበት አማናዊ ደረጃ ከደረሰና ከበፊቱ በበለጠ የከበረ ከሆነ በኋላ በተቃራኒው መንገድ ቢሆንም ቅሉ ከእነዚያ (ከነ ዳታን) የበለጠ ድፍረትን ያሳያሉ። የማይገባውን ክብር በመፈለግ መካከልና ይህን ታላቅ ክብር በማቃለል መካከል ያለው የንቀት ልዩነት እኩል አይደለምና። ነገር ግን ማጣጣል ከማድነቅ የሚለየውን ያህል የኋለኛው ከፊተኛው ይልቃል። ታዲያ ይህን ያህል ታላቅ ክብር የምትንቅ ምን ዓይነት ጎስቋላ ነፍስ ትኖራለች? ሰይጣናዊ ዝንባሌ ያደረባት ካልሆነች በስተቀር እንዲህ የምታደርግ ነፍስ ትኖራለች ብዬ አላስብም።




ወደ ተነሣሁበት ነጥብ አሁን እንደገና እመለሳለሁ። በመገሠፅ ብቻ ሳይሆን በመጥቀም መንገድም እግዚአብሔር ከወላጆቻችን የበለጠ ለካህናት ሰጥቷቸዋል። በርግጥ ሁለቱ የዚህ ዓለምና የሚመጣው ዓለም ሕይወት ያህል ይለያያሉ። የተፈጥሮ ወላጆቻን የሚወልዱን ለዚህ ሕይወት ብቻ ነው፤ እነዚያ ግን ለሚመጣው ሕይወት ነው። ወላጆች ከወለዷቸው ሞትን ማራቅ ወይም ከበሽታ መጠቃት ነጻ ማድረግ አይችሉም፤ እነ

መጠቃት ነጻ ማድረግ አይችሉም፤ እነ

ዚህ ግን የታመመችን ነፍስ ያድናሉ። በመጥፋት ላይ የነበረችንም ብዙም በማይጎረብጥ ቀኖና አማካይነት ገንዘብ ያደርጓታል። በትምህርትና በተግሣፅ ብቻ ሳይሆን በጸሎት በሚገኘው ዕርዳታና ኃይል በመታገዝ ሌሎችንም ሰዎች ተያይዘው በበሽታ እንዳይወድቁ ያደርጋሉ። በጥምቀት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በኋላ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን አላቸውና። እንዲህም ተብሏልና፡- «ከእናንተ መካከል የታመመ ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም በዘይት እየቀቡት ይጸልዩለት። የእምነት ጸሎት የታመመውን ይፈውሰዋልና። ጌታም ያነሣዋል። ኃጢአት ሠርቶም ከሆነ ይሠረይለታል።» (ያዕ.፭፥፲፬-፲፭) እንደገናም የተፈጥሮ ወላጆቻችን ልጆቻቸው ከዚህ ዓለም ባለሥልጣናት ጋር ቢጋጩ ብዙም ሊጠቅሟቸው አይችሉም። ካህናት ግን ገዢዎችንና ነገሥታትን ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ላይ በተቆጣ ጊዜ ሕዝቡንም ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቀዋል።

መልካም! እንግዲህ ከዚህ በኋላም እኔን ስለ ዕብሪት የሚከሠኝ ሰው ይኖር ይሆን? በእኔ በኩል ከዚህ ከተባለው ነገር በኋላ ይህን ሓላፊነትና ሹመት የሚሸሹትን ስለ ዕብሪተኝነትና ስለ ድፍረት የሚወቅሷቸው ሳይሆን ይልቁንም ወደ ክህነት ለመቅረብ ፈቃደኞች ሆነው እሺ የሚሉትንና ይህን ክብር ለራሳቸው ለማግኘት ጉጉት የሚያድርባቸውን ሰዎች እንደሚሆን አስባለሁ። የሰማዕያኑም ነፍስ እንዲህ ያለው ሃይማኖታዊ ማስተዋልና ፍርሃት ይኖራታል ብዬ አስባለሁ። ከተሞችን የማስተዳደር ሓላፊነት የተቀበሉ ሰዎች ማስተዋልና ጥንቃቄ ከማነስ የተነሣ የሚያስተዳድሯቸውን ከተሞች የሚያበላሹና ከዚህም ጋር አብረው ራሳቸውንም የሚያጠፉ ከሆነ ሓላፊነቱና ተግባሩ የክርስቶስን ሙሽራ ማስጌጥ የሆነ ሰው ከራሱ እና ከላይ የሆነ ምን ያህል ኃይልና ጥበብ ያስፈልገው ይመስልሃል?

፪. ከቅዱስ ጳዉሎስ በላይ ክርስቶስን የሚወድ አልነበረም። እንደ እርሱ ቅንዓቱን የገለጸ ለብዙ ጸጋም የታደለ አልነበረም። የሆነው ሆኖ ከእነዚህ ሁሉ ታላላቅ ልዕልናዎቹ በኋላ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ከእርሱ አስተዳደር ሥር ስላሉት በማሰብ ይፈራና ይንቀጠቀጥ ነበረ። እርሱ ራሱም «እኔ እፈራለሁ» ብሏል። «እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት

«እባብ [...] ንን እንዳሳታት

ሐሳባችሁ [...] ርስቶስ ከሚሆን
ቅንነትና [...] ት እንዳይለወጥ
ብዬ እፈ[...]። (፪ቆሮ.፲፩፥፫)
እንዲሁም [...] ር በድካምና በፍ
ርሃት በበ[...] ነበርሁ» ይላል።
(፩ቆሮ.፪፥[...] ን የሚለው ሰው
እርሱ እስ[...] ማይ ድረስ የተ
ወሰደና ለ[...] ትን ድንቅ የእ
ግዚአብሐ[...] ተካፋይ የተደ
ረገ ነው። [...] እንዲሁም አማኒ
ከሆነ በኋ[...] ቀናት መጠን
ሞትን ሲ[...]። በተጨማሪም
በርሱ ትያ[...] ምእመናን እንዳ
ይሰናከሉ [...] ክርስቶስ ለደቀ
መዛሙር[...] መብት እንኳን
ያልተጠቀ[...] «ከእናንተ ጋር
ሳለሁ በጐ[...] ንም አልከበድሁ
በትም ... [...] ንዳልከብድባችሁ
ተጠንቀቅ[...] ለሁ።» እንዳለ
(፩ቆሮ.፱፥[...]፥፱፤ ፩ተሰ.፪፥፱)
ከእግዚ[...] ካዘዛቸው ትእ
ዛዛት በላ[...] ትን ወደ ማድ
ረግ የሄደ[...] ሁም ሁል ጊዜ
የራሱን ግ[...] ርሱ የሚያስተ
ዳድራቸው[...] ቸውን ሰዎች
ጥቅም ብ[...] የነበረው እርሱ
የሓላፊነቱ[...] ሰበው ሁል ጊዜ
በፍርሃት [...] ብዙ ሁኔታዎች





www.eotcmk.org

የራሳችንን ጥቅም የምናስቀድም፣ ከታዘዘው አልፈን ትሩፋት ለመሥራት የማንችል፣ ይህም ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ የታዘዘውን በቀጥታ የምናፈርስ የእኛ ሁኔታ ምን ሊሆን ይችላል? «የማይደክም ማን ነው?» ይላል፣ «እኔ አልደክምምን? የሚሰናከል ማን ነው እኔ አልናደድምን?» (፪ ቆሮ. ፲፩፥፳፱)

እንደዚህ አንድ ካህን ሊሆን የሚገባው ሰው በርግጥ እነዚህ ትንሽ ነገሮች ስለሆኑ ከዚህ የበለጠ ሊሆን ይጠበቅበታል:: እነዚህ ነገሮች ልለው ካሰብሁት አንፃር ትንሽ ናቸውና:: እነዚህ ምንድን ናቸው? «በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና» (ሮሜ ፱፥፫) ይህን ቃል መናገር የሚችል እንዲህ ያለውን ጸሎት መጸለይ ደረጃ የደረሰ ካለ ይህ ሰው ከዚህ ሓላፊነት ቢሸሽ በርግጥም ሊወቀስ ይችል ይሆናል:: ነገር ግን እንደ እኔ ያለው ይህ ደረጃና ብቃት የሌለው ሰው ሊጠላና ሊነቀፍ የሚገባው ሓላፊነቱን እምቢ ቢል ሳይሆን እሺ ብሎ ቢቀበል ነው:: ለከፍተኛ ወታደራዊ ሓላፊነት የሚሆን ሰው ሊመረጥ ቢሆንና ለዚህ የሚሆነውን ሰው የመፈለግና የመሾም መብት ያላቸው ሰዎች አንዱን ጫማ ሰፊ ወይም ብረታ ብረት ሠሪ ወይም ሌላ መንገድ አላፊ መርጠው ቢሾሙና ሠራዊቱን በእርሱ አመራር እጅ ቢያደርጉ ለዚህ ክብር የተመረጠው ሰው አልችልም ብሎ ባይሸሽና እንዲህ ወዳለው ግልጽ ወደ ሆነ ችግር ዓይኑ እያየ እንዳይገባ የሚችለውን ነገር ሁሉ ካላደረገ ይህን ጎስቋላ ሰው አላመሰግነውም::

> *እስኪ ንገረኝ! በቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያሉ ታላቅ ችግሮች የሚመጡት ከየት ይመስልሃል? እንደ እኔ የእነዚህ ብቸኛ ምንጫቸው ጳጳሳትና ካህናት የሚመረጡበት መንገድ ጥንቃቄ የጎደለውና እንዲሁ በዘፈቀደ መሆኑ ነው::*

ካህን የሚለውን ስም መያዝ ብቻ የሚበቃ፣ ሓላፊነቱ የሚጠይቀውን ሥራ እንዲሁ በዘፈቀደ ማድረግ የሚቻል ከሆነና እንዲህ ማድረጋችን አደጋ የሌለው ከሆነ የሚፈልግ ሰው እኔን በዕብሪተኝነትና በክብር ፈላጊነት ይውቀሰኝ:: ነገር ግን ይህን ጥበቃ የሚወስድ ሰው እጅግ ብዙ መረዳትና ማስተዋል የሚያስፈልገው ከሆነ፤ ከዚህም በፊት ታላቅ የሆነ ጸጋ ከእግዚአብሔር ማግኘት፣ የምግባር ቀናነት፣ የሕይወት ንጽሕናና ከሰዎች ላቅ ያለ የመልካም ምግባር ሕይ ወት ሊኖረው የሚገባ ከሆነ ይህን ታላቅ ሓላፊነት በመቀበል በከንቱ ልጠፋ ባለ መፈለጌ ምክንያት ይቅርታን አትንፈጉኝ::

በተጨማሪም ሙሉ ጭነት የተጫነችና ውድ በሆኑ ነገሮች የተመላችን የነጋዴ መርከብ ሓላፊነት የተሰጠ አንድ ሰው እኔን ወስዶ ከመሪው ዘንድ አስቀምጦ የኤጂያንን ወይም የቲርሀን ባሕር አቋርጥ ቢለኝ ወዲያውኑ አልችልም ብዬ ከዚህ ሐሳብ ወደ ኋላ እላለሁ:: «ለምን?» ብሎ የሚጠይቀኝ ሰው ቢኖር «መርከቡን እንዳላሰጥመው ነው» እለዋለሁ:: ጥፋቱና ኪሳራው ቁሳዊ ሀብትን በተመለከተ ሲሆንና አደጋውም እስከ ሰውነት ሞት ብቻ ሊደርስ የሚችል ሲሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርጉትን ማንም አይነቅፉቸውም:: በማዕበል የሚማቱትና የሚናወጹት ሊወድቁ ሲሆን፣ ያውም በውቅያኖስ ሳይሆን በእሳት ጥልቅ ውስጥ ሊወድቁ ሲሆን፣ የሚጠብቃቸው ሞትም ነፍስን ከሥጋ የሚለየው ሞት ሳይሆን ከዚህ ጋር አብሮ ወደ ዘለዓለም ቅጣት የሚያስጥል ሲሆን እንዲህ ወዳለ ታላቅ ክፉ ነገር ስላልሰጠምኩኝ የአንተ ቁጣና ጥላቻ ሊደርስብኝ ይገባልን?

፰. ስለዚህ እንዲህ አታድርግ፣ ወንድሜ ሆይ እማልድሃለሁ፣ እማጸንሃለሁም:: ምን ያህል ደካማ መሆኔን የራሴን ነፍስ አውቃታለሁ፤ የዚህን አገልግሎት መጠንና የሥራውን ከባድነትና አስቸጋሪነት አውቃለሁ፤ የካህኑን ነፍስ ባሕሩን ከሚያውኩት ማዕበላት የበለጡ ከባድ ወጀቦች ያውኩታልና::

፱. በመጀመሪያ በጣም አስቀያሚና እጅግ አደገኛ የሆነው የውዳሴ ከንቱ (የራስን ክብር፣ ምስጋና መፈለግ) ነገር ነው:: ሆኖም አሁን ምንም ወደዚያ የሚገፋኝ ነገር እንኳ ሳይኖር ከዚህ ወጥመድ ራሴን ሙሉ በሙሉ ንጹሕና ነጻ አድርጌ መጠበቅ አልቻልሁምና:: ነገር ግን ይህን ጉዳይ ለእኔ የሚሰጠኝ ሰው ቢኖር እጆቼን ወደ ኋላዬ አሳስሮ በየቀኑ ይቦጫጭቁኝ ዘንድ በጫካ ለሚኖሩ አውሬዎች ከመስጠት ጋር አንድ ነው:: እነዚህ የዱር አራዊት እነማን እንደ ሆኑ ማወቅ ትፈልጋለህ?

እነዚህ ቁጣ፣ ብስጭት፣ ቅንዓት፣ ሽኩቻ፣ ስም ማጥፋት፣ ሐሜት፣ መነቃቀፍ፣ መዋሸት፣ አስመሳይነት፣ ግብዝነት፣ ዓድማ፣ ሤራ ጉንጎና፣ ምንም ጉዳት ባላደረሱትና ባላጠፉት ላይ መቆጣት፣ በሌሎች ካህናት የማይገባ ድርጊት መደሰት፣ በእነርሱ መልካም መሆንና ደኅንነት ማዘንና መበሳጨት፣ መወደስንና መመስገንን መውደድ፣ ክብርን መሻት፣ ሰዎችን ለማስደሰትና በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትን ለማግኘት ሲባል የሚዘጋጁ ትምህርቶችና አስተምህሮዎች፣ የእወደድ ባይነትና የአድር ባይነት ቁልምጫዎች፣ አሳፋሪ የሆኑ ሙገሳዎች፣ ድሆችን መናቅና ማቃለል፣ ባለ ጸጋዎችን መጎብኘትና የተለየ ቦታ መስጠት፣ በከንቱ መደንገጥና መፍራት፣ ቅንና ቀጥተኛ ንግግርን መጥላትና መጣል፣ እውነትን መጥላትና ማራቅ፣ ተግሣጽንና ስሕተትን መነጋገርን መጥላትና እንዳይኖር ማድረግ፣ ወይም ደግሞ እነዚህን በድሆች ላይ ከመጠን በላይ መጠቀም፣ በባለ ጸጎችና በባለ ሥልጣናት ላይ ግን ማንም ከንፈሩን ሊያንቀሳቅስ አለመድፈር ናቸው::

እነዚህ ሁሉ ክፉ አውሬዎች፣ ከእነዚህም በላይ የሆኑ ሌሎችም በዚህ ቀድም ብዬ ባልሁት ክፉ ዓለት ሥር ተደብቀው የሚራቡ ሲሆኑ እንዲህ ባለ ባርነት የተያዙ ሰዎች ሴቶችን ለማስደሰት ስንኳ ሳይቀር ባይገልጹዋቸው ወደሚሻሉ ብዙ ነገሮችን እስከ ማድረግ ወደ ሚያደርስ ጥልቅ ባርነትና ጉስቍልና ተስበው መወረዳቸው አይቀሬ ነው::

መለኮታዊ ሕግ ሴቶችን ከዚህ አገልግሎት (ከክህነት) ውጭ አድርጎአቸዋል:: እነርሱ ግን ራሳቸውን ወደዚህ ለማስጠጋት ይፈልጋሉ:: በራሳቸው በቀጥታ ምንም ማድረግ ስለማይችሉ ማድረግ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ በሌሎች ወኪሎቻቸው አማካይነት ያስፈጽማሉ:: እንዲሁም ካህናትን በእነርሱ ፈቃድ ማስ-ሾምም ሆነ ማሻርና ማባረር የሚችሉ እስከ መሆን ደርሰው ዋና አድራጊ ፈጣሪዎችና እንደ ፈለጉ የማድረግ ኃይል ያላቸው ሆነዋል:: በርግጥ ነገሮች ተገለባብጠዋል፤ «ተመሪዎቹ መሪዎቹን ይመራቸዋል» የተባለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሲፈጸም ይታያል:: ይህን የሚያደርጉትም ማስተማር ያልተፈቀደላቸው ሴቶች ናቸው:: ለምን ማስተማር እላለሁ? ቅዱስ ጳውሎስ በቤተክርስቲያን እንዲናገሩ እንኳ አላሰናበታቸውምና:: (፩ቆሮ.፲፬፥፴፬፤ ፩ጢሞ.፪፥፲፪) ሆኖም ግን የቤተክርስቲያንን ጳጳሳትና ካህናት ጌቶች አገልጋዮቻቸውን ከሚገሥፁበት ተግሣፅና ቁጣ በጠነከረና በከፋ ሁኔታ እስከ መገሠፅ





www.eotcmk.org

እስኪደርሱ ድረስ መጠን አለፍ የሆነ ልቅ የመናገር ነጻነትን አንደበታቸው ገንዘብ እንዳደረገ አንዱ ሲናገር ሰምቻለሁ።

፲. ሁሉንም ለእነዚህ ለተባሉት ነገሮች ጥፋተኛና ተጠያቂ እንዳደረግሁ አድርጎ የሚያስብና የሚረዳ አይኑር፤ ከእነዚህ መሰናክሎች በላይ የሆኑ ልዑላነ አእምሮ ወመንፈስ የሆኑ ብዙዎች፣ ቁጥራቸውም በዚህ ወጥመድ ከወደቁት የበለጠ የሆኑ አሉና። እንዲሁም ክህነትን ለእነዚህ ክፋቶች ተጠያቂ የማደርገው አይደለም፤ እንዲህ ያለው እብደት ከእኔ ይራቅ። ነገሮችን በትክክል የሚረዱ ሰዎች ለግድያ ተወቃሹ ሰይፍ፣ ለስካርም ወይን፣ ኃይልም ለቁጣና ጠብ፣ ወኔ (courage) ለቂላቂልነት ተጠያቂዎች ናቸው አይሉም። ነገር ግን ጥፋተኛነቱን በእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ስጦታ በአግባቡ ባልተጠቀሙባቸው ሰዎች ላይ ያደርጋሉ። ለጥፋተኛነታቸው የሚገባቸውን ተገቢውን ቅጣትም ይቀጧቸዋል።

ክህነትም እንዲሁ በአግባቡ ካልያዝነው በትክክል ያስጠይቀናል። ለተጠቀሱት ክፉ ነገሮች ምክንያቱ ክህነት በራሱ አይደለም፣ በብዙ ርኩሰት ያዋረድነውና ያረከስነው ተቀባዮቹ እኛ ነን። መጀመሪያ የራሳቸውን ድኅነት በተመለከተ ምንም ትምህርት ላልተማሩ፣ ዕውቀት ለሌላቸው፣ የክህነትን ከባድነት ለማያዉቁ፣ የተሰጣቸውን እሽ ብለው ለሚቀበሉ፣ ከዚያም በዕውቀት እጥረትና በልምድ ማጣት በመታወር ወደ ሥራው ሲገቡ ሊጠብቋቸው ሓላፊነት የተሰጣቸውን ሕዝብ ስፍር ቁጥር በሌለው የማይገባና ክፉ ነገር ግራ ለሚያጋቡ፣ የሰጧቸውን ሁሉ እሽ ብለው ለሚቀበሉ ተራ ሰዎች የምንሰጠው እኛ ነን።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ቤተ ክርስቲያኑንና የእኔንም ነፍስ በማትረፍ ከእነዚህ አደጋዎች ፈጥኖ ባያተርፈኝ ኖሮ በእኔ ላይ ሊደርስ የነበረውም ይኸው ነበር። እስኪ ንገረኝ! በቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያሉ ታላቅ ችግሮች የሚመጡት ከየት ይመስልሃል? እንደ እኔ የእነዚህ ብቸኛ ምንጫቸው ጳጳሳትና ካህናት የሚመረጡበት መንገድ ጥንቃቄ የጎደለውና እንዲሁ በዘፈቀደ መሆኑ ነው።

ከእርሱ በታች ካሉ ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች የሚመነጨውን ክፉና ደካማ ሐሳብ ለመግዛትና ለመቆጣጠር ይችል ዘንድ ራስ ከሁሉም በላይ ጠንካራና ጽኑዕ ሊሆን ይገባዋልና። ራስ ደካማ ከሆነና እነዚህን ለመቆጣጠር ካልቻለ ግን ራስም ደካማ ከሆኑት አካላት የባሰ ደካማ ይሆናል። ሌላውን የሰውነት ክፍልም ያጠፋል። አሁን ይህ እንዳይፈጸም እግዚአብሔር እኔን ቀድሞ በተሰጠኝ ደረጃዬ በእግርነቴ እንድቀጥል አደረገኝ።

> *ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች የሚመነጨውን ክፉና ደካማ ሐሳብ ለመግዛትና ለመቆጣጠር ይችል ዘንድ ራስ ከሁሉም በላይ ጠንካራና ጽኑዕ ሊሆን ይገባዋልና። ራስ ደካማ ከሆነና እነዚህን ለመቆጣጠር ካልቻለ ግን ራስም ደካማ ከሆኑት አካላት የባሰ ደካማ ይሆናል። ሌላውን የሰውነት ክፍልም ያጠፋል። አሁን ይህ እንዳይፈጸም እግዚአብሔር እኔን ቀድሞ በተሰጠኝ ደረጃዬ በእግርነቴ እንድቀጥል አደረገኝ*

ባስልዮስ ሆይ፣ አንድ ካህን ሊኖረው የሚገቡ፣ እኔ ግን የሌለኝ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሌሎች እጅግ ብዙ የሆኑ ችሎታዎች አሉና። በተለይም ደግሞ ከሁሉም በላይ ነፍሱ ይህን ሹመትና ክብር ከመሻትና ከመመኘት ፈጽሞ የነጻችና የጸዳች ልትሆን ይገባል። ለዚህ ክብር ውሳጣዊ ዝንባሌና ፍላጎት ያለው ከሆነ ሹመቱን እንዳገኘው ወዲያውኑ ሙሉ በሙሉ በሹመቱ ፍቅር ቁጥጥር ሥር ይሆንና ይህን ሥልጣኑን አስተማማኝ ለማድረግ፣ ለማስጠበቅ ማቆላመጥን እስከ መጠቀም ወይም አሳፋሪና የወረደ ወደ ሆነ ነገር ራሱን ዝቅ ማድረግን ወይም ብዙ ገንዘብ እስከ መበተን ደርሶ ስፍር ቁጥር የሌለው ክፉ ነገር ውስጥ ይዘፈቃል። ለዚህ ክብር ሲሽቀዳደሙና ሲቀናቀኑ አንዳንዶች በአብያተ ክርስቲያናት ስላደረሱት መገዳደል ወይም በከተማዎች ላይ ስላደረሱት ጥፋት አሁን አልናገርም። ለአንዳንዶች ሰዎች እየተናገርሁት ያለሁት ነገር ሊታመን የማይችል እንዳይመስላቸው ነው። የእኔ አመለካከት ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባ እንደሆነና የዚህን ሓላፊነት ሸክም ሊፈራውና ገና ከመጀመሪያው አልችልም፣ አይሆንልኝም ብሎ ሊሸሸው ይገባል፤ ከገባበት በኋላም ቢሆን ሊያስወርደው የሚችል ችግር ቢፈጠር ሌሎች እስከሚፈርዱበት ሳይጠብቅ ራሱን በማውረድ አስቀድሞ ከሌሎች በፊት በራሱ ላይ መፍረድ ይገባል የሚል ነው። በዚህም ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ሊያገኝ ይችል ይሆናል። ከትሕትናና ሊሆን ከሚገባው ነገር ወጥቶ በዓመፅ መንገድ የሙጥኝ ማለት ግን ራስን ከይቅርታ ሁሉ ማራቆት ነው። እንዲያውም ከመጀመሪያው የባሰ አስጸያፊ ስሕተት ውስጥ በመጨመር የእግዚአብሔርን ቁጣ ማቀጣጠል ነው።

፲፩. ነገር ግን ይህን ሕማም ማንም ሁል ጊዜ አይችለውም፤ የዚህ ሹመትና ክብር ፍቅር በእውነት አስፈሪ ነውና። ይህን በማለቴ ቅዱስ ጳዉሎስን የምቃወም አይደለሁም፤ ከእርሱ ቃላት ጋር በፍጹም የምስማማ እንጂ። እርሱ ምን አለ? «ማንም ጵጵስናን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል» (፩ጢሞ. ፫፥፩) እኔ ሥራን መፈለግ መጥፎ ነገር ነው አላልሁም፣ ከዚያ የሚገኘውን ሥልጣኑንና ክብሩን መፈለግን እንጂ። ስለዚህ ይህን የሥልጣንና የክብር ፍላጎት እንዲህ ዓይነት ስሜት እንዳይገዛው ገና ከመጀመሪያው ከውስጡ ማራቅና ማባረር ይኖርበታል፤ ማንኛውንም ነገር በነጻነት ማድረግ ይችል ዘንድ። የክህነት ሥልጣን ምኞቱ የሌለውና በዚህ ሹመት ሆኖ መታየት የማይፈልግ ሰው ቢሾምም ያንን ከማጣትና ከመውረድ አይፈራም፤ አይሳቀቅምም። ይህን ባለመፍራትም ለክርስቲያኖች ነጻነት እንደሚገባ ሥራውን በፍጹም ነጻነት ያከናውናል። በዚህም ያለ ፍርሃትና ያለ ሥጋት ማንኛውንም ነገር ለክርስቲያኖች እንደሚገባ ያከናውናል። ሹመታቸውን እንዳያጡ የሚፈሩና የሚጨነቁ ግን በክፋት ነገር ሁሉ ይመሉና መራራ ባርነት ላይ ይወድቃሉ፤ ሰውንም እግዚአብሔርንም ወደ ማሳዘን አስገዳጅ ሁኔታ ይደርሳሉ።

ነፍስ እንዲህ ባለ ሁኔታ ልትዘፈቅ አይገባትም። ነገር ግን በጦርነት ላይ ልዑላነ መንፈስ የሆኑ ወታደሮች በፈቃዳቸው ተዋግተው በጀግንነትና በክብር እንደሚወድቁ ሁሉ ወደዚህ ሓላፊነት የመጡ ሰዎችም ቢሾሙም ወይም ደግሞ ከመንበራቸው ቢባረሩም እንዲህ ያለው ከመንበር መውረድና መባረር የክህነትን ሥራ በአግባቡ ከመፈጸም ያላነሰ ክብርና ዋጋ ያለው መሆኑን በማወቅ ለክርስቲያን ሰው እንደሚገባ እኩል ደስተኞች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ማንም ለዚህ ክብር ወደማይገባ /የወረደና የዘቀጠ ነገር/ ባለማጎንበሱ እንዲህ ዓይነት ነገር ቢደርስበት ያለ አግባብ ከመንበሩ ለሚያወርዱት ሰዎች ቅጣትን ያመጣባቸዋል፤ ለራሱም ታላቅ ክብርን ያገኛል። ጌታችን «ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሐሴትም አድርጉ» ብሏልና። (ማቴ ፭፥፲፩-፲፪) እንደ እርሱ ያለ መዓርግ ባላቸውና እኩያዎቹ (በመዓርግ) በሆኑ ሰዎች በቅናትም ይሁን ክብሩን

ወደ ገጽ ፴፭ ዞሯል



www.eotcmk.org

## ለኔ ነው እንባ የሚያሻው /ቁጥር ፫/

የቀናው ጉዞዬ - ፍኖቴ ሲጣመም፣
በልጅነት ገዳም - በ'ርጅና ወደ ዓለም።
ቋርፍ ግጦ ማደር ጾም፣ጸሎቴን ለተውኩ፣
ሥጋና መሻቷን! -
ከሰቀልኩበቱ - አውርጄ ለለበስኩ፤
ለኔ እንጂ እየዬ - ማቅ ለብሶ መባጀት፣
'ወዮ!' ብሎ ማዝራት - እንባን እንደ ጅረት።

የላመ፣ የጣመ - ብልጭልጩ ማርኮኝ፣
መቁነኔን ለገፋሁ- በአቴን ለጣልኩኝ፤
ቀሚሴን አርዝሜ - ቆቤን አንጋድጄ፣
ሳይወድቅ አይቀር ሆኜ- እኔው ተንጋድጄ፤
ወበ ከንቱ ለሆንኩ!!
በደም የጸናውን - ሕግ ለተላለፍኩ፤
ለኔ ነው የሚያሻው - ማረኝ ብሎ መውደቅ፣
ቸርነቱን አምኖ - በእንባ ለመታረቅ።

ፍትፍትሽ፣ ዝልዝልሽ- 'ዓለም ባንቺ'ን ለማልኩ፣
ከቀለጠው መንደር - ከተማ 'ለገደምኩ'፣
ወርቄን ጠጠር ብዬ - መክሊቴን ላቀለልኩ፣
መካኔን፣ ደብሬን - ገዳሜን ላስደፈርኩ፤
ለ'ኔ እንጅ እየዬ - ልብን የሚያወዛ፣
ከበአት የሚያኖር - አደብ የሚያስገዛ።

*አንዱዓለም አባተ*
*ደብረ ብርሃን*

### እቴጌዪቱ

ስሟ ጣይቱ የግእዝ ቋንቋ፣
ዐማርኛዋም ኮከብ ጨረቃ፤
ፊደሏ ብርሃን ዘእምብርሃን
ሰባት ቁልጭልጭ የግዜር በግ ዐይን
ግእዝ ግእዙ ወርቅ ቀለም፣
ባለ ፯ ዐጽቅ ጉንደ ተቋም፤
ስድስቱም ዐጽቆች ግራና ቀኙ፣
ከሱራፌል ክንፍ የተሰናኙ፤
ከኪሩቤልም ካራቱ ኹሉ፣
በራብዕ ትውልድ ይዛመዳሉ።
ከአዳም ከኖኅ ካባት ከናቷ፣
ለሴም የታጨች ስለ ውበቷ፤
ከንጉሥም ከግዜር ከባለቤቱ፣
ስለ ተሰጣት እቴጌነቱ፤
ምንም ቢያጅቧት መኳንንቶች፣
ዐይኗና ልቧ ከተማሮች።
እንዲህ ብታይዋት ድኻ መስላችኹ፣
ባለ ጸጋ ናት ግእዝ ቋንቋችኹ።
ባዕዶቹ ነሜች ሲሻሙባት
ምነው እናንተ የማትደፍሯት፤
ደፈሩኝ ብላም እንዳትከሳችኹ፣
እኔ ስለርሷ ልማልላችኹ።

*ምንጭ፦ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም፤ ገጽ. ፻፹፬*

### ምክር ከዲድስቅልያ

- «ነፍስ ከሥጋ እንድትበልጥ ክህነትም ከመንግሥት ትበልጣለች /አስመ ተዓቢ ነፍስ እም ሥጋ ወክህነት ተዓቢ እ መንግሥት/» */ዲድስቅልያ አንቀጽ ፱ቁጥር ፳፫/*
- «ከስንፍና ራቁ! ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሰነፎችን ይጠላልና» */ዲድስቅልያ አንቀጽ ፲፪ ቁጥር ፳፫/*
- «አንተ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሰው /ወንድም/ ሆይ የራስህን ጠጉር አታሳድግ፣ ወገኖ፣ ስሉስ አትሠራ፤ ጉንጉን አትታታ፤ ይህ ሁሉ የዝሙት ኃጢአት ምልክት ነውና።» */ዲድስቅልያ አንቀጽ ፩ ቁጥር ፶፫/*
- «ሥራ ፈት ሆነህ አትኑር» */ዲድስቅልያ አንቀጽ ፪ ቁጥር ፩/*
- «ብዙ የወይን ጠጅ ጠጥታችሁ የምትሰክሩ... ዘፋኞች፣ ነፍስ ገዳዮች፣ መማለጃ ጉቦ የምትቀበሉ አትሁኑ» */ዲድስቅልያ አንቀጽ ፮ ቁጥር ፳፲/* ❖

*ዲ/ን ኪዳነ ወልድ ኃይለ ጊዮርጊስ*
*ከደብረ ገሊላ ቅ/አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን*
*አዲስ አበባ*

### አንቺም ከዳሽኝ

አቡነ አሮን በ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ቅዱስ ናቸው። የአባታቸው ስም ገብረ መስቀል የእናታቸው ስም አመተ ማርያም ይባላል። ነዳያንን በመርዳት የታወቁ መሆናቸውን ገድለ አሮን ይተርካል። በአንድ ወቅት አቡነ አሮን ከዐፄ ሰይፈ አርእድ ጋር እርቅ ከመሠረቱ በኋላ ወደ ዳውንት ተጓዙ። ወደ ደብረ ቀጢን ለመድረስ መንገዱ ረጅም በመሆኑ ቶሎ መድረስ አልቻሉም። ገና ብዙ ርቀት ይቀራቸው ነበር። ፀሐይ እያቆለቆለች ሔደች። በዚህ ጊዜ አቡነ አሮን ወደ ፀሐይ ዓይናቸውን አቅንተው አንቺም ከዳሽኝ? አሏት። በዚያው አገሩ «አንቺም» ተባለ። ከዚያም ወደ ደብረ ቀጢን እስክንገባ ፀሐይ ጠብቂን ብለው አዘዟት። በሠርክም ወደ ገዳማቸው ደረሱ። ያዳፈኑት እሳት ሳይጠፋ፣ ያቦኩት ሊጥ ሳይበላሽ ማግኘታቸውን ገድሉ ይተርካል። ምሽት ላይ አንዱ ተማሪያቸው ፀሐይ እንደ ቆመች አይቶ ለአቡነ አሮን ስለነገራቸው እንድትገባ አደረጓት።

*/የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፤ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት፤ ገጽ. ፩፻፹፩/*

### ብሒስ አበው

- «እውነተኛ የብቃት ሕይወት እንደ ባሮች ቅጣትን ከመጥላት የተነሣ ክፉ ነገርን ማስወገድ ወይም ሽልማትን ተስፋ በማድረግ ምክንያት መልካምን ሥራ መሥራት አይደለም»

*./ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ/*

- «ከሰው ርቆ በብሕትውና የሚኖር ሰው ከሦስት ፈተናዎች መራቅ ይችላል፡ ከማየት፣ ከመናገር፣ ከመስማት፤ ለርሱ የሚቀረው ፈተና አንድ ነው፤ ያም የፍትወት ፆር ነው።»

*/አባ መቃርስ/*



' www.eotcmk.org

# በጆሮአችን የሰማነውን በዐይናችን አየነው

**ጌታቸው በቀለና መ/ር ሳሙኤል ተስፋዬ**

በምዕራብ ኢትዮጵያ የምትገኘው ጅማ ከአዲስ አበባ ፫፻፶ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ጅማ በያዝነው ዓመት ፻፸፰ ዓመቷን አክብራለች፡፡ እኛም ጅማ በዚህ የደስታ መንፈስ ውስጥ በነበረችበት ወራት የካቲት ፳ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም ወደዚያው ተጉዘን ነበር፡፡ በዚሁ ቀን ከቀኑ 10:00 ሰዓት አካባቢ እንደደረስን ሻንጣችንን ይዘን ወደ ጅማ ማዕከል ማኅበረ ቅዱሳን ሱቅ ሄድን፡፡ ከመንፈሳዊ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሰላምታ ከተሰጣጣን በኋላ መስተንግዶ አደረጉልን፡፡ ከዚያም ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት ተጓዝን፡፡ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አባታችን አቡነ እስጢፋኖስ ቡራኬ ተቀብለን ስለ ዘገባችን ተነጋግረን፤ ብፁዕ አባታችንም ጠዋት እንድንመጣ ቀጠሩን ከዚያም ወደ ማደሪያችን ሔድን፡፡ በማግስቱ 3:00 ሰዓት በሀገረ ስብከቱ ግቢ ተገናኝተን ቡራኬ ተቀብለን ዘገባችንን አሐዱ አልን፡፡

የሀገረ ስብከቱ ሠራተኞችም ሆኑ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ አቀባበል በማድረግ፣ መኪና በመመደብ፣ ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ መኪና መግባት በማይችልባቸው ቦታዎች ሳይቀር ብፁዕነታቸው በእግራቸው ከእኛ ጋር ተጉዘው ላደረጉልን ቀና ትብብር ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

የጅማ ሀገረ ስብከት እንደተመለከትነው ጠንካራ የልማት ሥራዎች የሚሠሩበት አካባቢ ነው፡፡ በልማት ጠንካራ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ሁሉ በካህናት እጥረት የተነሣ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትም አሉ፡፡ በሌላ ጎኑ ደግሞ የሙስሊሙ እንቅስቃሴ፣ የመናፍቃኑ ወረራ በስፋት የሚታይበት አካባቢ ነው፡፡ ችግሩ ፈርጀ ብዙ ነው፡፡ ብፁዕነታቸውም ቀን ዕረፍት፣ ሌሊት እንቅልፍ ሳያምራቸው ችግሩን ለመቅረፍ ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች ጋር ሲጥሩ ይውላሉ፡፡ ከአንደበታቸው ዘወትር የሚደመጠው የቤተክርስቲያን ነገር ነው፤ ልማት ነው፤ እውነትም ልማት አስብለውናል፡፡ እነሆ፡፡

## የሀገረ ስብከቱ ልማትና ፈተናዎቹ

በጅማ ሀገረ ስብከት ፪፻፷ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት በጅማ ከተማና በወረዳ ከተሞች እንዲሁም በመኪና መስመር ዳር አካባቢ የሚገኙ ፩፻፲ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ፩፻፳ው አብያተ ክርስቲያናት ግን በካህናት እጥረት የተነሣ አገልግሎት አይሰጡም፤ ተዘግተዋል፡፡

በጠባቂ እጦት የተነሣ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ባይፈርስም በሊሙ ኮሳና በጢሮ አፈታ ወረዳ በግለሰብ ቤት ሳይቀር የተቀመጡ ታቦታት እንዳሉ ብፁዕ ታቸው ገልጸውልናል፡፡

በጅማም ሆነ በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ካህናት የሚመጡት ከሰሜኑና ከመሀል የሀገራችን ክፍል መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተለይ በጅማ በመስከረም ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም የክርስቲያኖች መጨፍጨፍና የአብያተ ክርስቲያናቱ መቃጠል ወዲህ ግን ሁኔታዎች ተቀይረዋል፡፡ በርካታ ካህናት በወቅቱ በተከሰተው ችግር ከዚያም በኋላ በሚታዩ አንዳንድ ድርጊቶች አብያተ ክርስቲያናቱን እየዘጉ ወደ የመጡበት ሄደዋል፡፡ ሀገረ ስብከቱ ይህን ችግር ለመቅረፍ የአካባቢውን ቋንቋ የሚያውቁ አገልጋዮችን ማሠልጠን ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ መሆኑን በመገንዘቡ ፪፻፵ ሰዎችን ማሠልጠን የሚችል ዘመናዊ የካህናት ማሠልጠኛ ሠርቷል፡፡ «ስሙ የካህናት ማሠልጠኛ አልነው እንጂ ካህናት ከየት መጥተው ይሠለጥናሉ? ቢጨንቀን የተዘጉትን አብያተ ክርስቲያናት ለማስከፈት ብለን በአካባቢው በጎ ፈቃድ ያላቸው ቋንቋውን የሚያውቁ በሰንበት ት/ቤት ያደጉና ፈቃደኛ የሆኑ ወጣቶች ለማሠልጠን ዐቅደን ነበር» የሠራነው ይላሉ፤ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ፡፡

ሀገረ ስብከቱ ወደ አበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም ፵ ዲያቆናትን በማስገባት እያሠለጠነ ነው፡፡ ብፁዕነታቸው በዚህ ቦታ የሚያስፈልጉትንም ካህናት «በቤተክርስቲያን የሚቀድሱ፣ የሚያስተምሩ የማኅሌት አገልግሎትም ሊሰጡ የሚችሉ መሆን አለባቸው» ይላሉ፡፡

በአስተርጓሚ ንስሐ የምንገባው እስከ መቼ ነው? የሚል ጥያቄ እየጠየቁ ያሉ ምእመናን አሉ፡፡ ብፁዕነታቸው «በአስተርጓሚ ንስሐ መቀበል አይቻልም፡፡ የሀገረ ስብከቱ መፍጨርጨር ብቻ ችግሩን ሊፈታው አይችልም፤ ሁላችንም ተባብረን የአብያተ ክርስቲያናቱን ችግር መፍታት ካልቻልን ከጥቂት ዓመታት በኋላ በዚህ አካባቢ ቤተክርስቲያን ነበረች የሚባልበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም» በማለት ነበር ስጋታቸውን የገለጹት፡፡

የሀገረ ስብከቱን የልማት እንቅስቃሴ ከብፁዕነታቸው ጋር ተዘዋውረን ለመመልከት አሐዱ ብለን የጀመርነው በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በ ፵ ቀን ከተሠራው በቅዱስ



ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ

ዑራኤል እና በአባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ ቤተክርስቲያኑ በጥሩ ሁኔታ የታነጸ ነው፡፡ ቅድስቱና ቅኔ ማኅሌቱ በቅዱሳት ሥዕላት የተሞላ ነው፡፡ በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ሰፊ መሬት አለው፡፡ በአጠገቡም ዘመናዊ የካህናት ማሠልጠኛ ሕንጻ ተገንብቷል፡፡ ወደፊት ዘመናዊ ቤተ መጻሕፍት ያለው ኮሌጅ፣ የሕፃናት ማሳደጊያ፣ የአረጋውያን መጦሪያን የሚያካትት እንደሚሆን ተረድተናል፡፡

ከማሠልጠኛው በስተግራ በኩል የሀገረ ስብከቱን የልማት እንቅስቃሴ የሚያሳየው የተግባረ ዕድ ውጤቶች የሚመረቱበት ድርጅት ይገኛል፡፡ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጽ፣ ለቤትና ለቢሮ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ይሠራሉ፡፡ «ከማሠልጠኛው አጠገብ ማምረቻ ድርጅት የከፈትነው ካህናቱ ከትምህርታቸው በተጓዳኝ በሙያም እንዲሠለጥኑ ለማድረግ ነው» በማለት ብፁዕነታቸው ገልጸውልናል፡፡ ይህን ዓይተን ያቀናነው በመንበረ ጵጵስና ግቢ ወደሚገኘው ተስፋ ተዋሕዶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር፡፡

ዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ከመግባቱ አስቀድሞ ለበርካታ ዓመታት የሀገሪቱን የትምህርት ሚኒስቴርነት ሥፍራ ይዛ የቆየች፣ ሕዝቡን ከማይምነት ጨለማ ስትታደግ የኖረች፣ ብርዕ ቀርጻ ቀለም በጥብጣ ብራና ዳምጣ ታሪክ ሃይማኖት ጽፋ ያስቀመጠች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ቤተክርስቲያንም ዕውቀት ሽተው ወደ እርሷ የሚመጡትን ሰዎች በዕውቀት አበልጽጋ በምግባር ኮትኩታ፣ በሀገር ፍቅር ገንብታ ታሳድጋቸው



www.eotcmk.org

እንደነበር ሁሉ ዛሬም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ፲፪ኛ ክፍል ድረስ የሚዘልቁ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ላይ ይገኛሉ:: ከእነዚህም አንዱ በጅማ ሀገረ ስብከት የሚገኘው የተስፋ ተዋሕዶ ትምህርት ቤት ነው::

«ተስፋ ተዋሕዶ» አጸደ ሕፃናት እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተቋቋመው በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ጥረት ነው:: ትምህርት ቤቱ በሁለት ወር ውስጥ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ነው:: ትምህርት ቤቱ በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አለው፤ በርካታ ተማሪዎችንም በማስተማር ላይ ይገኛል:: ብፁዕነታቸው ለትምህርት ቤቱ መስፋፋት ካላቸው ፍላጎት የተነሣ ቢሮአቸውን ወደ ትምህርት ቤቱ እንዲቀየር እስከ ማድረግ ደርሰዋል:: የትምህርት ቤት ክፍያውም የኅብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ መሆኑን የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር መምህር ምትኩ ፍሪሳ ገልጸልናል:: ሀገረ ስብከቱ ከያዛቸው ልማቶች አንዱ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት በመሆኑ ከጅማ ከተማ ወጣ ብለው በሚገኙ የወረዳ ከተሞች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት /በሠኮሩ፣ በደነባ፣ በአጋሮና በዴዶ/ ትምህርት ቤት ከፍተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ::

ከሰዓት በኋላ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ የደብረ ሣህል ቅዱስ ማካኤል ቤተክርስቲያንን፣ የመረዋ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት የእርሻ ልማትና ሸዋበር ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያንን አስጎበኙን::

በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የተመሠረተው የደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ፸፯ ሺሕ ካሬ ሜትር ስፋት ይዞታ አለው:: ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩበት ወቅት ለጅማ ሕዝበ ክርስቲያን የመቃብር ቦታ እንዲሆን የታሰበ ነበር:: የቀድሞ ታሪኩን ስንመለከት ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት የደብረ መዊዕ መድኃኔዓለም ታቦት በስደት ወደ ዚህ ቦታ መጥቶ ተቀምጦ ነበር:: የፋሺስት ኢጣሊያ መንግሥት ከሀገራችን ድል ሆኖ ከወጣ በኋላ ታቦተ ሕጉ ወደ ቦታው ሲመለስ፤ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እንደተሠራ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ አስረ ድተውናል:: በተጨማሪም ካቴድራሉና በጅማ ከተማ የሚገኙ አድባራት እቁብ በመሰብሰብ በየተራ አንድ የልማት ሥራ የሚሠሩ ሲሆን በዚህም መሠረት በካቴ ድራሉ አጸደ ሕፃናትና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት መሠራቱን የተመለከትን ሲሆን በቀጣዩ ሌሎች አድባራት እቁቡ ሲደርሳቸው በመረጡት ፕሮጀክት መሠረት የልማት ሥራ ይሠራሉ::

ከዚያም መረዋ ወደ ሚገኘው የአቡነ ተክለ ሃይማኖትና የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ገዳም የእርሻ ልማት አቀናን:: በዚህም ታላቅ የልማት ሥራ አለ:: በ፲፱፻፹ ዓ.ም አምስት ሔክታር መሬት ከመንግሥት ተረክበው የከብት ርባታ ከፍተዋል፤ በቆሎ፣ ጤፍም... ያመርታሉ፤ ይሸጣሉ::

ለቤተክርስቲያኗ ጥሩ ገቢ ያስገኛሉ:: በዚህ ለሚያስፈልጋቸው አገልግሎት ይጠቀማሉ፣ በገዳሙ ላሉት ለአብነት መምህራን ደመወዝ በመክፈል ተተኪ ሊቃውንት እያፈሩ ይገኛሉ::

በቀጣዩ ዕለትም ከጅማ በስተደቡብ አቅጣጫ ፴ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው ዴዶ ወረዳ ተጓዝን:: የመጥሰ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን የተመሠረተው በ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ነው:: ቀደም ሲል ስብሐተ ነግህና ቅዳሴ አይታጎልበትም ነበር:: አሁን ግን በካህናት እጦት የተነሣ የሚቀደሰው በዓመት አንዴ ወይም ሁለቴ ብቻ ነው፤ ያውም ካህን ከተገኘ:: በአጥቢያው የሚገኙም አባወራዎችም ከ፴ የማይበልጡ ናቸው:: ወደ ቤተክርስቲያኑ ዘልቀን በዐውደ ምሕረቱ ላይ ተሰብስበው ወደ ተቀመጡ ከዐሥር የማይበልጡ ምእመናን አቀናን:: ደስተኞች አይደሉም፣ ገጻቸው ይናገራል በአግራሞት ነበር የሚመለከቱን ለችግራቸው የደረስንላቸው፣ ካህን ይዘን የመጣንላቸው ነበር የመሰላቸው:: ምእመናኑ በቂ አገልግሎት፣ አያገኙም:: የተደራረበ ችግርም ያለበት ቦታ ነው:: ሰበካ ጉባኤውም የሀገሪቱን ሕዝበ ክርስቲያን ድጋፍ በጽኑ ይፈልጋል:: መልአከ ገነት ፍሬ ጽድቅ ክርስቲያኑን ለማጽናናት ትምህርት አስተማሩ::

በ፳፻ ዓ.ም የጥምቀት ዋዜማ የከተራ ዕለት ታቦቱን የሚያወጣ ካህን በመጥፋቱ ምእመናን ከቤተክርስቲያኑ ቅጽር ተሰብስበው አልቅሰው ተለያይተው በድንገት አንድ ዜና ሰሙ፤ ከጅማ መድኃኔዓለም አንድ ዲያቆንና አንድ ካህን መጥተው ድልቢ ያለውን ታቦት ሊያወጡ ነው የሚል:: ካህናቱም ገስግሰው ወደ መጥሰ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን መጡ:: ሕዝበ ክርስቲያኑም ከየቤታቸው ተሰባስበው ከደስታቸው የተነሣ አነቡ:: ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ታቦቱን አወጡ:: ካህኑ በማግስቱ ዴዶ ሄደው ታቦቱን አስገብተው ተመልሰው መጥሰ መጥተው ታቦቱን አስገብተዋል:: አንድ ካህን ሁለት ቦታ በተለያየ ርቀት ላይ ሲያገለግሉ ማየት ያሳዝናል::

ቤተክርስቲያኑ ጥገና ተደርጎለት ስለ ማያውቅ ጣሪያው ያፈሳል፣ ግድግዳው በምስጥ ተበልቷል:: የሣር ጉዝጓዝ ስለሆነ የጧፍ እሳት ቢወድቅበት ቤተክርስቲያኑ በቀላሉ መቃጠል የሚችልበት ሁኔታ ከፍተኛ ነው::

ከዚያም ተመልሰን ወደ ዴዶ ከተማ ተጓዝን:: በዚህ ደግሞ ያለው ሁኔታ አሳዛኝ ነው:: በዴዶ ወረዳ ካሉት ፲፱ አብያተ ክርስቲያናት ፲፰ቱ በካህናት እጦት የተዘጉ ናቸው:: በከፊልም ቢሆን አገልግሎት እየሰጠ ያለው የዴዶ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ብቻ ነው:: የቤተክርስቲያኑ ሕንጻ ግድግዳው ተሰነጣጥቆ ጣሪያውን የተሸከሙት ምሰሶዎች ለመውደቅ ዘመው ይታያሉ:: ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል መገመት አያዳግትም:: የዴዶ ደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት አለው:: ለጊዜው ቤተክርስቲያኑ አንዳንድ ያሉበትን ሁኔታዎች እስኪያሟላ ድረስ ግለሰብ ተከራይቶት የአካባቢውን ሕፃናት ያስተምርበታል:: ቤተክርስቲያኗ ከዚህ የተወሰነ ገቢ ብታገኝበትም ወደፊትም ትምህርት ቤቱን የምታስተዳድርበትን ቀን እየተመኘን ወደ ጅማ ፈለገ ሠላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተጓዝን::

### ሥራና ሠራተኛ በፈለገ ሰላም ሲገናኙ

ከብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ፣ ከሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች ጋር ጅማ ፈለገ ሠላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ከቀኑ 10:00 ደረስን:: ደብሩ ዘመናትን ባስቆጠሩ ልዩ ልዩ ዛፎች ተከቧል፤ በወቅቱም የቀድሞው የሰበካ ጉባኤ የሥራ ዘመኑን አጠናቆ አዲስ ለተመረጠው ለማስረከብ በተዘጋጀ ሥነ ሥርዓት ላይ ነበር የደረስነው::

ወደ ቅጽረ ግቢው እንደዘለቅን ትኩረታችንን የሳበው የሕንጻ ቤተክርስቲያኑ የውጭ ገጽታ ነው:: በጥሩ ዲዛይን /በሞዛይክ/ የታነጸ ነው:: ውስጡም በጥንታውያን ቅዱሳት ሥዕላት የተሞላ በርካታ ንዋየ ቅድሳት እና ቅዱሳት መጻሕፍቱ ተሟልተው ያሉበት ነው::

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም የታነጸው የፈለገ ሠላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አገልግሎቱ በጥሩ ሁኔታ ሳይታጎል ይካሄዳል:: ለዚህ ደግሞ ደብሩ የብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስን መመሪያ ተግባራዊ አድርጎ መንቀሳቀሱ በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው::

የልማት ሥራውን ተዘዋውረን እንደተመለከትነው የሰበካ ጉባኤው እንቅስቃሴ የሚያስደስት ነው:: በአምስት ሔክታር መሬት ላይ የባሕር ዛፍ፣ አቮካዶ ተክሏል:: ከአቮካዶው በዓመት እስከ ሃያ ሺሕ፣ ባሕር ዛፉን በየሦስት ዓመቱ እየቆረጡ በመሸጥ ከሃምሳ እስከ መቶ ሺሕ ብር ገቢ ያገኛሉ:: ችግኞቹን ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ የሚያገኙ መሆናቸውን የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር አቶ መላኩ ዘለቀ ገልጸውልናል:: ደኖቹ ለቤተክርስቲያኗ ግርማ ሞገስ ከመሆናቸው በላይ ቤተክርስቲያኗ ለደን ጥበቃና ክብካቤ ከፍተኛ ጥረት የምታደርግ መሆኗን የሚያሳይ ነው::

ሰበካ ጉባኤው ለቤተክርስቲያን አገልግሎት አንድ አዲስ ሚኒባስ ገዝተዋል፣ ሁለገብ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ



www.eotcmk.org



*በ፵ ቀን የተሠራው ቅዱስ ዑራኤልና አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ቤተ ክርስቲያን*

አሠርተዋል፣ ውኃም አስገብተዋል። ቤተ ክርስቲያኗ በልማቱ ተጠቃሚ በመሆኗ ያለፈው ያገደመው ሁሉ እደጉ ተመ ንደጉ የማይላቸው የለም። ሰበካ ጉባ ኤው ይህን ልማት ሊሠራ የቻለው በብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ያላሰለሰ መመሪያና ፍ ጹም አባታዊ ምክር መሆኑን የገለጹት ምክትል ሊቀመንበሩ አቶ መላኩ «ማኀ በረሰቡ የሚጠቀምበት ክሊኒክ፣ የከብት ርባታ፣ የንብ ማነብ ሥራን ለማጠናከር ታቅዷል፤ ወፍጮ ቤት የመትከል የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ቤተክርስ ቲያኗን የገቢ ምንጭ ለማጠናከር ታቅዷል» በማለት አስረድተዋል። የሰበካ ጉባኤው ጥንካሬ ለሽልማትም አብቅቶታል። ለሌ ሎችም አርአያ በመሆኑ ከሀገረ ስብከቱና ከቅዱስ ሲኖዶስ በተለያየ ጊዜ ሰርተ ፍኬትና የተለያዩ ሽልማቶችን አግኝቷል። ሰበካ ጉባኤው በየጊዜው አዳዲስ ዕቅዶችን በማቀድ በከተማው የሚገኙ ገዳማትና አድባራትን ጥሪ በማድረግ የሥራቸውን ፍሬ በማሳየት የልምድ ልውውጥ በየጊ ዜው ያደርጋሉ።

ሰበካ ጉባኤው ከልማቱ በተጓዳኝም የቤተክርስቲያኑ አገልግሎት እንዳይታጎል በማሰብ የደብሩ ካህናት በቤት ችግር እንዳይሰቃዩ ለአገልግሎት እንዲፋጠኑ ከመ ንግሥት መሬት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እና ሰበካው ብር አበድሯ ቸው የቤት ባለቤት እንዲሆኑ ማድረጋ ቸውን ምክትል ሊቀ መንበሩ አስረድተ ውናል። ሥራና ሠራተኛ ሲገናኙ እንዲህ ነው። እኛም ሰበካ ጉባኤውን እያመሰገ ንን ሌሎችም አርአያነቱን እንዲከተሉ ተመኘን። በዚያም የነበረንን ቆይታ አጠ ናቀን ከብፁዕ አባታችን ጋር ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ወደ ጅማ ከተማ ተመለስን።

### ጥንታዊቷ ኮሳ ማርያምና ኮሳ ተክለሃይማኖት ጉርሙ መድኃኔዓለም

የካቲት ፳፫ ቀን ፳፻ ዓ.ም ሌሊት ከብፁዕ አባታችንና ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር በመሆን ከጅማ በስተ ሰሜን አቅጣጫ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ለመዘገብ ተጓዝን። የገጠሩ ጠመዝማዛ ኮረኮንች መንገድ የሚያልቅ አይመስ ልም፤ አንዱን ጋራ ስናልፍ ሌላው መልሶ ብቅ ይላል። ዕድሜ ጠገብ ዛፎችን፣ ጥቅጥቅ ደኖችን፣ ጋራ ሸንተረሩን እየተ መለከትን የብፁዕነታቸውን ትምህርት እየኮመኮምን መንገዳችንን ተያያዝ ነው። ከአንደበታቸው የሚወጣው ሁሉ ስለ ቤተክርስቲያን ልማት ነው። አንዳንዴም በመስኮቱ አሻግረን ተፈጥሮን እያ ደነቅን ሊሙ ኮሳ ደረስን። ሊሙ ኮሳ ከጅማ ፵፰ ኪ.ሜ ይርቃል።

ኮሳ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያ ንን ከሊሙ ኮሳ ከተማ በስተግራ ትተን አለፍ እንዳልን ከአባ ወልደ መድኅን ጋር ተገናኘን። ቀድመን ጉርሙ መድኃ ኔዓለም መሔድ ሳለነበረብን እርሳቸውን በመኪናችን ውስጥ ገብተው በመንገዱ ቀኝ ተገንጥለን ወደ እርሻ ልማት አመ ራን። በእርሻ ልማቱ ከሚሠሩ ሠራተ ኞች በስተቀር በእርሻ ልማቱ ውስጥ መግባት አይፈቀድም። ቤተክርስቲያኑ ግን ያለው በልማት ጣቢያው መሐል ነው። የልማት ቦታው የሚጠበቀው በሙ ስሊሞች በመሆኑ በሔድንበት አጋጣሚ በቀላሉ መግባት አልቻልንም። ከብዙ ውዝግብ በኋላ ግን እዚያው እንደቆምን አባ ወልደ መድኅን የፈቃድ ወረቀት ለማምጣት ወደ ውስጥ እየሮጡ ሔዱ፤ በኋላም ከአንድ ሞተረኛ ጋር የመግቢያ ፈቃድ ወረቀት ይዘው መጡ። ከዚያም ተፈቀደልንና ገባን። ጉርሙ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ከተራራው ጥግ ይገኛል።

ደብሩ ዘመናትን ባስቆጠሩ ልዩ ልዩ ሀገር በቀል ዛፎች ተከቧል። ወደ ተራራው እየቀረብን ስንመጣ ፀጥታው፣ የዛፎቹ ጥንታዊነት በግልጽ ያስታውቃል። ወደ ቅጽረ ግቢው እንደዘለቅን ትኩረታችንን የሳበው የሕንጻ ቤተክርስቲያኑ አሠራርና በዙሪያው ያሉ ጥንታውያን ሀገር በቀል ዛፎች ናቸው።

የደረስነው ቅዳሴው ሊያልቅ አካባቢ ነበር። ምእመናኑ ብፁዕነታቸውን ሲያዩ ተደነቁ፣ ተገረሙም። ጳጳስ አይተው አያ ውቁምና ተአምር የወረዳ ነው የመሰላቸው። እየመጡ እርስ በርሳቸው ይተያያሉ፤ ጸጥታው ሰፈነ። ቤተክርስቲያኑ በተራ ራው አናት ደልዳላ መሬት ላይ በመሆኑ በዙ ሪያው የሚገኘውን የእርሻ ልማት ማየት ይቻላል። ቦታው ከአዕዋፋት ድምፅ በስተቀር ምንም የማይሰማበት ሕ ይወትን የሚያድስ የቅዱሳን ቦታ ነው። በአጥቢያውም የሚገኙ ክርስቲያኖች ከሠላሳ የማይበልጡ ናቸው።

የቡና እርሻ ልማቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የአፈ ንጉሥ ጥበቡ በየነ፣ የአቶ መሐሪ እንዳለ፣ የጄነ ራል ቀልቤሳ... ይዞታዎች ነበሩ። ቤተ ክርስቲያኑ የሚገኘው ግን በአፈ ንጉሥ ጥበቡ በየነ ይዞታ ላይ ነው። በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም በተደረገው የመንግሥት ለውጥ የእርሻ ልማቱ ተወርሷል፤ አሁን በመንግ ሥት ሥር ይገኛል።

ቅዳሴው ተጠናቆ ከውስጥ የነበሩት ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጡ። በረንዳው ላይ ለብፁዕ አባታችን መቀመጫ መጣላቸው ምእመናኑም ከፊት ለፊታቸው ተሰባስ በው ዓይን ዓይናቸውን ያዩአቸዋል። ያረጀ ብል የበላው አልባሳት የለበሱት የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ መምሬ ዐይነ ኩሉ ዓለሙ ብቅ ብለው እጅ ነሱ። ቡራኬ ተቀብለው ስለ ቤተክርስቲያኑ አመሠራረት መናገር ጀመሩ «አፈ ንጉሥ ጥበቡ በየነ ቤተክርስቲያኑን በ፲፱፻፳፬ ዓ.ም አሳነጹት። በእርሻ ልማቱ የሚሠሩ ክርስቲያኖች ቅዳሴ የሚያስቀድሱበት፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ በማሰብ ነበር የሠሩት። በኋላም እርሳቸው በማረፋቸው ለቤተክር ስቲያኑ ያቀዱት ነገር ሁሉ በጅምር ቀረ። ዛሬም የአገልጋይ እጥረት አለብን፤ አል ባሳትም የለንም፤ አባታችን ከተገኙልን ችግራችንን ይቀርፉልናል።» ሲሉ በዚያ የተሰበሰቡ ምእመናን እልልታውን አቀለ ጡት። ከደስታቸው የተነሣ ሲቃ ተናን ቋቸው የሚያነቡም ነበሩ።

በመጨረሻ ብፁዕነታቸው ፊትለፊታቸው ተኮልኩለው ቡራኬያቸው ለሚጠባበቁ ሕዝበ ክርስቲያን የማጽናኛ ቃል ሲናገሩ «ለቤተክርስቲያን ባለውለታ የሆኑ አባቶ ችን እንድናስታውሳቸው፣ በረከታቸውን ለማግኘት፣ እናንተንም ለመጎብኘት ዳገ ቱን ወጥተን ቁልቁለቱን ወርደን መኪና እንኳን መግባት ባይችልም ልንጎበኛችሁ መጥተናል። በሃይማኖታችሁ ጽኑ ወደፊ ትም የጎደለባችሁን ነገር እናሟላላችኋ ለን» ብለው ነበር።

ቤተክርስቲያኑ እድሳት ተደርጎለት ስለማያውቅ ግድግዳው ተሰነጣጥቋል፤ ጣራ ውን የተሸከሙት ምሰሶዎች ዘመው ይታ ያሉ። ቤተክርስቲያን ውስጡ ንዋየ ቅድ ሳት፣ አልባሳት፣ ሥዕላት የሉትም። እኛም ጉዞአችን ረጅም በመሆኑ ልንሰናበታቸው ግድ አለን። እነርሱም አጅበውን እየዘ መሩ መኪናችን ድረስ ሸኙን። ከብፁዕ አባታችን ቡራኬ ተቀብለው ተሰናበቱን፤ እኛም ጉዞአችንን ቀጠልን።

አባ ወልደ መድኅን መኮንን እየመ ሩን ወደ ጥንታዊቷ ኮሳ ቅድስት ማርያም





www.eotcmk.org

ተጓዝን፡፡ የቤተክርስቲያኗን አጠቃላይ ታሪክ ለማወቅ ጉጉት አደረብን፡፡ «ኮሳ» የደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ጥንታዊ ከተማ ናት፡፡ የቀድሞ ስሟ «ኩሳ» ሲሆን ቃሉም የኦሮምኛ ነው ትርጓሜውም የሰው መሰባሰቢያ ማለት ነው፡፡ በወቅቱ ሕዝቡ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ ነጋሪት ተመትቶ የሚሰበሰቡበት አደባባይ በመሆኑ ከዚያው በወጣ መጠሪያ ኮሳ ተብሏል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ከፍ ብሎ የደጃዝማቹ ችሎት መቀመጫም ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ሳተላይት ተተክሎበታል ማስተወሻነቱ ግን አሁንም ይታያል፡፡

ወደ ቤተክርስቲያን ቅጽር ስንዘልቅ ይጠብቁን ከነበሩት አባቶች ጋር መንፈሳዊ ሰላምታ ተለዋወጥን፤ ጊዜ ለመቆጠብ ጸሎታችንን አድርሰን ወደ መጣንበት ዓላማ ተሠማራን፡፡ የኮሳ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በ፲፰፻፷፭ ዓ.ም በወቅቱ የከፋ ጠቅላይ ግዛት ገዢ በነበሩት በደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ታነጸች፡፡ ፳፫ ጋሻ መሬት መተዳደሪያ ነበራት፡፡ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በድንገት በተነሣ እሳት ቤተክርስቲያኗ ተቃጥላ እንደነበር በደብሩ የሚገኝ ታሪክ ያስረዳል፡፡

አባ እንደነገሩን ቤተክርስቲያኗ ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ በተከለለላት የጋሻ መሬት ስትገለገል ብትቆይም በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ መሬቷ ተወረሰ፡፡ አገልግሎቷም ተዳከመ፡፡ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም አጽራረ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ሰዎችን በማሠማራት ጥቃት ፈጽመውባታል፡፡ በ፲፱፻፸ ዓ.ም አንድ ግለሰብ የከተራ ዕለት የቤተ ክርስቲያኑን ቁልፍ ሰብሮ በመግባት ንዋየ ቅድሳቱን፣ ቅርሶቹን በሚያሳዝን ሁኔታ አወደመው፡፡ ከዚያ በኋላም ካህናቱ ኪዳን በማድረስ፣ እየቀደሱ ቤተክርስቲያኗ ከቦታዋ እንዳትጠፋ የተቻላቸውን ጥበቃ በማድረግ ለረጅም ጊዜ ያለ ደመወዝ ሲያገለግሉ ቆዩ፡፡ ካህናቱ በዚያ በረሐ ጠያቂ ሳይኖራቸው በአረማውያን ተከበው ሳሉ ለቤተክርስቲያን ያላቸው ፍቅር ለሃይማኖታቸው ያላቸው ጽናት ግን ያስቀናል፡፡

ይባስ ብሎ ከዚያችው መሬት ላይ በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም በነበረው የመንደር ምሥረታ መርሐግብር የቤተክርስቲያኗ መሬት ጥቂት ለቀብር ብቻ ሲቀርላት መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለግለሰቦች ቤት መሥሪያ አከፋፈለው፡፡ «በእንቅርት ላይ. . .» እንዲሉ ከዚያን ጊዜ በኋላ ቤተክርስቲያኗ እስከ አሁን ያልተወጣችው አስከፊ ችግር ተጋለጠች፡፡ ካህናቱ ያለደመወዝ ቤተ ክርስቲያን ያለ ጥበቃ ቆየች፡፡ ይህን የተመለከቱ አጽራረ ቤተክርስቲያን በ፲፱፻፹፭ ዓ.ም የቤተክርስቲያኗን አጸድ በማፈራረስና በሮቹን ሰብረው በመግባት ከጽላቷ ጋር የመጡትን ቅርሶች፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ መስቀል፣ ንዋየ ቅድሳት ዘረፉ፡፡

በዚሁ ዓመት መናፍቃን አዲስ ስልት ቀይሰው በዚህች ታሪካዊ፣ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ላይ ወረራቸውን አጠናክረው ቀጠሉ፡፡ ቤተክርስቲያኗ ያለባትን ኢኮኖሚያዊ ችግር ስለሚያውቁ ካህናቱንና ዲያቆናቱን በችግራቸው ደራሽ መስለው በገንዘብ ለማታለል ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም፡፡ የአካባቢው ምእመናንንም በማደናገር ከሃይማኖት ለማፈናቀል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል «ምስማርና ክርስቲያን ሲመቱት ይጠብቃል» እንዲሉ ካህናቱና ምእመኑ እጅና ጓንት በመሆናቸው የመከራው ጽናት አጠነከራቸው እንጂ ወደ ኋላ እንዲሸሹ አላደረጋቸውም፡፡ የደብሩ አስተዳዳሪና ካህናቱ ከምእመኑ ጋር አንድ በመሆን በየመንደሩ፣ በየማኅበሩ፣ በዕድሮች እየተዘዋወሩ ወንጌልን በመስበክ ምእመናን እንዳይበተኑ የመናፍቃኑን ሴራ አክሽፈዋል፡፡

የጠላትን ፈርጀ ብዙ ተንኮል የተረዱት በየአጥቢያው የሚገኙ የኮሳ እርሻ ልማት ምእመናን እኛ የምንበላው ይቅርብን ብለው፣ ከጉረሮአቸው ቀንሰው ዘበኛ በመቅጠር ቤተክርስቲያን ለዳግም ዘረፋና ጥቃት እንዳትጋለጥ ጥረት ቢያደርጉም፤ እነዚሁ አጽራረ ቤተክርስቲያን በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በህዳር ወር ከቀኑ 6:00 ሰዓት አካባቢ ቤተክርስቲያኗን አቃጥለዋታል፡፡ ዘበኛውንም ለመግደል ሲተናነቁ የአካባቢው ሕዝብ ደርሶ ቤተክርስቲያኑን ሙሉ በሙሉ ከመጥፋት ዘበኛውንም ከሞት አትርፈውታል፡፡

ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስም ካህናቱና የአጥቢያው ምእመናን በየጊዜው የሚያደርጉላቸው ሪፖርት ቀን ዕረፍት፣ ሌሊት እንቅልፍ ስለነሳቸው ታኅሣሥ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በቤተክርስቲያኑ ተገኝተው በማጽናናት ለካህናቱ መደጎሚያ በየወሩ አምስት መቶ ብር በጅተውላቸዋል፡፡ ሰበካ ጉባኤውም ምእመኑን በማስተባበር ባለችው ትንሽ ቦታ የቡናና የባሕር ዛፍ ተክሎ እያለማ ይገኛል፡፡

«ልጆቼ ቤተክርስቲያኑ በእርጅና ምክንያት ግድግዳው በምስጥ ተበልቶ እየፈረሰ ነው፡፡ የንዋያተ ቅድሳት እጥረትም አለብን» ያሉት አስተዳዳሪው ቅርሶቹ እንዳይዘረፉባቸው ምስጥ እንዳያበላሽባቸው በመኖሪያ ቤታቸው የሚያስቀምጧቸውን መጻሕፍትና ሌሎች ቅርሶች «ማየት ማመን ነውና ተመልከቷቸው» ብለው አስመጥተው አሳይተውናል፡፡ ቅርሶቹ የሰው ያለህ! እያሉ ይጣራሉ፡፡ አባቶች በተጋድሎ ያቆዩአቸው የብራና መጻሕፍቱ፣ የነገሥታቱ አልባሳት፣ ቃጭሉ ንዋየ ቅድሳቱ ወዘተ... ሲንገላቱ ማየት የአባቶቻችን ልጆች ነን ለምንል ያሳፍራል? ዐረፍተ ዘመን የገታቸው አባቶች ቀና ብለው ቢያዩን ምን ይሉ ይሆን? «በጎ አድራጊዎች ምእመናን ድረሱልን፤ ቅርሶቹን የምናስቀምጥበትም ሥሩልን...» በማለት ሐዘን በተቀላቀለው ስሜት ነበር አስተዳዳሪው የገለጹልን፡፡ ግን እስከ መቼ እንዲህ ይኖራሉ?

ከቅርሶቹ መካከል በ፲፱፻፸ ዓ.ም ከቃጠሎ የተረፉ፣ የተበላሹ፣ የተገነጣጠሉ ወዘተ... መጻሕፍትን አይተናል፡፡ በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ የታተመ ጥንታዊ የብራና ወንጌል፣ ተአምረ ማርያም የጽሑፍ አጣጣል የብራናው ንጽህና የሚያስደንቅ ነው፡፡ እነዚህን የሀገር ቅርሶች የኮሳ ቅድስት ማርያም አባቶች ጠብቀው አቆዩልን፡፡ ታዲያ ዛሬ በመንገላታት ላይ ለሚገኙት ቅርሶች የእኛስ መልስ ምን ይሆን?

ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ቅርሶቹን ከተመለከቱ በኋላ ያስተላለፉት መልእክት የሚያስለቅስ ነበር፡፡ «አባቶች ያቆዩትን ቅርስ፣ ደክመው የጻፉትን መጻሕፍት አይተናል፡፡ ቅርሶቹን ጠብቃችሁ አቆይታችኋል የሰው ያለህ እያሉ እየተጣሩ ነው፤ ይህን ያዩ በጎ አድራጊ ምእመናን ከሌባ፣ ከዘራፊና ከእሳት ቃጠሎ የተረፉትን ቅርሶች ሊታደጓቸው ይገባል፡፡ እንደ አባቶቻችን መቃብር ከመግባታችን፣ እንደበታችን ከመዘጋቱ እጅና እግራችን ከመታሠሩ በፊት ሥራ ልንሠራ ይገባል፡፡ ምእመናንም ሊደርሱላቸው ይገባል፡፡» ነበር መልእክታቸው፡፡

የቤተክርስቲያንን ታሪክ በመስማት ብቻ ሳይሆን ምእመናን በአካል ተገኝተው እንደነዚህ ዓይነት በመከራ ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን መጎብኘትና ቅርሶቹን መታደግ ሃይማኖታዊ ግዴታችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ብፁዕነታቸው በአጥቢያው ለሚኖሩ ምእመናንም «የአባቶቻችሁ አደራ አለባችሁ፡፡ እኛም ከዚህ ቦታ በረከት ለማግኘት ነው የመጣነው፡፡ የአባቶቻችንን ቅርሶች በእጃችን በመዳሰሳችን በረከት ተቀብለናል፡፡ እናንተ ከዚሁ ስለምትኖሩ እንደ ቀላል ነገር አትዩት፤ ያላችሁት በበረከት ቦታ ነው ቤተክርስቲያናችሁን ጠብቁ» በማለት አሳስበዋል፡፡

እኛም በቦታው ያሉ የምእመናኑን ሐሳብና ጭንቀት ሰምተን ካደረጉልን መስተንግዶ በኋላ በዚያው አቅራቢያ ትይዩ ሆኖ ወደሚገኘው ኮሳ ተክለሃይማኖት ተጓዝን፡፡ ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት በደጃዝማች ወልደጊዮርጊስና በባለቤታቸው በወ/ሮ የሺመቤት የታነጹ ናቸው፡፡

የቤተክርስቲያኑን ታሪክ እንዲያስረዳን የሰበካ ጉባኤ አባል አቶ ንጉሤን ብፁዕ አባታችን መደቡልን፡፡ ከአቶ ንጉሤም ገለጻ እንደተረዳነው በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጽላቱ ከኢየሩሳሌም እንደመጣ ቢነገርም ባለ ሰባት ደረጃ ሣር ክፍክፍ ክዳን ቤተክርስቲያኑን ያሳነጹት ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው፡፡ በኋላም በዕድሜ ብዛት ፈረሰ፡፡ በ፲፱፻፵ ዓ.ም የአጥቢያው ተወላጅ አቶ ወንድሙ ይትባረክ ቤተክርስቲያኑን ለማሠራት ሲሚንቶ፣ ቁሳቁስ አቅርበው ነበር፡፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ የታሰበው ሳይሠራ ቀረ፡፡

ወደ ገጽ ፴፯ ዞሯል



www.eotcmk.org

# «... እርስ በእርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ»

## ገላ. ፭፥፲፭

ዲ/ን ምትኩ አበራ

በአንድ ወቅት የሶርያው ንጉሥ ወልደ አዴር ሠራዊቱን ክተት ብሎ ሰማርያን በከበበና በጦርነትም ባስጨነቃት ጊዜ እስራኤላውያን ለጆሮ የሚቀፍና ለሕሊና የሚሰቀጥጥ ታሪክ ተፈጽሞባቸው አልፏል:: ቅዱስ መጽሐፉችን ይህንን ዘግናኝ ታሪክ እንዲህ አስፍሮታል:: «. . .የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር ሠራዊቱን ሁሉ ሰበሰበ:: ወጥቶም ሰማርያን ከበባት በሰማርያም ታላቅ ረሃብ ሆኖ ነበር:: እነሆ የአህያ ራስ በሃምሳ ብር፣ የርግብም ኩስ የጎሞር ስምንተኛ የሚሆን በአምስት ብር እስኪሸጥ ድረስ ከበቡአት:: የእስራኤልም ንጉሥ በቅጥር ላይ በተመላለሰ ጊዜ አንዲት ሴት ጌታዬ ንጉሥ ሆይ እርዳኝ ብላ ወደ እርሱ ጮኸች. . . ንጉሡም ምን ሆነሻል? አላት እርስዋም ይህች ሴት ዛሬ እንድንበላው ልጅሽን አምጪ ነገም ልጄን እንበላለን አለችኝ:: ልጄንም ቀቅለን በላነው በማግሥቱም እንድንበላው ልጅሽን አምጪ አልኋት ልጅዋንም ሸሸገችው ብላ መለሰችለት ንጉሡም የሴቲቱን ቃል ሰምቶ ልብሱን ቀደደ/አምርሮ አዘነ/. . .» ይለናል:: /፪ነገ.፮:፳፬-፴/:: ሰዎች እርስ በእርስ የተበላሉበት ዘግናኝ ታሪክ:: መቼም ይህንን እውነት በማስተዋል ያነበበ ሁሉ ልቡ በሃዘን ፍላጻ ከመነደፉም በላይ ይህም አለ ለካ ብሎ «ፈጣሪዬ ሆይ የምሰማውን አታሳየኝ» በማለት መማፀኑ አይቀርም::

ይህንን ያለፈ ታሪክ ያነሣሁት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለይም በታላላቅ ከተሞች አካባቢ እየተፈጠረ ስላለው አነጋጋሪ ጉዳይ ለመጻፍ መነሻና መረጃ እንዲሆነኝ ነው፤ ስለ ኑሮ ውድነት:: እኛ የኑሮ ውድነት የምንለውን የዘርፉ ባለሙያዎች የገንዘብ ዋጋ መውረድ ወይም የገንዘብ ግሽበት /Inflation/ ይሉታል:: ከዘርፉ ባለሙያዎች አንዱና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር የሆኑት ዲ/ን ያብባል ሙሉዓለም በቅርቡ በዓለማችን የተከሰተውን የዋጋ ግሽበትና በዚሁ ምክንያት በሀገራችን የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት አስመልክቶ የሚከተለውን ይላሉ::

«ዋጋ ሁል ጊዜ የሚወሰነው...» ብለው የጀምራሉ ምሁሩ:: «ለአንድ ዕቃ ባለው ፍላጎትና በዕቃው አቅርቦት መጠን ነው:: ስለዚህ የዋጋ መናር የፍላጎት ከአቅርቦት በጣም መብለጥ /አለመጣጣም/ የተነሣ የሚመጣ ነው:: የዋጋ ግሽበት ፍላጎቱ ሳይጨምር በአቅርቦት ማነስ ብቻ ሊመጣም ይችላል:: ለምሳሌ በድርቅ፣ በዝናብ አለመስተካከል፣ ወይም በጥሬ ዕቃ ዋጋ መጨመር /ለምሳሌ የነዳጅ ዋጋ መጨመር/ ሊመጣ ይችላል:: በሌላ በኩል ደግሞ አቅርቦቱ ሳይነካ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩም የዋጋ መናር ሊከተል ይችላል:: ይህኛው በተለይ በኢኮኖሚው /ምጣኔ ሀብት/ የሚዘዋወረው የገንዘብ መጠን ሲጨምር የሚከሰት ነው:: ለምሳሌ የደመወዝ መጨመር፣ ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ሲታተምና የመንግሥት ወጭ ሲጨምር፣ ብድር በከፍተኛ ሁኔታ ሲለቀቅ እና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሲያድግም የግለሰቦች የመግዛት አቅም ስለሚጠነክር የፍላጎት መጨመርና ከዚያም የዋጋ ንረት ሊያስከትል ይችላል::

የፍላጎት መጨመርና የአቅርቦት ማነስ /የጥሬ ዋጋ መጨመር/ በአንድ ላይ ሲከሰት ደግሞ ችግሩን የበለጠ ከባድ ያደርገዋል:: ስለዚህ የአሁኑ የዋጋ ግሽበት ከላይ ከተጠቀሱት ባንዱ ወይም በብዙዎች ምክንያት ሊከሰት ይችላል» የመስኩ ባለሙያ የገለጹትን የኑሮ ውድነትን መንሥኤ ይዘን መባባሻውን በተመለከተ ጥቂት ሐሳቦችን እንሰንዝር::

በተለይ እንደ መንፈሳዊነታችን ስንቃኘውና በሀገራችን ያለውንም ነባራዊ ሁኔታ ስናይ ብዙዎችም የሚስማሙበትና እንደ ዘርፉ ባለሙያዎችም ገለጻ የእኛ የኑሮ ውድነት በአንድም በሌላም ምክንያት ተከስቶ የተባባሰው ግን «ብቻዬን ይድላኝ» በሚለው ፍቅረ ቢስ አስተሳሰባችን ነው:: እስኪ ቆም ብለን ራሳችንን አንድ ጥያቄ እንጠይቅ:: በዚህ ዘመን ነጋዴም እንሁን ሸማች ክርስቲያኖች ከሆን ግን ክርስትናችንን በማኅበራዊ ኑሮ የምንገልጸው እንዴት ነው? ክርስትና በሰው ሥቃይ የምንደሰትበትና ነፍስ አጥፍተን ገነት የምንገባበት እንዲሁም የዕለት ምግብ ኖሮን ስናበቃ በተሳሳተ አቅጣጫ በመጓዝ ለነገ የምናግበሰብስበት ሕይወት ሳይሆን «የቀኑ ለማኝ ለማታው ለማኝ ይተርፋል» በሚል መርሕ ለወገናችን የምንተርፍበት ሕይወት ነው::

በመጀመሪያ ደረጃ ከላይ በጽሑፉ መነሻ ላይ እንዳነበብነው እስራኤላውያን በሰማርያ ያገኛቸው ዓይነት ታሪክ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለመከሰቱ ማለትም ሰዎች የሚበሉት አጥተው የአህያ ራስና ኩስ እስኪበሉና እርስ በርሳቸውም እስኪበላሉ የሚያደርስ አስከፊ ችግር ለማየት ባለመብቃታችን ልዑል እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሀገራችን በተፈጠረው የኑሮ ውድነት ሳቢያ ወገን በወገኑ ላይ ሲጨክን እያየን ነውና በተዘዋዋሪ መልኩ እርስ በእርሳችን እንዳንበላላ ራሳችን ለራሳችን ባለመላ ልንሆን ያስፈልጋል::

አንድ ጊዜ ሁለት ውሾች በእኩለ ቀን ጠብ ይገጥሙና መነካከስ ይጀምራሉ:: እነሱ በመነካከስ ላይ ሳሉ ድንገት ሰማዩ እንደደመና ግርዶሽ ባለ ሁኔታ ጨለማ ቢጤ ይፈጥራል:: ጠቡ ሳይቆም ከሁለቱ ውሾች አንዱ በተፈጠረው የጭለማ ድባብ ተገርሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ቀና ቢያደርግ ብዙ አሞሮች ከፍ ብለው እያንዣበቡ ያያል:: ለካስ ግርዶሹን የፈጠሩት እነሱ ናቸው:: ይህን ያየው ውሻ ወዲያው ንክሻውን ያቆምና ለሌላው ውሻ ጥያቄ ያቀርባል፤ እንዲህ ሲል «ስማ እንጂ አንተዬ እነዚህ አሞሮች እንዲህ ፀሐዩን እስኪጋርዱት ድረስ በላያችን የሚያንዣብቡት ምን ሆነው ነው?» ቢለው ሁለተኛው ውሻም «እነሱማ እኛ ተነካክስን ስናበቃ ከሆነላቸው ሁለታችንም ካልሆነም አንዳችን ስንወድቅ ሊዘነጣጥሉን /ሊበሉን/ነዋ» ብሎ ይመልሳል:: ይሔኔ ሐሳብ የገባው የመጀመሪያ ውሻ «ታዲያ እኛ ጠቡን አንተወውምን?» ብሎ ተነሣና ሁለቱም ተስማምተው ጠቡን ተውት:: ውሾቹ ሲስማሙና መነካከሳቸውንም ሲያቆሙ አሞሮቹም ተበታተኑ:: መላ ማለት ይኸው ነው::

በኢትዮጵያችንም እየሆነብን ያለው እና ልናደርገው የሚገባን ጉዳይ ይኸው ነው:: በመካከላችን የእርስ በእርስ መጨካከንና መበላላት ምልክቶች አሉ:: ለምሳሌ በንግድ ዙሪያ አንዳንድ ምርቶች ከተለያዩ ምክንያቶች አንፃር ዋጋ ሲጨምሩ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ምርቶችም ከሜዳ ተነሥተው ዋጋቸው ይጨምራል:: ለምሳሌ ነዳጅ ስለጨመረ የቤት አከራዮች በተከራዮቹ ላይ ዋጋ ይጨምራሉ:: የነዳጅ ዋጋ ስለጨመረ የዶሮ እንቁላልም ዋጋው ይጨምራል ወዘተ ... ሌላው ደግሞ ጥቂት ነጋዴዎች ብዙ ተጠቃሚ ያላቸውን ምርቶች በመለየት ምርቶቹም ከገበያ ሳይጠፉና የምርትና የአቅርቦት እጥረትም ሳይከሰት ለወገን በማያስብ ሕሊና ዓይነት በአንድ ቦታ አከማችተው በማቆየት ሰው ሠራሽ የምርትና የአቅርቦት እጥረት ፈጥረው የዋጋ ንረትን ሲያመጡ ይታያሉ::

ስለዚህ እየሆነብን ያለውና የሆነው ክፉ ነገር ሁሉ በተለይም የኑሮ ውድነቱ ማቀጣጠያ የእኛው አለመስማማትና አለመተዛዘን ነው ብንል ማጋነን አይሆንም::

በመሆኑም ችግራችንን የሚያባብሰውን የወቅቱን የእርስ በእርስ ንክሻ ለማስቆም ከላይ እንደተጠቀሰው ውሾቹ የወሰዱት የመጨረሻ እርምጃ ይተገበር ዘንድ ሁላችንንም ግድ ይለናል:: ወደድንም ጠላንም የእኛን እርስ በእርስ ተባልቶ ማለቅ የሚጠብቁ የሚታዩና የማይታዩ የውስጥና የውጭ አሞሮች በበዙበት፣ ሰው ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ዓለማዊ ኑሮው





www.eotcmk.org

ፈተና በሆነበት በዚህ ወቅት እርስ በእርሳችን መተዛዘንና መተሳሰብ ይገባናል:: በተረፈ ግን ግላዊ በሆነ አመለካ

ካልሸጥኩ ገበያ የለም በማለት «የበጌ መሞት ለውሻዬ በጃት» እንዲሉ የወገን ስቃይና ረሀብ የሚያስደስቀው

በፍየል የተመሰሉት

ጊዜ ለመክበር ጓጉተን እርስ
ምንጨካከንና የምንበላላ ከሆን
ግጫ ተጎጂዎች ነን:: በምንና
ደግሞ፦

ንና የተሰጠንን መብላትና
ጠቀም አንችልም

ለም ኑሮ ተስገብግቦ መሰብ
በስ መብላት የሚመስላቸው
ው:: ክርስቲያን ሊሰበስብ
አያግበሰብስም:: ምክንያቱም
ለከሙ መዝገበ ዘበምድር
ወይማስን ዝግቡ ለከሙ
ማያት ኀበ ኢይበሊ ወኢ
ጉሙም፣ «ኀልፈት ጥፋት
ች ቆፍረው የሚወስዱትን
/ አትሰብስቡ፤ ኀልፈት ጥፋት
ማያዊ መዝገብን /ሀብ ትን/
ልና:: /ማቴ.፮÷፲፱/
መብላት ቢሆን ኖሮ በሉ
ምዕራፍ ፲፪÷፲፮-፳፩ ታሪኩ
ምስኪን ባግበሰበሰው ክም
ቶ «... አንቺ ነፍሴ ለብዙ
ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ
ስ ይበልሽ. . .» ካለ በኋላ
ንተ ሰነፍ በዚህች ሌሊት
ጋህ ይለዩዋታል፤ ይህስ
ከማቸኸው/ ምን ይሆናል?»
ነበር:: የንባቡ መጨረሻ
ዘብ የሚያከማች በእግዚአ
ባለጠጋ ያልሆነ እንዲህ
ፍየሎች የሚበሉትን ብዙ
ቢያገኙ ብቻዬን ልብላው
እርስ በእርሳቸው ሲወጋጉ
ንጂ ተስማምተው አይበሉ
ግን ጥቂት ሣር ቢያገኙ
ይመገቡታል:: በፍየል የተ
ንም እንኳንስ ጥቂት ብዙም
ቸው በበግ የተመሰሉት
አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ
ት ስለሚኖሩ ብዙው ሳይ
ንደማያጣላቸው በምስጢረ
ርት ላይ በግራና በቀኝ
ፍየልና የበጎቹን ምስጢር
ስተማሩበት በአንቀጸ ትን
ታቸው ሊቃውንተ ቤተ
ታሉ:: በተንኮል የምንጠ
ፍትፍት መሰል ምርቅ
ካሽ/ አለውና ይደፋል
ም::
ኮ መሬት የተዘራባትን
ስጠች ምርቱ ከጎተራና
የችግር /የረሀብ/ ጊዜ
ትና በመጠበቅ ዓይነት
ሸ,ያጭ የተዘጋጀን ምርት
ማከማቸትና በውድ ዋጋ

አቀጣጫ እየቀያየሩ መነገድ እንጂ እንደ አንድ ክርስቲያን ስናስበው ይህንን ምርት /ዕቃ/ ደብቄ በጣም ሲፈለግ አውጥቼ በውድ ዋጋ ሸጬ በአንዴ እከብራለሁ ብሎ ማሰብ ከእግዚአብሔር ለመቅደም መሞከር ነው:: ለመሆኑ በእጃችን ያለውንና የሰበሰብነውን እንደ ምንበላውስ ምን ያህል እርግጠኞች ነን?

አፈሩን ከእህል ቀላቅሎ ሙዙን ከቅቤ አላቁጦ እንዲሁም በርበሬውን ከሸክላ ጋር አስፈጭቶ ወዘተ... እንደ ንፁሕ ምርት ለገበያ በማቅረብ እግዚአብሔርን እንደማያይ ቆጥሮ የማይገባ ግፍን በገዛ ወገን ላይ መፈጸሙም ሌላው የሰበሰብነውንና ያለንን እንዳንበላ ከሚያደርጉን ምክንያቶች አንዱ ነው:: መቼም ነጋዴ የሚነግደው ለማትረፍ ነው:: ስለዚህ ቢያንስ ለሕሊናችን እንኳ ስንል ንጹሕ ሥራ ሠርተን ተገቢውን የድካም ውጤት ማግኘት አግባብ ነው:: ከዚህ ውጪ ግን በራስም ሆነ በቤተሰብ ላይ ግፍ ማትረፍ ነው:: ታላቁ መጽሐፍም «... ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ» ይላል /ሉቃ.፫÷፲፫/:: እንግዲህ እያለን እንዳንራብ የተመረቱ ሸቀጦችና እህሎች እያሉ የኑሮው ሁኔታ እንዳይንር እርስ በእርሳችን ከመጨካከንና ከመበላላት ተቆጥበን እርስ በእርሳችን በመተዛዘንና በመተሳሰብ ልንኖር ይገባል:: «... ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተሰዎች መልካም እናድርግ» ተብለናልና:: ገላ.፮÷፲::

## ፪ኛ. የሰማይን ጠል የምድርን በረከት እናጣለን

እግዚአብሔር የዚህች ዓለም ሠራዒና መጋቢ ነው:: ፍጠረን ሳንለው የፈጠረን እርሱ ስለሆነ እኛ ለእኛ ከምንጨነቀውና ከምንጠበበው በላይ ስለእኛ ያስባል:: «ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል» እንዲሉ የቻልነውን እየሠራን ከመኖር ውጭ በሆነው ባልሆነው እንዲሁ እንጨነቃለን እንጂ «... እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት. . .» ተብለን ነበር:: /፩ኛ ጴጥ.፭÷፯/ ስለዚህ እርሱ ባወቀ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ፣ በነፋስ አድርቆ ይመግበናል:: ይህ ብቻ ሳይሆን የተመገብነውን ከሰውነታችን በማስማማት አዋሕዶ ያኖረናል:: ዳሩ ግን የተሰጠንን ተስማምተን የማንበላውና የማንጠቀምበት ከሆነ ተጨማሪውን አይሰጠንም ያለው ሲጨመርለት ከሌለው ግን ያው ያለው ሊወሰድበት ግድ ነው::

በሀገራችን ኢትዮጵያ ለተከሰተው የኑሮ ውድነት ችግር መንሥኤ አድርገው

ጥቂት ብዙም እንደማያስማማቸው በበግ የተመሰሉት ዳድቃን ግን አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ በመባባል ስሜት ስለሚኖሩ ብዙው ሳይሆን ጥቂቱ እንደማያጣላቸው መምህራን ያስተምራሉ::

ሁሉም ምሁራን ከሚስማሙበት አንድ ነገር የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ነው :: ይኸው የአየር ንብረት ለውጥ የፈጠረው የዝናም እጥረት ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ከብቶች እስኪያልቁና የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ለድርቅ የሚጋለጡበት ሥጋት ላይ እስኪወድቁ ድረስ ማስጨነቁን ቀጥሏል:: የተከሰተውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋትም እንደመፍትሔ የተቀመጠው አንዱ ነጥብ የፍጆታ መጠናቸው ከፍተኛ የሆኑ ምርቶችን ማሳደግ የሚል ነው:: እንግዲህ የኑሮ ውድነቱን ምክንያትና መፍትሔውን ስንመለከት ተስፋው ሁሉ በተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ነው:: ተፈጥሮን ፈጥሮ በቁጥጥሩ ሥር ያደረገ ደግሞ የፍጥረቱ ሁሉ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ በተፈጠሩልን ነገሮች ሁሉ እንድንጠቀምበት ለሕጉ በመገዛት እሺ በጀ ብለን እንድንኖር ይፈልጋል:: ለሚሰጠን በረከት ዋስትና ያደረገውም ይህንኑ እሺታችንን ነው:: «እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ . . .» እንዲል /ኢሳ.፩÷፲፱/::

እግዚአብሔር አምላካችን አልዘንብ አለ እያልን የምንጨነቅበትንና በየዓመቱ ምህላ የምንገብርለትን ዝናብን ያዘጋጀው ለእኛ እንጂ ለእርሱ አይደለም:: ይህም ሊታወቅ «በሥርዓቴ ብትሔዱ

ወደ ፴፱ ገጽ ዞሯል



'

www.eotcmk.org

## ከድፍረት ኃጢአት...

ከገጽ ፯ የዞረ

ገኖ ቢኖር እንኳ ከውጤቱ ሐሰትነቱ ይገለጣል::

መግደልም እስከ ሕጋዊነት መብት ቢሰጠውም እንኳን ነፍስ መግደል የመግደል ርኩሰት እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ቅድስና ሊሆን አይችልም:: ሰውን ከዕለተ

ዕንሱ ጀምሮ በሥጋዊ ፈቃድ ማስገደል፣ ማስወረድ አእምሮአችን በራሱ ለመጽናናት ፈልጎ ቢስማማም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን መግደል መሆኑን ሊፍቀው የሚችል አንዳችም ኃይል የለም:: በዮሐንስ ራእይ አምስቱ ከለባት የተባሉትም ከላይ የተጠቀሱትን የድፍረት ኃጢአት የሚፈጽሙ በመሆናቸው ከእግዚአብሔር ርስት የላቸውም::

በአጠቃላይም ቅዱስ ዳዊት ከልዩ ኃጢአት ባሪያህን አድነኝ ማለቱ በእሱ ላይ ሌሎች ከሚፈጽሙበት ከሚታዩትም ከማይታዩትም የጨካኞች ሴራ ተጠብቆ ድኅነትን ማግኘት ሽቶ እንደሆነ ሁሉ እኛም ዕለት ዕለት ሰይጣን ካሴረውና ካጠመደው ክፉ ወጥምድ እንድናመልጥ ዓይኖቻችንን ወደ አባታችን እግዚአብሔር ማንጋጠጥ ተገቢ ነው:: ቅዱስ ዳዊት በኀልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር የድፍረት ኃጢአት ከመፈጸም ይጠብቀው ዘንድ ጸልዮአል:: ይህን ሲጸልይ እንስሳዊ ባሕርዩንና መልአካዊ ባሕርዩን አስማምቶ መልካም ነገርን ያስፈጽመው ዘንድ ሽቶ ነው::

ሰው በዕውቀትም፣ በዕውቀት ማነስም ርኩሰትን ይፈጽማል:: ክርስቲያን ከዚህ ርኩሰት ለመዳን አይቶና ሰምቶ፤ ዐውቆና ፈቃደ ሥጋውን ገትቶ፤ ንግግሩን አርሞ፤ በሕሊና የሚመጡትን ክፉ ፈቃዳትን ታግሶ የድፍረት ኃጢአትን ካልተዋት ዋጋው ምን ይሆን? «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» በማለት ጌታ የተናገረውን ማሰብና ንጽሕናን ገንዘብ ማድረግ ያስፈልጋል /ማቴ.፲፮፥፳፮/:: የተወደዳችሁ አንባብያን ሁላችንም የፈቃደ ነፍስን ሥራ በመሥራት እንዲሁም ትሩፋትን ገንዘብ በማድረግ ከድፍረት ኃጢአት እንጠበቅ ዘንድ ዘወትር አሰምተን አቤቱ «የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ» በማለት ልንጸልይ ይገባል:: ለዚህም አምላከ ቅዱሳን በረድኤቱ አይለየን፤ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በምልጃዋ ትርዳን፤ አሜን::✦


*ከሶሜን አሜሪካ ምን ይደመጣል?*

*መካነ ድር /website/*

http://www.mahiberekidusan.org

**www.tewahedomedia.org**

| | |
|---|---|
| ሬድዮ<br>ለኢትዮጵያና አካባቢዋ<br>17.690 MHz አጭር ሞገድ<br>ዘወትር ሰኞ<br>ከምሽቱ 4፡00-5፡00<br>(10pm-11pm) | ዲሲ<br>1390 AM<br>Abyssinia Radio<br>Saturdays<br>7pm - 7:30pm EST |
| አትላንታ<br>860 AM<br>WAEC<br>Sundays<br>7:30 pm - 8:00 pm EST | ዴንቨር<br>670 AM<br>KLT Radio<br>Sundays<br>8:00 pm - 9:00pm EST |


## «ማንኛውም ዜማ ...»

ከገጽ ፱ የዞረ

ክፍለ ዘመንም እግዚአብሔር ጥሩ አገልጋይ አድርጎ ሊያስነሣ ይችላል:: ሰው ሲፈጠር እንዲዘፍን፣ እንዲጨፍር፣ ዓለምን እንዲመስል አልተፈጠረም፤ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል እንጂ:: መጽሐፍ ቅዱስም «ሁሉም የልጁን መልክ እንዲይዙ ፈጥሯቸዋል» ነው የሚለው:: ስለዚህ ሰው በተሰጠው ስጦታ ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያገለገል ነው:: ንግግራችን፣ አስተሳሰባችን፣ እንጉርጉሮአችን የእግዚአብሔርን ክብር መግለጽ መቻል አለበት::

*ሐመር፦ አስቀድመህ ዜማና ግጥም ችህን ለሊቃውንት እንደምታሳይ ገልጸሃል፤ ዜማና ግጥም አዘጋጅተህ እንዲያርሙልህ የምታሳያቸው ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ውክልና የሰጠቻቸው ናቸው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ ቤተክርስቲያን መዝሙርን በተመለከተ እንዲገመግም ያደራጀችው ጠንካራ ተቋም የለም:: እኛም ይህ ባለመኖሩ ሥራችንን ሳናቆም ባለው አማራጭ እንጠቀማለን:: ይኸም በአጠገብህ የሚኖሩትን የዜማ መምህራን ማነጋገር ነው:: በቤተክርስቲያን ቅዳሴ የሚያስተምሩ መምህራን፣ መሪጌቶች አሉ:: ከእነርሱ ውጭ ሌላ የትም ቦታ አትሔድም:: ምክንያቱም ለዜማው ቅርብ እነርሱው ናቸው:: ግጥሞቹንም በተመለከተ እኔም የተወሰነ ጥረት አደርጋለሁ:: ከ፲፮ ዓመት በላይ በሰንበት ትምህርት ቤት ነው የኖርኩት:: ከዚያም በኋላ በክህነት አገልግሎት ቆይቻለሁ:: ሥነ መለኮት ትምህርት ቤትም ገብቻለሁ:: ያ በራሱ እንዴት መጻፍ እንዳለብኝ ብዙ ያግዘኛል:: ቢሆንም ግን የምሰማው፣ የማነበው ነገር ብቻውን በቂ አይደለም:: ቅድም እንዳልኩት ዜማውን ለዜማ ሊቃውንት ስወስድ ግጥሙን ደግሞ ከመምህራኖች ጋር እየተነጋገርኩ የምሠራበት ጊዜ አለ:: ለመምህር ደጉ፣ ለመምህር እሸቱ ግጥሞቼን አሳይቼአቸው አውቃለሁ:: የትርጓሜ መምህራን ለሆኑ፣ ጥሩ ዕውቀት ላላቸው እያሳየሁ እሠራለሁ::

*ሐመር፦ ከአንተ ሥራ ውጭ የሌሎቹን ግጥምና ዜማ ስትመለከታቸው ምን ያህል ሥርዓት የጠበቁ ናቸው? ከዘፈን ጋር ስለሚመሳሰሉ ዜማዎችስ የምትለን ካለ?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ የአንዳንዶችን ግጥም ስመለከት ወረድ ያሉ ግጥሞችን እመለከታለሁ:: ግጥሞቻቸውን ይዘው እኛ ጋር ይደውላሉ:: ወይም አልፎ አልፎ እኔም ለጥናት ስሔድ ግጥሙን እያየሁላቸው የማስተካክልበት ጊዜ አለ:: አንዳንዶች ትክክል እየጻፉ እየመሰላቸው የሚያበላሹ አሉ:: የወረደ ግጥም የሚጽፉበት ጊዜ አለ:: እንደዚሁ ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ከዘፈን ጋር የሚመሳሰሉ ዜማዎችን ታያለህ:: በአንድ ወቅት የእኔን ሥራ ከዘፈን ጋር ይመሳሰላል ተብሎ አስተያየት ተሰጥቶኝ ነበር:: ከዘፈን ጋር የተመሳሰለበትንም ሁኔታ አይቻለሁ:: እኔ መዝሙር ቀድሜ አውጥቼ በኋላም አንድ ዘፈን ወጣ:: አንዳንድ ጊዜ ዘፈኑ ቀድሞ ወጥቶ በኋላ መዝሙሩ ይወጣል:: ታዲያ ሰዎች ይህን ዘፈን ይህኛውን መዝሙር ይመስላል ይሉኛል:: ዋናው ነገር የእኛ የኢትዮጵያውያን የዜማ ስልታችን፣ ልቅሶአችን፣ እንጉርጉሮአችን አንድ ዓይነት ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ ሳይታወቅ የመወሳሰድ ነገር ሊፈጠር ይችላል:: በዚህ ነገር ግን መጠንቀቅ እንዳለብን አምናለሁ::

ቤተክርስቲያኒቷ የዜማና የሥነ ቃል ባለቤት ናት:: የቀድሞዎቹን ዘፋኞች በአብዛኛው ስንመለከታቸው ቤተክርስቲያን የነበሩ በኋላ ከቤተክርስቲያን የወጡ ናቸው:: አብዛኞቹ ዘፋኞችም ኦርቶዶክሳውያን ናቸው:: ቤተክርስቲያኒቱ ያላትን ሀብት ነው ዓለም እየተጠቀመበት እያደገ የመጣው:: «ይትባረክ እንደ አብርሃም፣ ዘለሰኛ»... የሚሉትን ዜማዎች ዘፋኞች በካሴት እያወጡት ነው:: ነገ ከነገ ወዲያ እነዚህን ዜማዎች ዘፈኑ ስለነካው ብቻ እየተውነው፣ እየተውነው ከመጣን፤ ምናልባት «አሐዱ አብ ቅዱስ» ሊሉም ከቻሉ ልንተወው ነው? ስለዚህ ቤተክርስቲያኒቷ መብቷን ማስጠበቅ፣ ከዘፋኞቹ ጉሮሮም አውጥታ የራሴ ነው ብላ መከራከር አለባት::

*ሐመር፦ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የሚወጡት መዝሙሮች ሥርዓት የጠበቁ አይደሉም እየተባሉ ይተቻሉ፤ የአንተ አስተያየት ምንድን ነው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ የዜማ ሥርዓት እየተጠበቀ አይደለም የሚሉ አስተያየቶችን እኔም እሰማለሁ:: በመጀመሪያ ነገሮችን ቀና አድርገን ማየት ያስፈልጋል:: በአንድ ወቅት አንድ ዘማሪ «እግዚአብሔር በመንግሥቱ አለ» ብሎ ዘመረ ብለው ሲተቹት ሰምቻለሁ:: ቅዳሴው ማኅሌቱ እንዴት ይዘመራል? ለምን በካሴት ይወጣል? ብለው የማይደሰቱ ሰዎች ነበሩ:: ዝም ማለት ግን በአሁኑ ወቅት መፍትሔ አይሆንም:: በአሁኑ ጊዜ ዘፈን ገዝቶ የሚያዳምጠው ኦርቶዶክሳዊ ነው:: እነዚህን ኦርቶዶክሰውያን ለመመለስ የምንሠራው ሥራ ምን መሆን አለበት? ስለዚህ አሁን በዜማ ሥርዓት የሚጨነቁት፣ ትክክል አይደለም የሚሉ ሰዎች ባላቸው ችሎታ እየሠሩ ቤተክርስቲያኒቱን በማገልገል እኛንም ማስተማር አለባቸው:: እየሠሩ ሊያስተምሩን ያስፈልጋል:: ከተሳሳትን እንዴት እንደሚዘመር እያስተማሩን፣ እነርሱ እየቀደሙ እኛ ልንከተላቸው እንችላለን:: ከሠሩ ደግሞ የበለጠ እኛን ሊያስተምሩን ይችላሉ::

*ሐመር፦ ቤተክርስቲያን መዝሙርና ግጥምን በቅድሚያ የሚያርም ማዕከላዊ ተቋም ይኑራት ለሚለው ተደጋጋሚ*

ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



'
www.eotcmk.org

# «ማንኛውም ዜማ ...»

ከገጽ ፴፫ የዞረ

*ጥያቄ ያንተ አስተያየት ምንድነው?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ የቤተክርስቲያን መዝሙሮችን ግጥሞችን የሚያርም፣ የሚያደራጅ፣ የሚቆጣጠር አለመኖሩ ሊጎዳት ይችላል:: ማንኛውም ሥራ ማዕከላዊነት ቢኖረው በጣም ያስደስታል:: በደንብ መሥራት፣ መማር የሚቻለው ማዕከላዊነት ሲኖር ነው:: አንዳንድ ሰዎች ችግርም ሳይኖር ችግር አለ የሚሉት ማዕከላዊነትን የጠበቀ ሥራ ስለሌለ ነው::

*ሐመር፦ ቀረ የምትለው የምታስተላልፈው መልእክት ካለህ?*

ዲ/ን አሸናፊ፦ አብዛኛውን ጊዜ ቀና፣ ቀናውን የሚሻለንን፣ የሚጠቅመኝን ነገር እያየን ብንሄድ ጥሩ ነው:: ማኅበረ ቅዱሳን ጥሩ ጎን እንዳለው ሁሉ የተለያየ ነገርም ትሰማለህ፤ ጥሩ አይደለም የሚሉ አሉ:: እናንተ ጋርም መጥቶ ዘማርያን እንደዚህ ናቸው ብሎ ክፉ ነገራችንን፣ ያልዋልንበትን ይነግሯችኋል፤ ሌላው ደግሞ አባቶች እንዲህ ናቸው ብለው ያልዋሉበትን ይነግሯችኋል:: ቀና ቀናውን ያለማየት የደፈረሰውን ብቻ የማየት አባዜ ይዞናል:: ስለዚህ አንዳችን በአንዳችን አንጠቀምም:: ሁሉም በራሱ ነው የሚሄደውና የአመለካከት ለውጥ በጣም ያስፈልገናል:: ሁለንም የሚያጸድቅ፣ የሚመዝን አንድ እግዚአብሔር ነው:: በቀናነት ሆነን ብናገለግል በአገልግሎታችን የበለጠ አፍሪካን ማዳረስ እንችላለን::

እነዚህ ዝማሬዎች የቤተክርስቲያንን ክብር አስጠብቀዋል፤ የመናፍቃንን ዝማሬዎች ቀጥ ያደረጉት እነዚህ መዝሙሮች ናቸው:: በአሁኑ ሰዓት ክርስቲያኖች በሞባይል ስልካቸው፣ በመኪናቸው፣ በቤታቸው መዝሙር የሚሰሙ ሰዎች በዝተዋል:: ያ የዝማሬው አገልግሎት ትልቅ አስተዋጽዖ ነው:: በጣም ትልቅ ተጋድሎ የተከፈለበት ነው:: ለአገልግሎት ወደ ገጠር ስንሔድ የመዝሙር ካሴትን ጠቀሜታ ማየት ይቻላል:: ቴፕ ከፍቶ መዝሙር ሰምቶ፣ ሐመርና ስምዐ ጽድቅን አንቦ የሚመለስ በጣም ብዙ ሰው ነው:: አዲስ አበባ ያለነው ሰዎች ምንም ስለማይጎድልብን ጥቅሙን ላናውቀው እንችላለን:: አዲስ አበባ ሰባኪ፣ ካህን፣ ዘማሪ ከፈለግን እንደልብ እንደ ብፌ ግብዣ ነው የምናገኘው:: ገጠር ያለው ሰው ግን በዚህ አገልግሎት ምን ያህል እንደሚጠቀሙ የምታውቀው ሔደህ ስታይ ነው:: እና የዝማሬ አገልግሎት የቤተክርስቲያንን ክብር አስጠብቋል፤ የመናፍቃንንም አፍ አዘግቷል ብዬ አምናለሁ::

✥



# «ሁሉም ዜማ...»

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ቅዱስ ነው:: ዜማውን ደግሞ ከቅዱስ ያሬድ በመሆኑ እኛ መባል ያለብን አቀናባሪዎች ነው::

*ሐመር፦ ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በያሬዳዊ ዜማ ትገለገላለች:: አኀት አብያተ ክርስቲያናት /እስክንድርያ፣ ሶርያ. . ./ ዜማውን አያውቁትም:: ከዚህ አንፃር ለእኛ የያሬድ ዜማ ጥቅሙ ምንድን ነው?*

መ/ር በየነ፦ ይህ ዜማ የተሰጠን በቅዱስ ያሬድ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ነው:: እንደ ዘመን አቆጣጠራችን ዜማው የራሳችን መለያ ነው:: ለምሳሌ፡ ካቶሊካውያን በሮም ውስጥ የእኛ ዓይነት የቅዳሴ፣ የማኅሌት ሥርዓት የላቸውም:: በኢትዮጵያ ግን ቅዳሴ ይቀድሳሉ፣ ማኅሌት ይቆማሉ:: ለእኛ ያሬዳዊ ዜማ ለሀገር ኩራት፣ መለያችን፣ መታወቂያችን ነው:: በመንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ ትኩረት ቢሰጠው ኖሮ ትልቅ መኩሪያ ነበር:: ይህ ቅርሳችን፣ መታወቂያችን በመሆኑ ለሀገራችንም ትልቅ ቅርስ በመሆኑ ተንከባክበን ልንይዘው ይገባል:: ከዚያ አንጻር ደግሞ ቅድስት ቤተክርስቲያን ዜማው ለሥርዓተ ቤተክርስቲያንና ለምእመናን ሡነምግባር ካለው ጥቅም አንጻር በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለዝማሬ ይህን እንድንጠቀም አድርጋለች:: ይህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ነው:: ቤተክርስቲያን ደግሞ የሚመሯት አባቶቻችን ናቸው፤ ካላመዕን በስተቀር::

*ሐመር፦ አንዳንዶቹ ዜማ የኃጢአትና የጽድቅ ጉዳይ አይደለም ይላሉ፤ ካልሆነ ለክርስቲያኖች ያለው ጥቅም ምንድን ነው? ከያሬድ ዜማ ውጪ የሚጠቀሙትን ኃጢአት ሠሩ እንላቸዋለን?*

መ/ር በየነ፦ ድፍረት ባይሆንብኝ ዘፈን ነው የምለው:: እኔ በተለይ በአሁኑ ወቅት ያሉትን መዝሙሮች እንደተነገረኝም ከሆነ ከሱዳን ዜማ፣ ከተለያዩ ዘፈኖች የተወሰዱ ናቸው:: ዘፈን ደግሞ ኃጢአት ነው፤ መዝፈን የለብንም:: አንዳንድ ዘማርያን ሲዘምሩ እንደ ዛር የሚያርገፈግፉቸው አሉ:: አንድ ጊዜ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የአንድ ዘማሪ ካሴት ይመረቃል ተብሎ ከአንድ ወዳጄ ጋር ሔድን:: በዚያ መካከል በእንግድነት የተገኙ አንድ ትልቅ አባት ነበሩ:: መዘምራኑ ያወርዱታል፤ እንደ ዛር ይዘለላል፤ የነበረውን እንቅስቃሴ ማየት ይከብዳል:: መጨረሻ ላይ በወቅቱ የነበሩት ጳጳስ ሊያሳርጉ ተነሥተው ሲናገሩ «ልጆች መዝሙሩ ጥሩ ነው፣ ግን ያሬዳዊውን ባትለቁ... ደስ ይለኛል..» ብለው ይህችን ቃል ሲናገሩ አእምሮዬን መታኝ:: እኒያን ጳጳስ ባየኋቸው ቁጥር አከብራቸዋለሁ:: እንዲህ ብሎ የሚቆጣ አባት የለም:: እናም ከአዘማመሩ ጀምሮ ሳየው ለኃጢአት የሚያነሣሣ ነው ባይ ነኝ::

*ሐመር፦ የያሬዳዊ መዝሙር መሥፈርቱ ምንድን ነው?*

መ/ር በየነ፦ የያሬዳዊ ዜማ መሥፈርቱ ይታወቃል:: እኔም ከየት እንደ ተወሰደ አውቀዋለሁ::

ከድጓ፣ ከሰዓታት. . . የተወሰደ ከሆነ ይታወቃል:: ስለዚህ የቤተክርስቲያንን ዜማ አባቶች ያውቋቸዋል፤ መስፈርትም አላቸው::

*ሐመር፦ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለክርስቲያኑ የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድን ነው?*

መ/ር በየነ፦ ትልቁ ነገር ዜማና ዘፈንን መለየት ነው:: መዝሙር ሰዎችን ወደ ንስሐ ሕይወት የሚመልስ ዘፈን ደግሞ ወደ ደስታ ጭፈራ የሚወስዱ ናቸው:: ቅዳሴ እየተቀደሰ በተመስጦ እያለን ሳቅ ይመጣብናል? ደስታ ይመጣብናል? የማይሆን ነው:: ያሬድም በማኅሌት ሲዘምር እንዲሁ ነው:: ጭልጥ ወዳለ ተመስጦ ጽርሐ አርያም፣ ሰማየ ሰማያት ነው የምንሔደው:: ዘፈን ግን እንዲህ አይደለም፤ ምድራዊ በመሆኑ እዚሁ ያልቃል፣ ያበቃል ማለት ነው::

ያሬዳዊው ዜማ ግን የኢየሱስ ክርስቶስን መያዙን፣ መሰቀሉን፣ መገፋቱን፣ መከርኮሙን፣ ፲፫ቱን ሕማማተ መስቀል፣ መስቀሉን ተሸክሞ መኖርን እንድናስብ የሚያደርገን ሕያዊት ነፍሳችን እንዲኖራት የምትፈልገው የዘላለም ዕውቀት ነው::

*ሐመር፦ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን እንዲጠበቅ ማድረግ ያለበት ማነው?*

መ/ር በየነ፦ ጠቅላይ ቤተክህነት ነው:: እኔም በአለችኝ አነስተኛ ዕውቀት አብሬ አግዛለሁ፤ ችግሩ ጠቅላይ ቤተክህነት ይህን መሰብሰብ አለመቻሉ ነው:: አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ መስመር ማስያዝ ይቻላል:: በቤተክህነት ያላለፈ በሊቃውንቱ ያልታረመ ዜማ ቤተክርስቲያን እንዳ ይዘመር ካደረገች ያ ሰው ዕውቅና የለውም ማለት ነው::

በአብዛኛው አሁን ገበያ ላይ ያሉት መዝሙሮች ሥርዓት የጣሱ ወደ ዓለማዊነት ያደሉ ናቸው:: ካሴቱ ከዘፈን ይልቅ በከፍተኛ ዋጋ መሸጥ ጀምሯል:: ቤተክርስቲያንስ ማንኛውንም ሰው ነው የምታዘምረው? ማነው ያ ሰው? መጠየቅ አለባት:: ቤተክርስቲያኒቷ ተነሥቶ ለሚዘምረው ሁሉ ዕውቅና ከሰጠች ለፈተና ትጋለጣለች::

ግጥሙም ከዶግማ አንጻር ትክክል ነው ወይ? በማለት የሊቃውንት ጉባኤው ሊያየው ይገባዋል:: ዜማውንም እንደዚሁ ዜማ፣ አቋቋም በሚያውቁ ሰዎች የተዋቀረ ኮሚቴ ሊያየው ይገባል:: ለዚህ ነገር በቀን አንድ ሰዓት እንኳን እየሰጡ

ወደ ገጽ ፴፰ ዞሯል



www.eotcmk.org

# ክህነት በቅዱስ ...

ለሌሎች ለመስጠት ወይም በጥላቻ ወይም ከማንኛውም ብልሹ ኀሊና የተነሣ እንዲወርድ ቢደረግና ቢሳደድም ያው ነው:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከጠላቶቹ እጅ የደረሰበትን ሰው ግን በክፋታቸው እርሱን ምን ያህል እንደሚያከብሩትና እንደሚጠቅሙት ለማሳየት አንድ ቃል እንኳ መናገር የሚያስፈልግ አይመስለኝም::

ስለዚህ በሁሉም አቅጣጫ ልንጠነቀቅና የዚህ ፍቅረ ሲመት ጥላሸት ወይም ፍንጣሪ ምናልባት በስውር የሆነ ቦታ ውስጥ ተዳፍኖ ሳይታይ ውስጥ ውስጡን እየነደደና እየፋመ እንዳይሆን በጥንቃቄ መፈለግ ይገባናል:: መጀመሪያ ከዚህ ጾር ነጻ የሆኑ ሰዎች ሓላፊነቱን ከያዙ በኋላም እንደ በፊቱ ነጻ እንዲሆኑ ማሰብና መጠንቀቅ ይገባልና:: ነገር ግን ሹመቱን ገና ሳያገኘው ይህን ጨካኝና አስፈሪ ነገር ቢናፍቅና ቢመኝ ካገኘው በኋላ ራሱን ወደ ምን ዓይነት እሳት ውስጥ እንደሚወረውር ለመናገር አይቻልም::

እኔ ይህ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ አለብኝ (እዚህ ላይ እንዲሁ ራስን ለማዋረድ ብዬ እውነት ያልሆነ ነገር ይነግረኛል ብለህ አታስብ)፤ ይህ ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ሲደመር በከባድ ሁኔታ አስደነገጠኝ፤ እሸሽ ዘንድም አሳመነኝ:: ሰብአዊ ፍጥረትንም ሆነ ሌላ ነገር የወደዱ ሰዎች ከሚወዱት ነገር አጠገብ እንዲሆኑ ዕድል ካገኙና ከተፈቀደላቸው በውስጣቸው የበለጠ ይሰቃያሉ:: ፍላጎታቸው ከታሰረበት ነገር የሚቻለውን ያህል በራቁ መጠን ግን ጾራቸውን ማድከምና ማራቅ ይችላሉ:: ይህን ክብር የሚፈልጉትም በቀረቡት መጠን ክፋቱ ሊታገሡት የማይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን ሲርቁትና እርሱን ተስፋ ማድረግን ሲያቆሙ ምኞቱ ከተስፋው ጋር አብሮ ይጠፋል::

፲፪. ይህ አንዱ ምክንያት ብቻ ራሱ ቀላል አይደለም፤ ይህ ብቻ እንኳ በራሱ ራሴን ከዚህ ክብር ለማራቅ በቂ ነበር:: ሆኖም ግን ከዚህ ያላነሰ ሌላም አለ እንጂ:: እርሱ ምንድን ነው? ካህን ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ለብዙዎችም እንደሚኖር አእምሮው የሚያስብ፣ ረጋ ያለ፣ ጥልቅ ማስተዋልና መረዳት ያለው እና በሁሉም አቅጣጫ የሚያዩ ባለ ብዙ ዓይኖች ሊሆን ይገባዋል:: እኔ ግን ደካማና ሰነፍ የሆንሁ፣ የራሴን ድኅነት እንኳ ለመፈጸም እየተንገዳገድሁ ያለሁ መሆኔን ለእኔ ካለህ ፍቅር የተነሣ ስሕተቶቼን የምትሸፍነው አንተ ራስህ እንኳ የምታምነው ነገር ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለ መጾም፣ ወይም መሬት ላይ ስለ መተኛትና ስለ ሌላ የሰውነት ገድል አትንገረኝ:: በእነዚህ ነገሮች እኔ

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ምን ያህል ብዙ የሚጎድለኝና ደካማ እንደ ሆንሁ ታውቃለህና:: እንዲሁም በጥንቃቄ የፈጸምኳቸው ብሆን ኖሮ እንኳ አሁን ባለው ስንፍናዬ ለዚህ የሥልጣን ቦታ እነዚህ በራሳቸው ምንም ሊጠቅሙኝና ሊያገለግሉኝ አይችሉም ነበር:: እነዚህ ነገሮች በበዓቱ ለዘጋና ስለ ራሱ ብቻ ለሚያስብና ለሚጋደል ሰው ታላቅ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል:: ብዙ በሆኑ ሰዎች መካከል ሲከፈልና በእርሱ ጥበቃ ሥር ወዳሉት ወደ እያንዳንዳቸው የግል ጥበቃና እንክብካቤ ሲገባ ግን ጠንካራና እጅግ ጽኑዕ የሆነ ሰብእና ያለው ካልሆነ በስተቀር እነርሱን ለመጥቀምና የተሻሉ ለማድረግ ምን ነገር ሊበቃው ይችላል?

፲፫. ከዚህ ጥንካሬና ጽናት ጋር በተያያዘ በነፍስ ሊኖር የሚገባ ሌላ የጥንካሬ መለኪያ ብፈልግ የሚገርም አይሁንብህ:: ለምግብና ለመጠጥ እንዲሁም ለሚመች መኝታ ግድ የሌለው መሆን ለብዙዎች ብዙም ከባድ የሆነ ነገር እንዳልሆነ እናያለን:: ቢያንስ ጽኑዕና ሻካራ የሆነ ሕይወትን ለለመዱና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ላደጉ፣ እንዲሁም ለሌሎች ለብዙዎች በጣም ከባዶች አይደሉም፤ ይህም ሰውነትን ማለማመድና ልምድን ማስገዛት የእነዚህን አድካሚ ተግባራት ከባድነት ስለሚያለሰልሰው ነው:: ነገር ግን ቁጣ፣

> *ካህን ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ለብዙዎችም እንደሚኖር አእምሮው የሚያስብ፣ ረጋ ያለ፣ ጥልቅ ማስተዋልና መረዳት ያለው እና በሁሉም አቅጣጫ የሚያዩ ባለ ብዙ ዓይኖች ሊሆን ይገባዋል:: እኔ ግን ደካማና ሰነፍ የሆንሁ፣ የራሴን ድኅነት እንኳ ለመፈጸም እየተንገዳገድሁ ያለሁ መሆኔን ለእኔ ካለህ ፍቅር የተነሣ ስህተቶቼን የምትሸፍነው አንተ ራስህ እንኳ የምታምነው ነገር ነው::*

ስድብና ነቀፌታ፣ ሻካራ ንግግር፣ በመሪዎችም ሆነ በተመሪዎች የሚነገርን ስድብና ተግሣጽ /አግባብ የሆነም ይሁን ያልሆነ/ መቻልን ጥቂቶች ብቻ ሊታገሡት የሚችሉት ነገር ነው:: በርግጥም እዚህና እዚያ ያሉ አንድ ወይም ሁለት ብቻ፤ ቀድመው በተነገሩት ነገሮች ላይ ጠንካራ የሆኑ ሰዎች እንኳ ከክፉ የዱር አውሬዎች የባሰ አስፈሪዎችና አውሬዎች እስኪመስሉ ድረስ ፈጽመው ሲበሳጩ ይታያሉ:: በተለይ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ክህነት ከደረሰበት እንዳይደርሱ ማድረግ ከክህነት ወሰን ክልል ውጭ ሊደረጉ ይገባል:: ካህን ምግብን ባይጾምና ችላ ባይል ወይም በባዶ እግሩ ባይሄድ በቤተ ክርስቲያን ተግባርና ደኅንነት ላይ ምንም ጉዳት አይደርስም:: ቁጡ መንፈስ ግን ለራሱ ለባለቤቱም ለጎረቤቶቹም ታላቅ ጉዳት ያደርሳል:: እንዲሁም እነዚያን በማያደርጉ ላይ የተነገረ መለኮታዊ ቅጣት የለም፤ ያለ ምክንያት በሚቆጡ ላይ ግን ሲዖልና የሲዖል እሳት እንደሚጠብቃቸው ተነግሯል:: ውዳሴ ከንቱን የሚወድ ሰው ብዙዎችን ማስተዳደርን ገንዘብ ሲያደርግ በእሳቱ ላይ ተጨማሪ ነዳጅ ይጨምርበታል:: ስለዚህም ብቻውን ሳለ በራሱ ወይም ከጥቂቶች ጋር ብቻ ሳለ ቁጣውን መቆጣጠር ያልቻለና ቁጣው እንዳሻው የሚነዳው ሰው መንጋውን እንዲመራ ሓላፊነት ቢሰጠው እርሱ ራሱም በሰላም መኖር አይችልም:: በምእመናን ላይም በጣም ብዙ በሆኑ ጦረኞች ተከቦ እንደሚዋከብ አውሬ ይህ ነው የማይባል ሁከትና ችግር ይፈጥራል::

፲፬. የአመክንዮን ብሩህነት፣ የኅሊናን ንጹሕ ዕይታና ሚዛን የሚያደበዝዝና የሚያጨልም እንዳልተገራ ቁጣ ያለ የለም:: «ቁጣ አስተዋዩን እንኳ ያጠፋልና» እንዳለ:: (ምሳ.፲፭፥፩) በጨለማ በሚደረግ ውጊያ የነፍስ ዓይን ስለሚጨልምባት ወዳጅን ከጠላት መለየት እንደማትችልና እንዲህ በማድረጓ የሚደርስ ጉዳት ቢኖር እንኳ ለጊዜያዊ ደስታ ለማግኘት ስትል ሁሉንም በአንድ ዓይነት መንገድ እንደምታያቸው ነው:: የቁጣ እሳት ነፍስን ከእርካታ በበለጠ ያስጨክናታል፤ ጤነኛ ሁኔታዋን ሙሉ በሙሉ ያናውጸዋል:: ሰዎችን ወደ ዕብሪት፣ ኢምክንያታዊ ወደ ሆነ ጥላቻ ያነሣሣቸዋልና፤ ከንቱና ብላሽ የሆኑ ነገሮችን ለማድረግ ዝግጁ ያደርጋቸዋል:: ይህን የመሰሉ ብዙ ነገሮችን ወደ ማለትና ማድረግ ይገፋፋቸዋል::

*ባስልዮስ:-* እንዲህ ያለውን ስውርና ውስጠ ወይራ ነገርህን ከእንግዲህ ወዲህ ልታገሥ አልችልም፤ አንተ ከዚህ ድካምና ጾር ምን ያህል የራቅህ መሆንህን የማያውቅ ማን አለና ነው እንዲህ የምትለው?♦

*ይቆየን!*



www.eotcmk.org

# በጆሮአችን የሰማነውን...

በወቅቱ በርካታ ሊቃውንት እንደነበሩ ይነገራል:: ቀደም ሲል ዓመቱን ሙሉ ሰዓታት፣ ስብሐተ ነግህና ቅዳሴ አይታጎልበትም ነበር:: አሁን ግን አገልጋይ በማጣቱ በከፍተኛ ችግር ላይ ይገኛል:: ቤተክርስቲያኑ ቀደም ሲል ይተዳደርበት የነበረው ርስት በመወረሱ አሁን ምንም መተዳደሪያ የለውም:: በቤተክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የንዋየ ቅድሳት ችግር ይታያል:: የሚያሳዝነው ነገር ያንን የመሰለ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን በጥንታውያን ሥዕሎች አለመሞላቱ ነው:: ግድግዳውም ተሰነጣጥቋል፤ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ከባድ ጉዳት ሊደርስበት ስለሚችል አሁን ልንታደገው ይገባል:: አሁን ያለው ሕንጻ ቤተክርስቲያን በ፲፱፻፳ዎቹ የተሠራ እንደሆነ አቶ ንጉሤ አስረድቶናል:: በቀድሞ ጊዜ ይፈጸሙ ከነበሩ ተአምራት ውስጥ አንዱን አቶ ንጉሤ ሲገልጹልን የተክለ ሃይማኖት ገድል ከመነበቡ በፊት ፲፪ ጋን ውኃ ይሞላ ነበር፤ ገድሉም ሲነበብ በጋን ውስጥ ያለው ውኃ ይፈላል:: በዚህ ጠበልም በደዌ ዳኛ፣ በአልጋ ቁራኛ የተያዙ፣ አጋንንት የሚያሰቃያቸው ሰዎች ተጠምቀው ይድኑ ነበር::

በአሁኑ ወቅትም የተለየዩ ተአምራቶች ይፈጸማሉ:: ሕሙማንም እየተፈወሱ ይገኛሉ:: ከውጭ ሀገር ሳይቀር ብዙዎቹ መጥተው ተጠምቀው ከበሽታቸው የሚፈወሱበት ቦታ ነው:: በሀገር ውስጥም በሐኪም ተስፋ የላችሁም ከተባለ በኋላ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ወደዚህ ጠበል በመምጣት ጠጥተው፣ ተጠምቀው የተፈወሱ ምእመናን በርካታ ናቸው::

ብፁዕነታቸው ለካህናቱ እንደ ኮሳ ቅድስት ማርያም በየወሩ አምስት መቶ ብር በጀተውላቸዋል:: ቅርሶቹ የሚቀመጡት በአለቃው መኖሪያ ቤት ውስጥ ነው:: ቤተክርስቲያኑ በመኪና መንገድ አጠገብ የሚገኝ በመሆኑ ቱሪስቶችም ሊጎበኙትና ለቤተክርስቲያኑ የገቢ ምንጭ ማግኘት የሚችሉበት ዕድል አለ:: እንደ ኮሳ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በዚህ ቦታ ጥንታውያን ቅርሶች የሰውያለህ እያሉ ይጣራሉ:: የነገሥታቱ አልባሳትና የተለያዩ የብራና መጻሕፍት ከአቀማመጥና ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ አደጋ ላይ ናቸው:: ሰበካ ጉባኤውና ምእመናን ሊያስብበት ይገባል:: ብፁዕነታቸው ቡራኬ ሰጥተው፤ ከጅማ ፴ ኪ.ሜ ርቀት ወደሚገኘው በማና ወረዳ ኬንተሪ ቅዱስ ሚካኤል ተጓዝን::

በማና ወረዳ የሚገኘው የኬንተሪ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በሀገረ ስብከቱ ተዘጉ ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ወደሆነው ገብተን ተሳለምን:: ከዚያም የቢሊዳ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ተሳልመን ወደ ጅማ ገባን::

በብፁዕነታቸው ቤት መስተንግዶ ተደረገልን:: ሻይ ቡና ብለን ዐረፍ አልን:: ብፁዕነታቸውና ሊቀ መዘምራን ግን ብርቱ

ከገጽ ፴ የዞረ

ናቸው የድካም መንፈስ አይታይባቸውም ዕረፍታቸው ሥራ፣ ልማት ነው:: ከጥቂት የዕረፍት ቆይታ በኋላ ከጅማ ፳ ኪ.ሜ ርቀት የቦ ቅዱስ ሚካኤል ላይ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ጉባኤ እያደረጉ መሆኑ ሲነገረን ወደዚያው አመራን:: ሰፊ ጉባኤ ነበር:: ለብፁዕ አባታችንም ከፍተኛ አቀባበል አድርገው ተቀበሏቸው::

ለሦስት ቀናት በተዘጋጀው ጉባኤ በርካታ ሕዝበ ክርስቲያን ነጭ በነጫቸውን ለብሰው ተሰባስበው ሲማሩ ይታዩ ነበር:: የመናፍቃንን ወረራ የሚከላከሉበት የቃለ



*የተቃጠለችው ጥንታዊቷ ጨጐ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ፍርስራሽ*

እግዚአብሔር ስንቃቸውን እየሰነቁ እንደሆነ የግቢ ጉባኤው ተወካይ ዲ/ን ዓለማየሁ አስረድቶናል:: ጉባኤው በጸሎት ከተዘጋ በኋላ ወደ ጅማ ተመለስን:: እኛም ከብፁዕ አባታችን ቡራኬ ተቀብለን ወደ ማደሪያችን አቀናን::

በማግስቱ የካቲት ፳፬ ቀን ፳፻ ዓ.ም ከ፻ ዓመት በላይ ዕድሜ ወዳስቆጠረው በልፎ ባለወልድ ቤተክርስቲያን ተጓዝን:: ቤተክርስቲያኑ ጥንታዊ ቢሆንም አስታዋሽ ያጣ መሆኑ ሁኔታው ይናገራል:: በጅማ ሀገረ ስብከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በአብዛኛው ያሉበት ሁኔታ አሳሳቢ፣ አሳዛኝ መሆኑን እየተነጋገርን አጋሮ ከተማን አልፈን ወደ ጨጎ ቅዱስ ገብርኤል ተጓዝን::

ጨጎ ትንሽ የገጠር ከተማ ስትሆን ከጅማ ፷፪ ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል:: የጨጎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በአክራሪ እስላሞች ከነጽላቱ ሙሉ በሙሉ የተቃጠለ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: ጉዞአችንም ሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ያለበትን ሁኔታ፣ በአጥቢያው ያሉ ክርስቲያኖችን መንፈሳዊ ሕይወት ለማየት ነበር ::

ጨጎ ስንደርስ የፀሐዩ ሐሩር ጠንክሯል፤ ሙቀቱ ለአዲስ ሰው ያስጨንቃል:: ከቤተክርስቲያኑ መዳረሻ አካባቢ የሰኞ ገበያ ይቆማል። ገበያው ደርቷል። ከየአቅጣጫው ገበያተኛው መጥቶ ጨጎ ተጨናንቃለች:: መኪናችንን እንደምንም ከገበያው ዳር አቆምናት:: ገበያውን አቋርጠን ስንጓዝ፣ የአራታችንም አካሔድ በሰልፍ ነበር:: ሊቀ መዘምራን እየመሩ፣ እኛ ከመሀል፣ ሹፌራችን ክርስቲያኑ መሐመድ ከኋላ ተከተልናቸው:: ቀድሞ ያ አሰቃቂ ድርጊት የተፈጸመበት በመሆኑ በዐይነ ኅሊናችን እየታወሰን ነው መሰል ቦታው ያስጨንቃል ተራራውና ቁልቁለቱ ተጨምሮ ከፀሐዩ ጋር ስላደከመን መራመድ እየተሳነን በዝምታ ዳገቱን ተያያዝነው:: በውስጣችን ፍርሃት ስላለ ይሆን የማናወራው? ዳገቱ አፋፍ ላይ ወጣ ስንል ፊት

ለፊታችን በቆርቆሮ የታጠረ ቤተክርስቲያን አየን:: ትንፋሻችን እየተቆራረጠ፣ ሰውነታችን እየራደ አይደርስ የለ ደረስን::

የቤተክርስቲያኑ በር በቁልፍ ተቆልፏል:: ሰው ዝር አይልም:: ለዚያውስ የትኛው ምእመን! ቦታው ፀጥ ረጭ ብሏል:: የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ቄስ ጸዳሉ ማኅበረ ቅዱሳን ቤተክርስቲያኑ ከተቃጠለ በኋላ ለማቋቋሚያ እንዲሆን በከፈተላቸው ወፍጮ ቤት ነበሩ:: እኛን ሲያዩ ሮጠው ተከተሉን፤ ከሊቀ መዘምራን በኋላም ከእኛ ጋር ሰላምታ ተለዋወጥን:: ወደ ግቢው እየመሩን እኛም ተከተልናቸው:: ከኪሳቸው ቁልፍ አውጥተው በሩን ከፈቱት፤ ወደ ውስጥ ከገባን በኋላ መልሰው ዘጉት:: መቼም ይህ ስጋታቸው ለሁላችንም ግልጽ ነበር:: ለምን ይዘጉታል ብለን አልጠየቅናቸውም::

በዓይኖቻችን አሳዛኙን የቤተክርስቲያኑን ቃጠሎ አየነው:: የቃጠሎው ቅሪት በግቢው ተከምሯል በኅሊናችን ዘመነ ሰማዕታትን አስታወስን:: ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጽር ገብተን መከራውን የተቀበለችውን ምድር ተደፍተን ሳምናት፤ ዕንባችንም ሳናስበው ፈሰሰ::

ጨጎ ቅዱስ ገብርኤል የተተከለው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሲሆን የአተካከሉም ታሪክ የሚደንቅ ነው:: በዚሁ መስመር አንድ ካህን የቅዱስ




www.eotcmk.org

ገብርኤልን ታቦት ይዘው ሲሄዱ መሸባቸውና ጨጎ አደሩ:: በማግስቱ ለመሔድ ሲነሡ ታቦቱ አላንቀሳቅስ አላቸው:: በዚህ ማረፍን እንደፈለገ ተረዱ፤ በዚያውም ሊተከል ቻለ:: ሕንጻውም እጅግ በአማረ መልኩ ምእመናን እንደሠሩት ታሪኩን የሚያውቁ አባቶች አስረድተውናል። የቀድሞ ፎቶውም ምስክር ነው:: ታቦቱም ስእለት ሰሚ ስለሆነ በርካታ የአጋሮ ክርስቲያኖች ለማስቀደስ ይመጣሉ::

የዚህ ቤተክርስቲያን ተእምር ሰላም የነሳቸው አጽራረ ቤተክርስቲያን የረጅም ጊዜ ሕልማቸውን መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ተግባራዊ አደረጉት:: ፀረ ቤተክርስቲያን የሆኑ አክራሪ ሙስሊሞች እጅግ በሚያሳቅቅ ሁኔታ ቤተክርስቲያኑን ከነ ጽላቱ አቃጠሉት:: እሳቱም ከአንድ ወር በላይ ሳይጠፋ ይነድ እንደነበር የዐይን እማኞች አስረድተውናል:: በግቢው ውስጥ የተቃጠለው ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ ተራራ አኽሎ እንደተከመረ ይታያል::

ከቤተክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ በስተግራ የቀብር ቦታ አለ:: መቃብሩ ዛሬ ሰው ተቀብሮበት ወዲያው በአካባቢው የሚኖሩ ሙስሊሞች ከብት ያሰማሩበት ነበር:: ከዚያም የከብት ገበያ አድርገውት እንደ ነበር ሊቀመዘምራን ብርሃኑ አስረድተውናል:: ቤተክርስቲያኑ ከተቃጠለ በኋላ ግን ብፁዕነታቸው ከክልሉ መንግሥት ጋር ባደረጉት ጥረት የክርስቲያኖቹ የቀብር ቦታ እንዲከበር፤ የከብት ገበያውም ከመቃብሩ ክልል ውጭ እንዲሆን ተደርጓል:: ከቃጠሎው በኋላ በአካባቢው የነበሩ ክርስቲያኖች በደረሰባቸው ጥቃት የሰለሙትም ተመልሰዋል፤ አንዳንዶቹም ቀዬአቸውን ለቀው በአጋሮ የሚኖሩ አሉ:: ስድስት ሕፃናትም ወደ አበልቲ ሄደው በአዳሪነት እየተማሩ ዲያቆናት እንደሆኑ ከሊቀ መዘምራን ገለጻ ተረድተናል::

አሁንም ሰላም የሰፈነ ቢመስልም አንዳንድ ትንኮሳዎች መኖራቸውን በአካባቢው ያገኘናቸው ምእመናን ገልጸውልናል:: በአጥቢያውም ያሉት አባወራዎች ከሃያ የማይበልጡ ናቸው:: መረጋጋት አይታይባቸውም፣ አንዳንዶቹም አስተያየት ለንጠይቃቸው እንኳ ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ነበር የሚናገሩት:: ወደፊትም በዚህ ቦታ የመኖራቸው ሁኔታ እንደማያስተማምን የአሁኑ ዓይነት ጥቃት ላለመከሰቱም ዋስትና እንደሌላቸው፤ ዘወትርም በስጋት እና በጭንቀት እንደሚኖሩ ይገልጻሉ::

በቤተክርስቲያኑ የደረሰውን ጉዳት መቼም ቢሆን የሚከፍለው ነገር አይኖርም:: በሕዝበ ክርስቲያኑም የማይፋቅ ጠባሳ ጥሎ አልፏል:: ታሪክም ሲያስታውሰው ይኖራል::

ከቃጠሎው በኋላ ምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የሆነ መቃረቢያ ቤተክርስቲያን ተሠርቷል:: ለሀገረ ስብከቱ ትልቅ ችግር የሆነው የካህናት እጥረት ቢሆንም ወደ ጨጎ ቅዱስ ገብርኤል ግን ፍፁም ፈቃደኛ ሆኖ የሚሄድ ካህን የለም:: አሁን እያገለገሉ ያሉት ቄስ ጸዳሉና ቄስ ፍስሐ ቀድሞ በመረዋ አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን የሚያገለግሉና ታኅሣሥ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ጽላት ሊያስገቡ ሲሉ ሁለቱን ካህናት ለአንድ ወር ቤተክርስቲያን እንዲያገለግሉ ለጊዜው የተመደቡ ናቸው:: ያውም ያን ጊዜ በሕይወት አንድ ቀን ለማደር አስፈሪ በነበረበት ጊዜ፣ መስዋዕትነትን ከፍለው የተገኙ ናቸው:: ዛሬም ካህናቱ የሚያጽናናቸው የሚረዳቸው ይፈልጋሉ:: ካህናቱ ከዚህ ከለቀቁ ቤተክርስቲያኑ መፈታቱ እንደማይቀር የሁሉም ስጋት ነው::

ካህናቱ ክርስትናቸው፣ ሐዋርያነታቸው አስገድዷቸው እያገለገሉ ነው ያሉት፤ ቀድሞ ዓመቱን ሙሉ ሰዓታት፣ ስብሐተ ነግህና ቅዳሴ አይጎድልበትም ነበር:: አሁን ግን ሁሉ ነገር ነበር ብቻ ሆኖ ቀረ:: ከሁለቱ ቀሳውስት ሌላ አንድ ዲያቆን አለ::

በአሁኑ ወቅት ያለውን ሁኔታ ቄስ ጸዳሉን ስንጠይቃቸው «የሚከፈለን ደመወዝ ዝቅተኛ ነው፤ ኑሮው ከአቅማችን በላይ ነው፤ ምግብ እንኳን ገዝተን እንዳንበላ በአካባቢያችን ያሉት ሁሉም ምግብ ቤቶች የሙስሊም ናቸው:: ገብተን መብላት እንፈራለን:: በረሐብ እየተሰቃየን ነው:: ወደ አጋሮ እንኳን እንዳንሄድ ቤተክርስቲያኑን ለማን ጥለን እንሂድ፤ እዚህ ያሉ አንዳንድ ምእመናንም እኛን ሊያጽናኑ ይቅርና ራሳቸውም የተረጋጉ አይደሉም፤ ሙስሊሞቹም በየጊዜው ይዝቱብናል፤ ማስፈራሪያ ወረቀትም ይበተናል፤ በአጠቃላይ በስጋት ነው ያለነው» በማለት ነበር ዕንባ እየተናነቃቸው ስላለው አጠቃላይ ችግር የገለጹልን::

ቆርቆሮ በቆርቆሮ አዲስ የተሠራችው መቃረቢያ ተዳፋት መሬት ላይ በመሆኗ የጎርፍ ውኃ በቀላሉ ወደ ውስጧ ይገባል:: የዙሪያው የቆርቆሮ አጥር ጎርፍ ሸርሽሮት ችካሉም እየወላለቀ ነው:: በክረምት ምስጡ ጣሪያው ድረስ የሚወጣበት ሁኔታ አለ:: «ኧረ ምስጥ ሊጨርሰን ነው ልጆቼ» አሉ ቄስ ጸዳሉ ዐይናቸው በእንባ እየተሞላ:: በአዲስ አበባ ከተማ ሦስትና አራት ብር የሚያወጣ የምስጥ መድኃኒት ለጨጎ ቅዱስ ገብርኤል አባቶች ውድ ሆነ::

ቤተክርስቲያኑ በአሁኑ ወቅት ለአገልግሎት የሚሆን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ አልባሳት ወዘተ የሉትም::

እኛም ውስጣችን እያዘነ ከቤተክርስቲያኑ ተሰናብተን ልንወጣ ተንደረደርን:: ከመንፈሳውያን ወንድሞቻቸውና ልጆቻቸው መለየቱ አስጨነቃቸው፤ ቄስ ጸዳሉ ግን ክርስቲያን ናፍቋቸው ነበርና ከእሳቸው ጋር ውለን ብናድር ደስተኛ ነበሩ:: ነገር ግን ሌሎችም ተመሳሳይ ዘገባዎች ስላሉን ግቢውን ለቀን ወጣን፤ ተሰናበትናቸውም:: ሹፌራችን መኪናዋን አስነሥቷት ስንሄድ እጃቸውን እያውለበለቡ ከመኪናዋ ኋላ ተከተሉን:: ዕንባችን መጣ፤ መኪናችን ፍጥነቷን ጨመረች፤ ሆዳችን እየባባ ክርስቲያናዊ ወገን የናፈቃቸው ቄስ ጸዳሉን ቆመው እጃቸውን እያውለበለቡ፤ ተለየናቸው:: ጉዞ ወደ በሻሻ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ. . .✦

*ይቆየን::*

# «አብነቱ...»

ከገጽ [illegible] የዞረ

እንዲያመነጭ የሚያስችል አካሄድ መፍጠር (እንደ ቅኔ ትምህርት ቤቶች ባህል)

፭. በተማሪዎቹና በመምህራኑ መካከል በመከባበር ላይ የተመሠረተ በጋራ ዕውቀትን የመመርመር ኅበረትን መመሥረት

፮. በኢትዮጵያ በሁሉም ደረጃዎች በሚገኙ የትምህርት ተቋማት በሚገኙት አብያተ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት መጻሕፍት የአውሮፓና የአሜሪካ ሲሆኑ ከነዚህም ብዙዎች በእርዳታ የተገኙና አካዳሚያዊ አቋማቸው እዚህ ግባ የማይባል ጭምር ነው:: አስደናቂው ነገር ግን ሀገራችን ይህን ያህል የጥንታዊ ትምህርት ባህል ኖሯት ሳለ በየአብያተ መጻሕፍቱ ይህን የሚያሳይ ምንም ነገር አለመገኘቱ ነው::

## ፮. ሌላው ዘመናዊው ትምህርት

ከአብነቱ መውሰድ ያለበት ጉዳይ የመምህርነቱን ብቃት ነው:: በአብነት ት/ቤቶች ለመምህርነት የሚበቁት ትምህርቱን ያጠናቀቁት ሁሉ ሳይሆኑ በዚያ ሙያ ላይ ልዩ ብቃት በማሳየት የተመሰከረላቸው፤ በሥነ ምግባራቸውና ትምህርቱን ለትውልድ ለማስተላለፍም ቃለ መምህሩን በማክበራቸው ጭምር ነው::

ከዚህ በላይ እንዳየነው የአብነት ትምህርት ቤቶች የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት ከዘመናዊ የትምህርት አሰጣጥ የሚበልጥባቸው በርካታ ነገሮች አሉት:: የዘመናዊ አስተዳደርም ከጥንታዊው አስተዳደርና ታሪክ የሚማራቸው በርካታ ነገሮች አሉ:: እነዚህ ነገሮች በጥንቃቄ ማጥናት፣ በፖሊሲዎቻችንና በሥርዓተ ትምህርቶቻችን ውስጥ በአግባቡ ማካተትና ቢያንስ ባህሉን፣ ጥንታዊውን ትምህርትና ሥልጣኔ የሚያከብር ዘመናዊ ሥርዓት ትምህርትና አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ ነው:: ይህንን ከኔ የበለጡት ባለሙያዎች አጥንተውታል፣ ወደፊትም በሚበጀን መንገድ ሆን ብሎ ማስጠናትና ፊታችንን ወደ ራሳችን በማዞር እንደ እስያውያን ጥበብን ከምዕራባውያን ባህልን፣ ሃይማኖትንና ምግባርን ከአባቶቻችን በማለት መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል::

ሌላው ይህን ጥንታዊ የትምህርት ሥርዓት፣ ታሪኩን፣ የሚሰጠውን ትምህርት፣ በዘመናት የነበሩትን ስመ ጥር መምህራን ታሪክ፣ የአብነት ትምህርት ቤቶቹን ታሪክ፣ ... እየጻፉ በየትምህርት ቤቶቹ በትምህርት መልክ እንዲካተቱ

ወደ ፴፰ ገጽ ዞሯል



www.eotcmk.org

## «አብነቱ...»

ከገጽ ፴፯ የዞረ

ማድረግ ያስፈልጋል:: ታላላቅ መምህራን እንደ ትውልድ ሀረግ የመምህራን ሐረግ አላቸው:: ያንን ሐረግ ተከትሎ ታሪካቸውን፣ ልዩ ችሎታቸውን፣ የትምህርት አሰጣጣቸውን፣ ሥራዎቻቸውን፣ ወዘተ. የያዙ ታሪኮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ይህ ሥራ ምናልባት በመልክአ ምድር ሊወሰን ቢችልም ያጋሩ በሆኑት ነገሮች ላይ ማስተማር ጠቃሚ ነው:: እንኳን የሀገራችንን የሌሎች ሀገራትን ታሪክ፣ የትምህርት ሥርዓት፣... ሁሉ የሚያካትቱ ትምህርቶች እየሰጠን ነውና ብዙም የሚያስፈራ አይመስለኝም::

የአብነት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት፣ የሚያስመርቋቸው ተማሪዎች ሊይዟቸው የሚገቡ ሙያዎች፣ ሊሠሯቸው የሚችሏቸው ነገሮች እና የሚሰለፉባቸው የሥራ መስኮችን ዘርዝሮ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ይህን ተግባር በተሳካ ሁኔታ እንዴት ሲያከናውኑ እንደነበር መመርመርና ዘመናዊውን ሥርዓተ ትምህርት በዚያ ልምድ ላይ መመሥረት ያሻል::

በራስ ቋንቋ የማስተማርን አስፈላጊነትም ያሳያል፤ ይኸው ሥርዓተ ትምህርት በእስያ ሀገሮች እንደተደረገው እና በጥንታዊውም ትምህርታችን እንዳየነው ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ በቋንቋችን መስጠት አለበት:: በየትኞቹ ቋንቋዎች ለሚለው በሂደት ከአንድ ቋንቋ ጀምሮ ከፍተኛ ተናጋሪ ባላቸው ቋንቋዎች መስጠት ያስፈልጋል:: በኢትዮጵያ ሥልጣኔን ለማየት ይህ ግዴታ ነገር ነው:: ጥንታዊው ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋው ትምህርቱት በግእዝ በመስጠቱም ጭምር ነው፤ በዓረብኛ ወይ በግሪክ ወይ በላቲን ሆኖ ቢሆን ይህን ደረጃ አያገኘውም ነበር ለማለት ይቻላል:: በሀገራችንም እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በአማርኛ ቋንቋ ጀምሮ በኦሮምኛና በትግሪኛ መስጠት እስካልተጀመረ ድረስ በእንግሊዝኛ በማስተማር የትም መድረስ አንችልም::

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የሥነ ጽሑፍ ት/ቤት፣ የሥነ ጥበብ ት/ቤቶች፣ የሙዚቃ ት/ቤቶች፣ የታሪክና የፍልስፍና ተቋማት በጥንካሬ እነዚህን ሀብቶች መርምረው የማጥናት በዘመናዊ ሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥም የማካተትና በጥንታዊ ሀብቶቻችን በመጠቀም ወደ ፊት የመራመድ ሓላፊነቶች አሉባቸው::♦

## «ሁሉም ዜማ...»

ከገጽ ፴፬ የዞረ

የሚያዩበት ሁኔታ ሊመቻች ያስፈልጋል:: ይህ ከሌለ ግን ሕዝቡን መያዝ አልቻልንም ማለት ነው::

ሕዝቡ ምን ዓይነት መዝሙር ይፈልጋል ተብሎ ዜማ መዘጋጀት የለበትም:: ቅዳሴ የምናስቀድሰው ሕዝቡን አስተምረነው ነው? ስለዚህ ሕዝቡ ምን ይፈልጋል ብሎ ማለት ሳይሆን አባቶች ያቆዩትን ሥርዓተ ዜማ እንዲያውቀው ማስተማር ነው ያለብን:: አሁን ያለውን መዘበራረቅ ያመጣው የንግድ ችግር ነው:: አንድ ጊዜ ሁለት መዝሙር ቤቶች «እባክህ ወደ ዘፈን ቀረብ የሚል አድርገህ ቸብቸቦ ሥራልን» ያሉኝ አሉ:: እኔ በቤተክርስቲያን ያደኩበት ሕይወት ይሄ አይደለም:: የማዘጋጀው የጥንቱን ሥርዓት ጠብቄ ነው እናም መዝሙር ቤቱን አልችልም ብዬ ነው የመለስኩት::

ስለዚህ ይህን ለመጠበቅ ጠቅላይ ቤተክህነት ትልቅ ሓላፊነት አለበት:: ለችግሩ መባባስ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረከተው ቤተክህነቱ ነው:: ቤተክርስቲያን ሕዝቡን የማዘዝ፣ የማስተማር፣ የማገድ መብት እያላት አልተጠቀመችበትም:: በየአጥቢያው ያሉ ሰበካ ጉባኤያት፣ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ትኩረት ሊሰጡት ይገባል::

ያሬዳዊ መዝሙር ቢታወቅ፣ ቢለመድ ጥሩ ነው:: መዘምራኑ ይህን ለማወቅ ብለው ጥናት ውስጥ ይገባሉ፤ ዜማ ውዳሴ ማርያም ሲጮኹ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን ሰውም ይሆናሉ::

*ሐመር፦ ዘማርያኑ ግጥምና ዜማውን ለሊቃውንት አሳይተናል ይላሉ፤ ከሙያዎ አንጻር ሲያዩት ዜማዎቹ በሊቃውንት የተተቹ ይመስላሉ?*

መ/ር በየነ፦ እኔ የተተቹ አይመስለኝም:: ሳዳምጣቸው ጉድለቶችን በግልጽ ታያለህ፤ ግእዙን ሲናገሩ በንግግራቸው ታውቃቸዋለህ:: አንድ ሰው የቤተክርስቲያን ትምህርት እንዳለው እንደሌለው በንግግሩ ይታወቃል የግጥሙ አጣጣል፣ አወራወር ያስታውቃል:: በአብዛኛው የሚጠቀሟቸው ተራ ግጥሞች በሳድስ በሚያልቁ በቀላል ቃላት የተሠሩ መሆናቸው በራሱ ደረጃቸውን ያሳያል::

*ሐመር፦ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?*

መ/ር በየነ፦ እኔ ባለኝ ዕውቀት ማንኛውም ሰው መዝሙር ካሴት ለማውጣት ያሰበ መጥቶ ቢያናግረኝ፤ ልረዳውና ምክር ልሰጠው እችላለሁ:: በተቻለ መጠን ሁላችንም ወደ ያሬዳዊ ዜማ ብናዘነብል ጥሩ ነው::♦

## «የተጮኸ ሁሉ ...»

ከገጽ ፴፬ የዞረ

ተምረው፣ አስመስለው ቢደርሱ አንድ መፍትሔ ነው::

ዜማ የሚማሩ ሰዎች ያሬድን ተምረው የያሬድን አስመስለው ለመድረስ እንዲችሉ ሥራዎቻቸውን ለሊቃውንት ቢያሳዩ፤ ዜማውም በዜማ ሰዎች ቢታይ ጥሩ ነው:: በዜማ ሁሉም ሊቃውንት አንድ ሳይሆኑ ይችላሉ:: እኔ ከሌላው ላንስ ወይም ልሻል እችላለሁ፤ መማሩ ግን ዋነኛ መፍትሔ ነው::

*ሐመር፦ ዜማ የኃጢአትና የጽድቅ ጉዳይ ሊሆን አይችልም የሚሉ አሉ፤ እርስዎ ምን ይላሉ?*

መ/ር ሐዲስ፦ ዜማ ስንል መጀመሪያ ከመልእክቱ ጋር ካልመጣ ዜማ ልንለው አንችልም:: ጩኸት ነው የሚሆነው:: ጩኸት ደግሞ እዚህ ግባ የማይባል ነው:: ስለዚህ ዜማ እግዚአብሔርን የሚያመሰግን፣ መልእክት ያለው መሆን አለበት:: ንባብም እኮ ዜማ አለው፤ መልእክቱ ከዜማ ጋር አንድ ሆኖ ነው ዜማ የሚባለው:: በመልእክቱ ስሕተትን ልንሠራ እንችላለን::

መልእክቱስ ምንድን ነው? ማነው የደረሰው? ብለን መለየት አለብን:: በዜማም በኩል በጣም ደስ የሚያሰኝ ነፍስን የሚያስገዛ ዜማ እንዳለ ሁሉ ለሥጋ ፈቃድ አሳልፎ የሚሰጥ ዜማ አለ:: እንዲህ ዓይነቱ ደግሞ ዘፈን ነው:: ዘፈን ደግሞ ኃጢአት ነው::

*ሐመር፦ በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?*

መ/ር ሐዲስ፦ የያሬድን ዜማ ለማወቅ መጽሐፎቹን በደንብ ማጥናት ያስፈልጋል:: ዜማ ሲደርሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸው ግንኙነት ቢታይ፣ መልእክታቸው መንፈሳዊነታቸው ቢመዘን ጥሩ ነው:: ለምሳሌ መንገድን ብናይ ሁሉም ሰው ኃጥኡም፣ ጻድቁም በአንዱ መንገድ ይሔዳሉ:: በአንድ መንገድ ስለሔዱ አንድ አይደሉም:: ስለዚህ እኛ ማድረግ ያለብን መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን መለየት ነው:: ወጣቶቹም የያሬድን ዜማ በትንሽ በትንሹም ቢሆን ምልክቶቹን ማጥናት አለባቸው:: የሚደርሱትን መዝሙርም የያሬድን ሳይዙ የያሬድ ነው ማለት ቢቀር፤ ሌላ ከሆነ ሌላ ደራሲ አለው ቢባል ጥሩ ነው::

የተደረሰውን ነገር ለመለካት የሚፈልግ ደግሞ የዜማ ሰው መሆን አለበት:: የተጮኸ ሁሉ የያሬድ ዜማ አይደለም፤ የያሬድ ዜማ ሃይማኖታዊ መልእክቱንና ድምፁን አስተባብሮ የያዘ ከመጽሐፍ የተወሰደ ወይም በያሬድ የዜማ መሥፈርቶች ሊለካ የሚችል መሆን አለበት::♦



www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን *«አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት»* የተሰኘ ዓምድ ከ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል። በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በተቋቋመው *«የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር»* የሚዘጋጅ ነው። ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው።

*መ/ር ደሴ ቀለብ*

# በ ግ እ ዝ   እ ን ነ ጋ ገ ር




| ሐምለሰት | ደራርቱ |
|---|---|
| ሰላም ለኪ ደራርቱ<br>ሰላመ ላንቺ ይሁን ደራርቱ | ወሰላም ለኪ ሐምለሰት<br>ላንቺም ሰላም ሐምለሰት |
| አይቴ ውእቱ ፍኖት?<br>መንገድ ወዴት ነው? | ኀበ አዋሳ ወ አርባ ምንጭ<br>ወደ አዋሳ እና አርባ ምንጭ |
| ምንተ ትገብሪ ህየ<br>በዚያ ምን ታደርጊያለሽ | አነ አሐውር ኀበ ብርብር ማርያም<br>ወደ ብርብር ማርያም እሔዳለሁ |
| መኑ ይእቲ ዘነበረት ምስሌኪ?<br>ከአንቺ ጋር የተቀመጠችው ማን ናት | አበበች ይእቲ<br>አበበች ናት |
| እም አይቴ ይእቲ?<br>ከየት ናት | እም ዝዋይ<br>ከዝዋይ |
| እኅትኪኑ ይእቲ<br>እኅትሽ ናት | እዎ ይእቲ መንፈሳዊት እኅትየ<br>አዎ መንፈሳዊት እኅቴ ናት |
| ትመስለኪ<br>ትመስልሻለች | ንስቲት ንስቲት<br>ትንሽ ትንሽ |
| ምንት ውእቱ ክፍለ ትምህርታ?<br>የትምህርት ክፍሏ ምንድን ነው? | ሥነ ሕይወት ውእቱ<br>ሥነ ሕይወት/ባዮሎጂ/ ነው |
| ውስተ አራት ኪሎኑ?<br>በአራት ኪሎ ነውን | እዎ<br>አዎ |
| እፎኑ ሕይወት?<br>ሕይወት እንዴት ነው | ሠናይ ውእቱ<br>ጥሩ ነው |
| ሠናይ ሚጠት እም አርባ ምንጭ<br>መልካም መልስ ከአርባ ምንጭ | ወለኪ እም ወለጋ<br>ላንቺም ከወለጋ |
| ማእዜ ውእቱ ተባርኮ?<br>ምረቃ መቼ ነው? | በነሐሴ ውእቱ<br>በነሐሴ ነው |

## «. . . እርስ በእርሳችሁ...»

ከገጽ ፴፪ የዞረ

ትእዛዛቴንም ብትጠብቁ ብታደርጉትም ዝናባችሁን በወቅቱ አዘንባለሁ ምድሪቱም እህልዋን ትሰጣለች. . .» ይለናል። /ዘሌ.፳፮፥፫/ ስለዚህ የዝናሙ በወቅቱ ያለመዝነም ችግር የእኛው እንጂ የማን ሊሆን ይችላል?

ሰው በሰው ላይ ሲጨክን እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ ይጨክንበታል፤ ያለንን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ተስማምተንና ተፋቅረን በመተሳሰብ ከመጠቀም ይልቅ እርስ በእርሳችን በመጨካከን መበላላት ከጀመርን እግዚአብሔርን እሺ አላልነውምና ዝናማችንን በወቅቱ አይሰጠንም። ስለዚህ ለኑሮ ውድነቱ መከሰቻ ምክንያትና መፍትሔው የእኛ እግዚአብሔርን እሺ ማለት ጉልህ ሚና አለው።

መቼም ሻጭና ገዢን በገንዘባቸው ገብቶ ማዘዝን ማንኛውም አካል አይሞክረውም፤ የገበያ ነጻነትን ገና ያኔ ጥንት ፍትሐ ነገሥቱ «ሻጭና ገዢ በገንዘባቸው ሥልጣን ያላቸው ካልሆኑ በቀር መገበያየት እውነተኛ አትሆንም» ሲል ይገልጸዋል /ፍት.ነገ. አንቀጽ.፴፫፥፪፻፱/። ይሁን እንጂ ወቅቱ በፈጠረው ሁኔታ ውስጥ እኛ ክርስቲያኖች ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች አሉን።

*ነጋዴ ከሆንን፦* እግዚአብሔርን ስናገለግል ሁሌም በታማኝነት በመሆን ነው። የትም እንሁን የት ማንም እንሁን ማን ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን ከፊት ማስቀደም አለብን። እግዚአብሔር ፍጥረቱን እንድናገለግል በተለያየ ቦታ ያስማራናል። ነጋዴ ማለት በሸማቹ ላይ የተሾመ መጋቢ ማለት ነው። ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል።«. . እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው እውነት እውነት እላችኋለሁ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል» /ሉቃ.፲፪፥፵፪/። የነጋዴዎች ሁሉ ፈተና ውሸት እንደሆነ በሐመር ፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፱ ላይ አንዳንድ ነጋዴዎቹ ጠቁመው ምክንያታቸውም እከስራለሁ፣ ከውድድር እወጣለሁ የሚል ፍርሃት እንደሆነና መፍትሔውም በእግዚአብሔር ማመን እንደሆነ ራሳቸው ነጋዴዎች ጠቅሰውታል። /ማቴ.፳፥፳፯/ ስለዚህ ሁሉም ነጋዴዎች ሲሆን እግዚአብሔርን ፈርተው ካልሆነም በሰብአዊ ርህራሄ በወገናቸው ላይ የሚጨክነውንና በአንዴ ልክበር

ወደ ገጽ ፵ የዞረል




'

www.eotcmk.org

## ጦማረ ወልደ ማርያም እም ባሌ

*ለአበበ ዘዐራት ኪሎ*

ሰላም ለከ አበበ እኁየ:: አነ ጸሐፍኩ ለከ ዘንተ ጦማረ ለካልአይ ጊዜ:: ለምንትኑ አንተ ዘኢትጽሕፍ ሊተ:: ፍርሀት /ቴንሺን/ አኀዘከኑ? ማዕዜ ውእቱ ፈተናከ? ንሕነ ፈጸምነ ፈተናነ:: ናሁ ዕረፍት ውእቱ:: ሕይወትሰ ዳኀናኑ? እም ውእቱ ጉባዔክሙ መንፈሳዊት:: ሰማዕነ በከመ ሀሎ አሐዱ መነኮስ ማዕከሌክሙ:: ወብዙኃን ዲያቆናት ዘኮኑ አርድዕተ ግእዝ:: በኌንተዝ ይመስለኒ ሕይወትክሙ ዘኮነ ሠናየ:: አቤ! ማዕዜ ውእቱ ተባርኮ አነ እመጽእ ኀቤከ::

እስኩ ጸሐፍ ሊተ:: አው ንግረኒ ሊተ በምኅላፈ ቃል:: ፈኑ ሊተ መጻሕፍተ ቅዱሳተ፣ ወአነ እፌኑ ለከ ዘሀለው ምስሌየ:: አቤ እፎ ውእቱ ማኅበርነ? ኢንኀድግ ማኅበረነ::

እስከ እመጽእ ኀቤከ ይኩን ጸሎትከ ምስሌየ::

## ኀበ ቤተ ሰብእ /ሰብአ ቤት/ ዘግእዝ

ሰላም ለከ አቡየ፣ ሰላም ለኪ እምየ፣ ወሰላም ለክሙ አኃውየ፣ ወሰላም ለክን አኃትየ እንቋዕ አብጽሐክሙ ለ፳፻ ዘመነ ክረምት እፎ ውእቱ? ማእዜ ትመጽኢ እምየ ኀቤየ:: አንሰ ኀሠሥኩ ምክረኪ እስመ ይብል መጽሐፍ ብእሲ ዘአልቦ ተግሣጽ ይትሜሰል ከመ ሥጋ ዘአልቦቱ ነፍስ:: ጾመ ፍልሰታ እፎ ይእቲ? አአምር አንሰ ከመ ተሐውሩ ለቅዳሴ ኀበ መካነ ብርሃን ሥላሴ:: ወአይቴ ተሐውር እኁየ ጌትነት በዝንቱ ዕረፍትከ/ እስመ ዕረፍትሰ ሠናይ ለኩሉ::

ምንተ ትገብሪ እኅትየ ገነት በሐዲስ ዓመት:: አንሰ በፈቃደ እግዚአብሔር እከውን ዲያቆነ:: ወይመስለኒ ዘእከውን ሐዋርያ ግእዝ ወ እምነ ቤተክርስቲያን:: ናሁ ወጠንኩ ተምህሮ ልሳነ ግእዝ ውስተ ማኅበረ ቅዱሳን በማዕከለ ሐዲስ ጽጌ::

*ዮሐንስ*

*እም ሐዲስ ጽጌ/ከአዲስ አበባ/*




**ሐመረ ተዋሕዶ ዘ፳፻ እየደረሰ ነው!**

- የምንኖርባትን ዓለም ከሁለት አቅጣጫ መረዳት ይፈልጋሉ?
- ዓለማዊነትና ሉላዊነት ምን ይዘው እየመጡ ይሆን?
- አክራሪ እስልምናውስ?
- ለአልነጃሺና ለሌሎች የአክራሪዎች ጥያቄዎች መልስ ይሻሉ?

እንግዲያውስ ሐመረ ተዋሕዶ ዘ፳፻ ምእትን ያንብቡ፣ መልሱን ያገኛሉ::


## «... እርስ በእርሳችሁ...»

ከገጽ ፴፱ የዞረ

የሚለውን ልቡናቸውን ሊያራሩትና በሃቅ ስለሃቅ ሊሠሩ ይገባል:: በዚህ ዓለም የሚያስፈልገን እኮ ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው:: ስለምንስ በብዙ እንጨነቃለን? እግዚአብሔር ሲመዝነን «ብዙ ያከማቸ አላተረፈም ጥቂትም ያከማቸ አላጎደለም» ብሎ ነው /፪ቆሮ.፰፥፲፭/::

*ሽማቾችም ከሆን፦* በዚህ ዘመን ትልቁ ነገር ልንለምነውና ልንሳሳለት የሚገባው ጉዳይ ጤና ብቻ ነው:: ከዚያም ሰፋና ዘና ብለን መኖርን ለራሳችን ካስለመድን ሰብሰብ ብሎ በጥበብ መኖርን እንጀምር ቅዱስ መጽሐፍ «በመጠን ኑሩ...» ይላልና /፩ኛጴጥ.፭፥፰/:: ሌላው ሁልጊዜ እንዴት እንሆን ይሆን? እያሉ ከመጨነቅና ከመጠበብ ይልቅ አቅማችን የፈቀደልንን ሁሉ እየሠራን ባለን እናመስግን:: ሰማይ ይወድቃል ብሎ ባላ መትከልን የመሰለ ጭንቀት ውስጥ አንግባ::

በወርም ይሁን በቀንና በሳምንት እጃችን ላይ የሚገባውን የጉልበታችንና የአዕምሮአችን ውጤት የሆነውን ንዋይ እግዚአብሔርን አመስግነን ከመጠቀም ይልቅ «አሁን ይህቺን ገንዘብ በዚህ የኑሮ ውድነት እንዴት አደርጋታለሁ?» እያልን በሐሳብ ፍላጻ ልባችንን አንበሳሳው:: በኤልሳዕ ዘመን እንዲህ ሆኖ ነበር «አንድ ሰው... የበኩራቱን እንጀራ ሃያ የገብስ እንጀራ የእህልም እሸት በአቁማዳ ይዞ ወደ እግዚአበሔር ሰው መጣ:: እርሱም /የእግዚአብሔር ሰው/ ይበሉ ዘንድ ለሕዝቡ ስጣቸው አለ:: ሎሌውም ይህን እንዴት አድርጌ ለመቶ ሰው እሰጣለሁ? አለ:: የእግዚአብሔር ሰውም ይበላሉ፣ ያተርፋሉም ብሎ እግዚአብሔር ተናግሯልና ለሕዝቡ ስጣቸው አለ:: እንዲሁም በፊታቸው አኖረው፣ እንደ እግዚአብሔርም ቃል በሉ አተረፉም»:: /፪ነገሥ.፬፥፵፪-፵፬/

እግዚአብሔር እኮ ጥቂቱን ብዙ፣ መራራውን ጣፋጭ ማድረግ ይችልበታል:: ስለዚህ እግዚአብሔርን በኑሮአችን ሁሉ ከፊት እናስቀድመው በዚህ ወቅት በተለይ መምህራኑ ወንጌል ነን ከምንል ሁሉ ብዙ ይጠበቃል:: ከፊታችን የተከሰተውን ችግርና ከዚህም የከፋ እንኳ ቢመጣ አስቀድመን ችግሮችን እኛው መቅረፍ፣ ችግሮች ከመከሰታቸውም በፊት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣ ስለ አብሮ መብላትና አብሮ መኖር ስለመተሳሰብና መተዛዘን አብዝተን ልንሰብክና የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ልናጽናናው ይገባናል:: እስራኤልን በበረሐ የመገበ በዮሴፍ ምክንያት ግብጽን በበረከት ያትረፈረፈ ረዳኤ ምንዱባን ልዑል እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያን ከረሀብና ከችግር ያትርጠፍልን፣ ሁላችንንም በበረከት ይጎብኝን፣ የምንሠራውን ሁሉ ይባርክልን፣ አሜን::



www.eotcmk.org

# « መሥዋዕቱስ ያርጋል ! »

አዲስ አበባ የዘንድሮ ክረምቷ ጧት ጧት ብቻ ይመስላል:: ብርዱም፣ ዝናቡም ሰውነቴን አፍዝዞታል:: መንገድ የለመደው እግሬ አላስቆም አለኝና ከጧቱ ካፊያ በዝናብ መከላከያ ጃኬቴ ተጠልዬ ዘርይሁን ሕንፃ ደረስኩ:: ከሕንፃው ፊት ለፊት ፊታቸውን ወደ መስቀል አደባባይ አዙረው ወደሚጠሩ ታክሲዎች ተሻገርኩና አንደኛው ላይ ገባሁ:: «መሥዋዕቱ አያርግም!» ሲል በጩኸት ድንገት ከዕንቅልፉ እንደነቃ ሰው ከሚያንቀጠቅጠኝ ብርድ ተላቅቄ ዘወር አልኩ:: ሁለት ወጣቶች ናቸው፤ ይከራከራሉ:: ከክፍለ ሀገር ሲጓዙ አድረው የመጡ እንጂ ጧት ላይ ታክሲ ውስጥ የተገናኙ አይመስሉም:: ሞቅ አድርገው ይከራከራሉ:: ታክሲው እስኪሞላለት ትንሽ ከታገሠ በኋላ መንቀሳቀስ ጀመረ:: በቀጠሮ የተገናኙ ይመስል ከእነርሱ በኋላ የተቀመጡትም ጉዳዩን ተቀላቀሉብትና ያው የተለመደው የእኛ ቤት ችግር ይወራ ጀመር::

«ሰው ታምሞ ለመናዘዝ ገንዘብ ከተጠየቀ ይህ ምኑን አገልግሎት ሆነ? ሰውየው ጸሎተኛና ባሕታዊ መስለው እናቶችን እያታለሉ ገንዘብ ሲሰበስቡ መኖራቸው የገባኝ አሁን ነው:: ...» ይላል:: ጠይም ፊቱን ክስክስ አድርጎ የሚናገርላቸውን ሰው የሚያያቸው ይመስል ዓይኑን አፍጥጧል:: «መጀመሪያ ተረጋጋ! እንኳን ቤተ ክርስቲያን ያሉትን አባቶች ቀርቶ እኔንም እንደዚህ መናገር አትችልም! ...» እያለ ጓደኛው ይመልስለታል:: «እኔም እንዳንተ ነበርኩ! ይህን ብታይ አንተ የበለጠ ልትናገር ትችላለህ!» መልሶ ያፈጥበታል::

በመሐል ገባሁና «ምን ሆንህ ወንድሜ? ምን ገጠመህ? አልኩት:: «ይስሙኝ ጌታዬ» አለ እየተነፈሰ::

አንድ ጓደኛዬ በጭንቅ ታመመ:: እናቱ ደሀ ናቸው፤ ቢሆንም በሚችሉት መጠን አሳከሙት:: አልድን ሲልና ሕመሙ እየባሰበት ሲሔድ ለእናቱ:- 'አንድ አባት ጥሪልኝ፤ ሳልሞት ንስሐ ልግባ' ይላቸዋል:: እናቱም አጥቢያቸው ሔደው በቅርብ ጊዜ የመጡትንና እንደ ባሕታዊ የሚታዩትን አንድ አባት ይዘውለት መጡ:: እርሳቸውም መጥተው ካነጋገሩትና ኑዛዜውን ካደመጡ በኋላ «ለገጠር ቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ አንድ ሺሕ ብር መክፈል አለብህ» አሉት:: እርሱም ደነገጠና ከእናቴ ጋር ይነጋገሩ አላቸው:: ለእናቱም ይህንኑ ነገሯቸው:: እናቱም መምሩ ቀን ይስጡኝ እከፍላለሁ:: ብቻ ልጄ ይዳንልኝ ይላሉ:: ነገር ግን ልጁ በቅርብ ቀን ዐረፈ:: ሰውየው ግን ከዚህም በኋላ እየተመላለሱ ብሩን አምጡ ማለትን ያዙ:: እናቲቱ ደሀ ናቸው:: ልጃቸው ሞቷል:: በሞቱ ጊዜም የተለያዩ ወጭዎችን አውጥተዋል:: ታዲያ ሴትዮዪቱ ትሑትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው በመሆናቸው «እባክዎትን ይቀንሱልኝ? ትንሽ ቀንም ይስጡኝ! ሠርቼ እከፍላለሁ!» ቢሉም ሰውየው ግን ፍንክች አልልም አሉ:: እንደምንም ተለምነው ትንሽ ብር ቢቀንሱም ወዲያው ካላመጣችሁ አሉ:: ታዲያ የእነዚህ ጸሎት ያርጋል? ንገረኝ! አሁንም ይበሳጫል:: ስማ ይህን አታድንቅ! ልንገርህ እኔ .... ከኋላ የተቀመጠው ጐልማሳ ነው:: አማቾቹን ይዞ የሚጦር ጓደኛችን አማቱ ዐረፉበት:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔዶ ጸሎተ ፍትሐት አድርገው እንዲቀብሩለት ሲጠይቅ ስንት እንደጠየቁት ታውቃለህ? 10,000 ብር:: ሁሉም ተደናገጠ:: የት ነው? ምን ያደርግልሃል እርሱ፤ ብቻ እዚሁ አዲስ አበባ ያለ የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ይመልስለታል:: «አይ! እኔ ሰፈር አራት ኪሎ አካባቢ ነው:: ታዲያ አጥቢያዎቹ ለፍትሐት የሚያስከፍሉት እንዲህ ያለ ክፍያ የለም:: የታወቀ የአገልግሎት ክፍያ አለ:: እርሱን በሥርዓቱ መሠረት ወደ ሰበካ ጉባኤው ሒሳብ ክፍል ሔደህ ትከፍላለህ::» ረጋ ብሎ ማስረዳቱን ቀጠለ:: «ስለዚህ የጠየቀው ሰው ቤተ ክርስቲያን ተጠግቶ የሚኖር አንዱ ወንበዴ ይሆናል እንጂ መቼም ሓላፊነት የሚሰማው እውነተኛ ካህን ሊሆን አይችልም::

«ስማ ሰውዬ! የገንዘብ ፍቅር አሁን ስተት ብሎ የገባው እነርሱ ጋር ነው! መሐል ከተማ ያሉት እንዳልከው ጥሩ አሠራርና የተረዱ ሰዎችም ሊኖራቸው ይችል ይሆናል:: ግን ወረድ ብለህ ከካዛንችስ ጀምሮ ብዙ ነገር ልትሰማ ትችላለህ:: ለምሳሌ በእኔ አጥቢያ የተደረገውን ልንገርህ:: ወንድሜ የሰበካ ጉባኤው አባል ነው:: ታዲያ በንግሥ ቀን ብዙ ሕዝብ ስለሚሰበሰብ ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚገባ ይጠበቃል:: ኰሚቴው ተሰብስቦ ሙዳየ ምጽዋቱ ሲከፈትና ሲቆጠር ግን አንድ ሁለቱ ሙዳዮች ብቻ ሞልተው ሌሎቹ ሁልጊዜም ጎደሎ ናቸው:: ይህ ነገር አብዝቶ ሲደጋገም ጊዜ አንድ ቀን አንድ ብልህ ሰው አንድ ብልሃት ያመጣል:: ለማንም ሳይነግሩ የሙዳዮቹን ታችኛውን ክፍል (በሥር በኩል) በቢጫ ቀለም ምልክት ያደርጉበታል:: ከዚያ በኋላ የመክፈቻው ዕለት የተሰበሰቡትን ሙዳዮች ሲያዩ ከዓሥሩ ውስጥ ሰባቱ ምልክታቸው የለም:: ሲከፈት ምልክታቸው ያለው የሦስቱ ሞልቶ ሲገኝ የሰባቱ ጐደሎ ሆነ:: በዚህ ጊዜ ሙዳዮቹ እንደሚለወጡ አረጋገጡ:: ከዚህ በኋላ በሚቀጥለው ለፖሊስ ጉዳዩን አስረድተው ሌላ ምልክት አደረጉ:: በዚህ መሠረት ፖሊስ እጅ ተፍንጅ ሌቦቹን ያዘ:: ...» እነማን ነበሩ? ልጃቸው ስለሞተባቸው ሴትዮ የተረከልን ነበር አፍጥጦ የጠየቀው:: «ምን ያደርግልሃል?» «ታዲያ አሁን የእነርሱ ጸሎትና መሥዋዕት አርጎ አገር ይጠበቅበታል? ...» ያወራል ያለማቋረጥ:: ከዚያ ስለአራት ኪሎ አድባራት አገልግሎት በመናገር ይከራከር የነበረው ሰው እንደገና ተመልሶ ወደ ውይይቱ ገባ::

«በነገራችን ላይ የገንዘብ ጉዳይ ሊያስጨንቃችሁ አይገባም::» ገና መናገር እንደ ጀመረ ከአፉ ነጠቀውና «ታዲያ ምንድን ነው የሚያስጨንቅህ?» አለው::

ተረጋግቶ «እኔ ለማለት የፈለግሁት ገንዘብ አያስፈልግም ወይም ድርጊቱ ምንም ማለት አይደለም ማለቴ አይደለም:: ነገር ግን ከሁለት አቅጣጫ ብታዩት አትረበሹም:: ወደአልሆነ ድምዳሜ ከመድረስም ያድናችኋል::»

«እሺ እኮ አስረዳን!» ወጣቱ አሁንም ንዴቱ አልበረደለትም:: «የመጀመሪያው የእኔ የግሌ አስተሳሰብ ነው:: በግሌ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በደንብ ጥቅም ላይ የማይውልበት አጋጣሚ እንዳለ ስሰማ ባዝንም ስርቆቱና ዝርፊያውን ግን በሌላ አቅጣጫ ለመመልከት ችያለሁ:: ለዚህ የበቃሁት ደግሞ አንድ አባት ባስተማሩኝ ትምህርት ነው:: በአንድ ወቅት እዚሁ አዲስ አበባ የሰማሁትን የገንዘብ መዘረፍ ነገርኳቸውና <እግዚአብሔርስ ለምን ዝም አለ?> ስል ጠየኳቸው:: እርሳቸውም እያዘኑ <አይ ልጄ እግዚአብሔር እኮ ተሰርቆም፣ ተቀምቶም፣ ተጭበርብሮም በመጣ ገንዘብ አይደሰትም:: ስለዚህ ዘራፊ ያዘዘበት አለመደሰቱን ለመግለጽና ገንዘቡም መሥዋዕት ሆኖ መቅረቡን ስለተጸየፈው ይሆናል:: ዳግመኛም ልጄ አትቸኩል:: የእግዚአብሔርን ትዕግሥት በሰው አሠራር አትመዝን:: የይሁዳን ታሪክ አታውቅም? ይሁዳ እኮ የሚሰርቀው ዓሥራቱን በኩራቱን ነበር:: እርሱንም ቢሆን ጌታ ይታገሣል:: ሰጭዎቹ ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት ብለው የሰጡት ገንዘብ በመሰረቁ ጽድቃቸው አይቀርባቸውም:: ሌቦቹን ግን እንደማያውቅ ሆኖ የሚታገሳቸው እንደ ይሁዳ ራሳቸው ወጥተው እንደሚወድቁ ስለሚያውቅና በፍርድም ጊዜ «ተገፋን» እንኳ ብለው ምክንያት እንዳያቀርቡ ነው...» በማለት ብዙ ትምህርት ከሰጡኝ ወዲህ ተሰረቀ፣ ተዘረፈ፣ ...> ስሰማ ብዙ አልደነግጥም:: ስሰማው ባፍርም ጉዳዩን የሚታገስበት የእግዚአብሔር ዓላማ ስላለው አልናወጽም::

ሌላው ግን እንደ ክርስቲያንነታችን ስናየው አሁን አሁን እያየነው ያለነውን መመርመር አለብን:: ለምሳሌ አንተ ወንድሜ ቅድም ያነሣሃቸው ለኑዛዜ ብዙ ብር የጠየቁት፣ ለፍትሐት ብዙ ሺሕ ብር የተቀበሉት፣ ... የመሳሰሉ እንዳላችሁት አሉ፤ ይኖራሉም:: ነገር ግን እዚያ አጥቢያ ከእርሳቸው ውጭ ያሉት ሌሎቹን ንጹሐን አገልጋዮች መዘንጋት የለብንም:: ስለዚህ እያየን ያለነው ብዙዎቹን ደኅናዎች ሳይሆን ጥቂቶቹን አጭበርባሪዎች ይመስለኛል:: በአንድ ወቅት እኔን የገጠመኝ መነኩሴ መሳይ ሰው ማስረጃ ይሆነኛል:: ሰውየውን ያየሁት በሕማማት ነው:: ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሆኖ ለስግደት የሚመጡትን ሁሉ መስቀል ሳሳልም ይላል:: አንዳንዶቹ ቢሳለሙም አንዳንዶቹ ግን የጐሪጥ እያዩት ያልፋሉ:: እንግዲህ ተመልከቱ ይህ ሰው ቆቡን ደፍቶ፣ ቀሚስ አድርጎ፣ መስቀል ይዞ የመጣው እንደተለመደው ሊያጭበረብር ነው፤ ነገር ግን በሕማማት መስቀል እንደማይሳለም እንኳ አላጠናም ነበር ማለት ነው፤ ...» ማስረዳቱ ሳይጨረስ አቋረጡት::

«እሺ! እንዳልከው ይሁን! ታዲያ የሰበካ ጉባኤው ዘረፋስ ምንድን ነው? እነርሱስ የውሸት ናቸው ልትለኝ ነው? ...» ወጣቱ እስካሁን ንዴቱ ገና አልበረደም:: እርሱንማ ነግሬሃለሁ:: ይሁዳዎችም አይጠፉም፤ አብዛኛው ገንዘብ ግን እኒያ አባት እንዳሉት በሥርቆት እንደ መጣው በስርቆት ይሔዳል ማለት ነው:: ስለዚህ በአንዱ በይሁዳ ዐሥራ አንዱ ሐዋርያት እንደማይወቀሱት በእነዚህ በጥቂቶቹ ምግባረ ብልሹዎችም ብዙዎቹን አትውቀሱ» ብሎን አስተዋዩ ወጣት ወረደ::

እውነት ለመናገር የምእመናኑ አስተያየት አስገርሞኛል:: ክርክሩም ጣፍጦኛል:: ባልናገረውም እኔም አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነበር:: «ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ <ተሰርቆና ተዘርፎ የመጣን ገንዘብ በእሳት አቃጥሉት» የሚለውን ሲተረጉሙ እሳት የተባሉ ኃጥአን ነዳያን ናቸው፤ ለእነርሱ ይሰጥ ማለት ነው> ብለዋል» እያሉ የኔታ ያስተማሩኝ ትዝ አለኝ::

ኀሊናዬ ግን ይህንኑ ማሰብ አላቆመም:: ታዲያ ይህ ገንዘብ እንደተባለው ከተሰረቀውና ከተዘረፈው የሚሰጥ ከሆነ ገንዘቡን ሰርቀው የሚበሉት እግዚአብሔር ባወቀው «እሳቶቹ» ይሆኑ? እንጃ እግዚአብሔር ይወቅ::

የመሥዋዕቱ ነገር ግን ቆጭቶኛል፤ ማስረዳት ነበረብኝ:: ምክንያቱም ለየዋሐኑ እውነት ይመስላልና:: ሌላ ሰው እንደ ይሁዳ እንኳን ከሙዳዩ ከመሥዋዕቱም ይሰርቃል፤ ልክ ይሁዳ እጁን ከወጭቱ ከትቶ እንደታየው:: በዚያው ሰዓት ይሁዳም ሐዋርያቱም ሥጋ ወደሙን ተቀብለዋል:: ነገር ግን ሌብነቱ ራሱን ጐዳው፣ በድፍረትም ሥጋ ወደሙን ስለ ተቀበለው እሳት ሆኖ ገንዘቡን እንደበላ እርሱንም ሥጋ ወደሙ እሳት ሆኖ አስጠመው እንጂ የመሥዋዕቱን ውላጤ የእርሱ ሌብነት አላስቀረውም:: አሁንም እንደዚያው ነው:: መቼም መች መሥዋዕት የሚከብረውና የሚያርገው በእግዚአብሔር ቃልኪዳን እንጂ በሰዎች ቅድስና አይደለም:: ... መሥዋዕቱስ ያርጋል!

«ጌታው ይጨምራሉ!» ረዳቱ ነበር:: አይ ደርሻለሁ፤ አልኩና ወርጄ የእግር መንገዱን ተያያዝኩት:: ... እግሬም ልቡናዬም መንገድ ላይ ነው:: እስከምንገናኝ ደኅና ሁኑልኝ::♦

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## « ጣና ገዳማት ክፍል 2»

በጣና ደሴቶች ላይ ስንት አብያተ ክርስቲ ያን እንዳሉ ያውቃሉ? በደሴቶቹ ላይ ስላሉት አድባራትና ገዳማት በውስጣቸው ስላሉት ቅርሶች፣ መዘክሮች፣ ስለታሪካቸውና ስለ አስገራሚው ተፈጥሮአዊ ገጽታዎቻቸውስ? ለኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ግንባታ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ ሰምተዋል?

----------- ለእነዚህ እና ለሌሎችም ጥያቄዎች መልስ የሚሹ ከሆነ አዲሱን ዘጋቢ ፊልም መመልከት ግድ ይለዎታል።

በቅርቡ የሚወጣው « ጣና ገዳማት ክፍል 2» ዘጋቢ ፊልም በዓይነቱና በይዘቱ የሚመረጥ ለጥያቄዎችም መልስ ይሰጥዎታል።

**በቅርብ ቀን**

አዘጋጅ የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲ ያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በኦድዮ ቪዥዋል እና ሥነ ጥበባት ሥራዎች ማዕከል
011124 61 81/0911667800/09 11318032

## ኤል ሮኢ የቆዳ ውጤቶች
## Elroe Leather



- የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን በልክ እንሠራለን
- እናድሳለን
- ለመንግሥት እና ለግል ድርጅቶች የዱቤ አገልግሎት እንሰጣለን

አድራሻ ለም ሆቴል ማትያስ ሕንፃ
አዋሽ ባንክ አጠገብ

Tell 0116546285/0116636505
Mob. 0911413206/0911892399
P.oB.50272
E-Mail--Elroeleather @ethionet.et.







Made in Ethiopia!

## የዕሥራ ምእት ልዩ የመዝሙር
## ቪሲዲ በገበያ ላይ




ነፍስዎን የሚያረካ መዝሙር ማድመጥ ይሻሉ?
ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የጠበቀ፣በቤተክርስቲያኒቱ የዜማ መሣሪያዎች የተቀናበረ በአባቶች የዜማ ሥልት የተቃኘ፣ነፍስን የሚሰረሥር መንፈስን የሚያነቃ፣ተመስጦን የሚያመጣ ልዩ መዝሙር በቪሲዲ የማኅበረ ቅዱሳን ቁ .3 ቪሲዲ ቀርቦልዎታል።

**ስብሐተ እግዚአብሔርን በማድመጥ ነፍስዎን ያለምልሙ።**

አዘጋጅና አሳታሚ:- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

## አዲስ መጽሐፍ




በእርግጥ እግዚአብሔር ለኔ ሕይወት ፍቃድ አለው?
ሳያነቡት ሊያመልጥዎ የማይገባና ለልብ ወዳጅዎ በገፀ በረከትን ሊሰጡት የሚችሉ ምርጥ መጽሐፍ
. የእእግዚአብሔር ፍቃድ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ምን እንደሚመስል በሰፊው ያትታል
. በመከራ ውስጥ ስንሆንእግዚአብሔር እንዴት አድር ኀመከራችንን እነደ ሚመለከተው ይናገራል
. በተለይም በአሁኑ ጊዜእግዚአብሔር የሚፈቅደው እውነተኛው የአምልኮ ሥርዓት የትኛው እንደሆና ሌሎችንም ጉዳዮችን ይዳስሳል።
መጽሐፍን ማከፋፈል ለምትፈልጉ
0912 14 10 44 ደውሉልን


ዋጋ 4.00

ሜጋ ማተሚያ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር

'

©

!"          #$          %

& '     (        )   *          $++